# አምስት ፡ ስድስት ፡ ሰባት



ከስብሃት ገብረ
እግዚአብሄር

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# አምስት ስድስት ሰባት

## እና

## ሌሎችም ታሪኮች

ከስብሀት ገብረ እግዚአብሔር

መስከረም ፣1981

የሽፋን ሥዕል ፥ መስፍን ሃብተማርያም

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

ቦሌ ማተሚያ ቤት

# ማውጫ

አሮጊት....4
“ፍራሽ አዳሽ?”.... 18
እኔ ደጆኔ ....22
እትዬ አልታዩ ....23
ተከታትለው ሸው ወደ ብሾፍቱ.... 28
ለጉድጓድ .... 34
ዘር .... 37
እናት.... 45
ሞትና አጋፋሪ እንደሻው .... 63
አምስት ስድስት ሰባት .... 93
ስለደራሲው በጥቂቱ....102

# አሮጊት

አያሌ ጐረምሳ የሙዚቃና የዳንስ ናፍቆቱ እንዲወጣለት ዳጉቶ ውቤ በረሀን ሞልቶት ነበር።

የፀሀይ ዳሌ ከውቤ በረሀ ሴተኛ አዳሪዎች ሁሉ ይበልጥ ያምራል። ያላት የሙዚቃ ሸክላ ደሞ ምርጥ ምርጥ ነው።

አንድ ቀን ማታ -- ወደ አራት ሰዓት ላይ--ቤቷ ቁጭ ብዬ ሙዚቃውን እየሰማሁ የውን ህልም ሳልም ፤ ዳሌዋ ሲወዛወዝ እያየሁ በምኞት ሀይቅ ስዋኘ ሴተኛ አዳሪዎችና ወንዶች ሲደንሱ ሲሳሳቁ እያየሁ ስለምደርሰው አስደናቂ መፅሀፍ ሳስብ ፤ እንደልማዱ የበሩ መጋረጃ ተውለበለበና ወደ ሣራ በኩል ተገለጠ። የገባው ጐረምሳ ወንድ አይደይለም። የጐረቤት ሴተኛ አዳሪም - አይደለችም። ኦቾሎኒና ከረሜላ- ማስቲካ ሻጭም አይደለም። አንዲት ቀጭን ጠይም አሮጊት ናቸው። ጊዜና እድፍ ያጠቆረው ቀሚስና ነጠላ ለብሰዋል።

ጥልቅ አሉና ሩምባ "ሚደንሱት ወንዶችና ሴቶች መካከል ቁመው ፣ ደስ በሚል ለስላሳ ድምፅ ሩምባ ሙዚቃውን ተወዳደሩት :

"አያልየው ሞኙ

ሰው አማኝ -- ሰዋማኘ!"

ስምንቱ ደናሾች ዳንሳቸውን ተዉና ሴትዮዋን በመገረም ተመለከቱዋቸው። ፀሀይ ሮጥ ብላ ሙዚቃውን አቋረጠችው።

"ለንየ ነው ጨኸቱን ያቆምሽልይ ውቢት?" አሏት?

"አዎን" አለች "ይዝፈኑ። "7

"እሺ የኒያለም። "

"ተይኛ -- ላልኩሞይ....... ተኳኩልዎ መይዳ

"ተይኛ _ _ላልኩሞይ-... ተኳኩልዎ መይዳ

አይን ወረ--ተኛ ነው... ይወዳል እንግዳ

አይን ወረ--ተኛ ነው-.... ይወዳል እንግዳ

አያል በጐንደር

ሽር እንበል ብሎኝ ነበር"

ሴተኛ አዳሪዎቹና ወንዶቹ እያጨበጨቡ ተቀበሉዋቸው፣

"አያል በጐንደር

ሽር እንበል ብሎኝ ነበር"

ሴትዬዋ አወረዱ ፣

እንዴ'ነሽ - እንዴ' ነሽ.......... አንባ--ባልሞይ

ሰው ታባቱ ገዳይ ይታረቅ– የለሞይ"

አሉና ታዲያ "አያሌው ሞኙ'ን እንደመቀጠል ሌላ ዜማ ጀመሩ ፤

"ላማ "ለሽ ወይ በርዬ--ላማ' ለሽ ወይ በርሄ

ላማለሽ ወይ በርዬ ላማለሽ ወይ በርዬ

ላጋባሽ ጐንደርዬ።"

ተቀባዮቹ ፤ "ምነው እማማ? ምነው ኣሮጊት?

-- ኤጭ! ሙዚቃውን አርጊ!" እያሉ ማጉረምረም ጀመሩ።

ኣሮጊቷ ፤

"ምነዋ ልጆችየ? አትቀበሉም?" አሏቸው። አንድ ሱፍ የለበሰ ደስ የሚል ቀይ ውጣት ፀሀይን እንዳቀፈ ፥

"ዘባረቁት እማማ፡፡ እንዴት እንቀበል?" አላቸው

"ዋ! ልዥየ፤ ካልዘባረቅሁማ ምኑን አበድሁት?" ሰዎቹ ዝም ኣሉ፡፡

"ለይላ ዘፈን ላውርድላችሁ ይሆን? ወይም የጐጃም ወይም የምንጃር ወይም"

"አንፈልግም!" ብሎ ጮኸ፡፡ አንድ ቆዳ ጃኬት የለበሰ ወጣት ነው፡፡ ረዥም ሉጫ ፀጉሩን በጠርሙስ ሙሉ ቅባትና ባምስት አይነት ብሩሽ በጐን በኩል አስተኝቶ ፤ ግንባሩጋ እንደ ጉተና አቁሞታል ኣውራ ዶሮ፡፡ ፂሙን ግማሽ ጉንጩ ድረስ አሳድጓል- ኤል ቪስ ፕሬዝሊ፡፡ ሁላችን የእግዚአብሄር ፅሁፍ ነን፡፡ እግዚአብሄር "ውበት" የሚለውን ቃል ሲፅፍ ፀሀይን ፈጠረ ፤ "እብድ" ለመፃፍ እኚህን አሮጊት ፈጠረ ፤ "ከንቱ" ሲል እኔን ሰራ ፤ "ጉራ" የሚለውን ቃል ሲፅፍ ደሞ ባለቆዳ ጃኬት አውራ ዶሮ ቀረፀ፡፡

ይህን ሆሊውዳዊ አውራ ዶሮ ውቤ በረሀ ውስጥ ብዙ ጊዜ አይቼዋለሁ፡፡ እነ ጥላሁን እነአሀዝ ወይም ሌሎች የረብሻ ሰዎች በሌሉበት ቦታ ፤ ይነሳና ይንጐራደዳል ይሸልላል ፤ ሴቶችን በጥፊ ይመታል ፤ ወንዶቹን ይገላምጣል፡፡ እነ ጥላሁን እነአሀዝ ሲገቡ ግን ቶሎ ብሎ "ሀይ ኤቭሪቦዲ" (ታዲያስ ጐበዝ?) ይላቸውና ይጨብጣቸውና ሂሳብ ስንት ነው?" ብሎ እንደ ጨዋ ሰው፡- ክፍሎ ቀበሮ እንዳየ አውራ ዶሮ ሾልኮ ይጠፋል፡፡ ዛሬ ጥቁር ቆዳ ጃኬት ፤ በሽሚዝ ፈንታ አንድ ጥቁር ካናቴራ (የደረቱን ጡንቻ ቅርፅ አጉልቶ የሚያሳይ) እና ሰማያዊ ጂንስ ሱሪ ለብሷል፡፡ ቦዲ መሆኑ ነው፡፡

አሮጊቷ ዘወር ብለው ኣዩት፡፡

"ምናለ ብንጫወት ልዥየ?" አሉት፡፡

"ጋዴም ሺት! እኛ ልንደሰት ነው የመጣ ነው፡፡"

"ዛድያ እንዝፈና፡፡"

“ዘወር በይ ባክሽ ፤ ሺት!” አመናጨቃቸው። እጆቹን እኋላ ኪሱ ውስጥ ከተተና እንደ ማርለን ብራንዶ ቆመ።

“ዘወር በይ? እንየን? ማን መሰልሁህ አንተ? ወንድምየ የራስ አበበ መድፍ ተኳሽ ነው። ያንዱዱዋል!”

አውራ ዶሮው እንደማርለን ብራንዶ ቀስ እያለ እየተንቀባረረ ፤

“አንቺሳ ምንድነው ስራሽ?” አላቸው

“ድርወ የትልቅ ሰው ልዥ ነበርሁ። ኣሁን ግን እብድ ነይ ፡ ኸ!ኸ!ኸ! እንዳንተ ያለው እንኳ አንቺ ይለያል።! ኸ!ኸ!ኸ!”

ቆዳው ጃኬት ተናደደና ፀሀይን ሙዚቃውን እንድታስዘፍን አዘዛት። ቡጊ ተጀመረ።

ኣሮጊቷ “የንየሳ ዘፈን ፡ ቆንጂት?” አሉ።

“ምን ላርግ እማማ?” አለቻቸው። ጥሩ ልጅ ነች እቺ ፀሀይ።

“በሉ ተዉት። ተዉት! እንየ ምን እንዳይቀር ብይ?” ወደ አውራ ዶሮው ዘወር ብለው ዳንስ ሊጀምር ሲል ፤

“አዉ? አለ ዥቡ። ሚያው! አለች ድመቲቴ፡። ይኸ ሚስጥር ነው። እብድ ካልሆንህ ኣይገባህም። ደምወ አንተ ለማበድ ተስፋ የለህም። አለሌ!” አሉትና ወደኔ መጡ።

ብቻየን ነበር የተቀመጥኩት። እጐኔ አንዲት ትንሽ ክብ ጠረጴዛ አለች። ከሷ ቀጥሎ አንድ ባዶ ወንበር አለ። እሱ ላይ “ውገብየን! ወገብየን!” እያሉ ተቀመጡ። አዩኝ። አየኋቸው። የሚደንሱትን ወጣቶች ኣዩ። ይሽከረከራሉ። ቀይ ዱላ የመሰለ አምፑል የተለጠፈበትን ኮርኒስ ተመለከቱ። የመጠጥ መደርደሪያውን ቃኙ ፤ ከዛ ፊቴን አጠኑ። ትንንሽ ፈጣን አይኖቻቸውን ወደተደረደሩት የመጠጥ ጠርሙሶች እንደገና ጣል አደረጉና ፤

“ጠምቶያል ልዥየ” ኣሉኝ።

“ይጠጡዋ!” አልኳቸሁ።

“ውሀ አልጠማይም።”

“አውቃለሁ”

“ትከፍልልያለህ? ባሁን ዘበን ባለብየቱ ይሸጣል

“ንዝር አይጋብዝም። ክፉ ዘበን?”

ፀሀይ ነጭ አረቄ አመጣችና አጠገባቸው ክቧ ጠረጴዛ ላይ ስታስቀምጥላቸው የሚያንፀባርቅ ፈገግታ አሳየችኝ። እቺ ፀሀይ በጣም ቆንጆ ናት። አቤት የዳሌዋ ውዝዋዜ!

ኢሮጊቷ የጠወለገ ጅማታም እጅ ከጠረጴዛው በላይ ዘረጉና እጅጌየን ሳብ እያደረጉ ፤

“ስማይ ልገርህ ልዥየ” አሉኝ። “እብደቱ እንደ ዠመረይ ሰሙን ወራትና ዘበናት ፡ ሰው መፈንከት እወድ ነበር። ዛድያም አንድ ሁለትዜ ሲጠፍሩይ ግዝየተውሁት። አሁን መሳደብ ብቻ ነው። ደምወ አሁን ተሳደብሽ ብለው ቢያስሩይ ስድቡን እተው ነበር። ምን አለች በልይ። ነገር ግን አየህ ስድብ የማታይ ሰንበር ወይም ቁስል አይተውም። እንደዚህ ነዋ!

“ማበዴን ያወቅሁት ጥርስየ ላይ አንዷት ፀጉር የበቀለች ግዝዬ ነው። ” ሁለቱ የላይኛ የፊት ጥርሳቸው ተሸርፏል። “ከዛምልህ እቺን ፀጉር ጥርስየ ላይ በቅላ ካዩ ሰዎች ማበድየን ሊያውቁብይ አይደለምንዴ? ኣልሁና ፀጉሪቱን ለመንቀል በሀይል ስስባት ጥርስዩንም አብራ ይዛ ተነቀለች። እና ሸራፋ ሆንሁ እልሀለሁ። እየኝ!” እኝ አሉ። የሸራፋቸውን ጉድጓድ አይቼ ልስቅ ምንም አልቀረኝ።

አረቄያቸውን ፉት አሉና እያጣጣሙ ፤ “እም! ይህች አረቅየ ግሩም ናት። ምኒልክ ይሙት! አየለች መድኃኒቱን ያጠጣችይ ባረቄ ነበር። እቺ

እባብ!! እኔን የጐዳች መስሏት። እንየስ ርስቱ ምኔም አይደል። ይልቅ ኩነኔ ከመግባት እንዲሁ ብትለምነይ እተውላት አልነበረም? ያን የመሰለ የጠኸ ንግድ እያለይ መቸ ርስቱን እፈልግ ነበር? ግን በሰማይ ብየት እንፋረዳታለን። በጭራሽ አልተዋትም። እንዲያውም የሰማይ ብየት በር ለስዋ አይከፈትም። ምናለች በለይ! እንደዚህ ነዋ።

“ይኸ የማን ነው ብየት? “የንየ” አትልም?”

“የኔ”

“ይህ የማን ነው ብየት?” ክቧን ጠረጴዛ ልዩ ልዩ ቦታ እያንኳኩ ነው እንደዚህ የሚያናግሩኝ።

“የኔ”

ይህንኑ ጥያቄና መልስ ሰባት ጊዜ ያህል ከደጋገምነው በኋላ እንዲህ አዜሙ ፤

“ያዬ-- ሎልየ!

የብር መስ--ቀልየ!

ተዉ አስገቡ -ይ ዛርዬ!”

ዜማውን ስሰማ ፤ ድሮ እህቶቼ የሚጫወቱትን ጨዋታ አስታወስኩና እንደዚህ መለስኩላቸው

“ያዬ-ሎሌ!

የብር መስቀሌ!

አናስገባም ዛሬ!”

ድንገት የጨዋታው መንፈስ ከፊታቸው ተገፈፈ።

“ምነው ልኸየ ፤ እብድ ናት ብለህ ነው አናስገባም ዛርየ የምትለይ?” አይናቸው እንባ እያቀረረ “ኸረ ተው በማንም ሊደርስ ይችላል”

“አይዞዎት!” ብዬ እንደትንሽ ልጅ አባበልኩዋቸው። ውሸት ከየት እንደመጣልኝ እንጃ ፡

“በመጀመሪያ ጊዜ ማስገባት ጨዋታው ስለሚከለክል ጨዋታው እንዳይፈርስ ብዬ ነው እንጂ ሁለተኛ ጊዜ “ተዉ አስገቡኝ ዛሬ” ሲሉ ላስገባዎት ነበር” አልኳቸው።

ሀዘኑ ባንዳፍታ ለቀቃቸው። “እውነት?” አሉኝ

“እውነት”

“ፈረሰኛውን?”

“ፈረሰኛውን። በሉ እንደገና

“እሺ።” ሊጀምሩ አሉና ተዉት።

መሬቱን ማየት ጀመርኩ። ሳቅ ፡ እፍረት። ከባድ ሀዘን ልቤ ውስጥ ተቀላቀለ። የወለሉ ሳንቃ የሚገናኝበት ስንጥቅ ውስጥ የነበረው ስንጥርና ከመጥረጊያ ረግፎ የተቀረቀረ ሳር ይታዩኝ ጀመር። ሙዚቃው ቡጊ ሲጫወት የደናሾቹ እግር ወለሉን ሲፈትግ ተሰማኝ።

አሮጊቷ አዜሙ ፤

“ያዬ--ሎልየ

የብር መስ--ቀልየ

ተዉ አስገቡ--ይ ዛርየ”

ዜማ ፤ “ያዬ-ሎሌ

ነይ ግቢል--ኝ ፍቅሬ” አልኳቸው።

ከራሴ ፈጥሬ ነው እንጂ ጨዋታው ውስጥ ያለበት አይመስለኝም። የሆነ ሆኖ አሮጊቷ ደስ አላቸው።

"ገባሁ አሉ። አንተ ደምወ ተራህን ለምነይ" አሉኝ።

ተራዬን "ተዉ አስገቡኝ ዛሬ" አልኳቸው።

እንዲህ ስንል "አሊ ሆይ አላሊ ሆይ" እና ሌሎችም የልጅነት ጨዋታዎች ስንጫወት ግማሽ ሰአት ያህል አሳለፍን።

ይህን ሁሉ ጊዜ ጉረኛው ባለቆዳ ጃኬት እየደነሰ እየጠጣ ያፈጥብኛል። "ሺት ሁሉ እዚህ!" ብሎ እያጉረመረመ ነበር። እሱ አሮጌቷ እንዲወጡ ሲፈልግ እኔ መጠጥ ስለገዛሁላቸውና ስላጫወትኩዋቸው ብቻ ሳይሆን ፤ ፀሀይ ከሱ ጋር እየደነሰች ከኔ ጋር ስለምትሳሳቅም ነው። ዋናው ምክንያት ግን እኔ የለበስኳት ቆዳ ጃኬት የሱን ቆዳ ጃኬት ስለምታስንቅ ነው። ተነስቼ ከሱ እኩል ብሸልልና ብንጐራደድ ፈርቶ እንደሚተውኝ እርግጠኛ ነበርኩ። ግን ያሮጊቷ ጨዋታ በየቀኑ አይገኝም ፤ ድንገተኛ ያልታሰበ አጋጣሚ ነው ፤ እንዲያመልጠኝ አልፈለኩም። ከዚህም በላይ መሸለል አልወድም። ስለዚህ ፡ ልክ አንዱ ሸክላ አልቆ አጭር ፀጥታ ሲከተለው ፤ ቆዳው ጃኬት ፀሀይን ይዞ ሳለ ጮክ ብዬ እንዲህ አልኳት፤

"ፀሀይ! ጥላሁንና አህዝ መጥተው ነበር?"

"የለም"

ሰኣቴን እያየሁ "አፋ! እነሱ ደሞ ሰው መቅጠር አይሰለቻቸውም። እስቲ እባክሽን እዛኛው ቤት እንዳሉ ሰው ላኪና አስጠይቂልኝ"

"እሺ" ከውብ ፈገግታ ጋር።

ይኸኔ ሌላ ሸክላ መዝፈን ጀመረ። ከዛ በኋላ ጉረኛው ባለቆዳ ጃኬት እዛ መኖሬን ጨርሶ ረሳ። ስለብልጠቴ በሰፊሁ ራሴን ሳሞግስ ነበር። ብቻ ያሮጊቷ ወሬ ራሴን አስረሳኝ።

እንደገና እጅጌዬን በጅማታቸው እየሳቡ ፤

“ስማይ ልዥየ” አሉ። “እነአህዝ እነግእዝን ተዋቸውና ፤ አረቂዬን ጨረስሁ።”

ፀሀይ አረቂውን አመጣችላቸው። አሁንም የሚያንፀባርቅ ፈገግታ አጠጣችኝ። እቺ ፀሀይ ውብ ነች ብዬ የለ? ስለዳሌዋ ተናግሬአለሁ? አሁንስ ዳሌዋን በተለይ ለኔ ለግል ደስታዬ ያወዛወዘችው መሰለኝ። ስለዚህ

ስለዳሌዋ ውፋሬና ሙቀት ፤ ልስላሴ--ላስብ ስል ያሮጊቷ ወሬ ከለከለኝ፤

“ያባትየ ፈረስዎች ለእራት እንዝራ በወጥ ከነቅልጥም ካልመጣላቸው ቤት አፍርሰው ይሄዱና የዥብ እራት ይሆናል።

“አዉ! አለ ዥቡ።

“በልዥነታችን አንዲት የዥብ ቋንቋ ሚያውቁ አክስታችን ነበሩ። አንድ ቀን ማታ ከራት በኋላ ቁጭ ብለን እሳት ስንሞቅ ዥብ ጮኸ። አዉ! አለ።

“ሰአሊ ለነ ቅድስት!” አሉና ሰባት ጊዜ አማትበው ሲያበቁ ራሳቸውን ጉልበታቸው ላይ ደፉ።

“ምነው እቴ ሜቴ ምን ሆንሽ?” አላቸው አባባ።

“ዥቡ ነው” አለች እማማ። ያነየ እርጉዝ ነበረች።

“ዥቡ ምን አለ?” አልናቸው።

“ዛሬ ፈረሱን ትተን ፈረሰኛውን ነው (ምንበላው ፤ አለ” አሉ።

“በነገታው ማለዳ ገና ለማኝ ሳይነሳ የባለቤታቸው ፈረስ ባዶውን መጣ። የፈረሱን አንገት ኣቀፉና ስቅስቅ ብለው አለቀሱ።

“ባላቸውን ጅቡ በላው?” ብዬ ጠየቅኳቸው አሮጊቷን።

“ከየት መጥትዎ ልጌዋ? ያን ግዝዬ ባላቸው ከሞተ ሶስት አመቱ ነበር። ነብሱን ይማረውና።”

እንዳልስቅ ፈርቼ ያዝኩት።

“በልዥነታችን ከብት እንጠብቅ ነበር። ያባቴ ፈረሶች--እሱንማ ነገርየሀለሁ። ኺኺኺ! ለምን መሰለህ እንዲህ ‘ምስቀው? በጣም ስለማዝን ብቻ። የሀዘን ቋት ፤ የሀዘን ቀፎ። የሚያሳዝነኝን ታውቃለህ?

“በልዥነታችን ኩኩሉ ፤ ቅልቦሽ ፤ ገበጣ ፤ እንጫወት ነበር። አሁን እንግዲህ አድግናል፤ሰው ሲሞት እየወሰድን መቅበር ነው። “ግባ መሬት” ብለን አፈር ማልበስ ፤ ደንጊያ መጫን ነው።። ተነስቶ እንዳይረብሽ። ምኒልክ ይመት!” አነጋገራቸው አንድ ያዲሳባ አንዴ የባላገር ነበር።

“እረኛ ሳለሁ በጣም የሚያስቀይ ያህያ ዥራት ነበር። እህ! ህ! ህ! ይወዛወዛል ይንቀለቀላል። ኣያርፍም። ኣይገርምህም?

“ግን አህያ በጣም ያሳዝነያል። ሲጮህ ሰምተህ የለ? የሀዘን ጩኸት ነው። የሀዘን ቀፎ ፤የሀዘን ጥሩንባ።

“እህል ይጫንብያል ፤ እንጨት፤ ጭድ! ሁሉ ነገር ይጫንብያል። ዠርባዬ እስኪቆስል ስድብም ሳቅም ይጫንብያል ፤ መከላከያ ቀንድ የለይ ፤ የሚከራከርልይ የለ። በምን ፈረድክብይ?” ብሎ እግዜርን ያማርራል። ደምወ እውነቱን ነው። በምን ፈረደበት?

“ዛድያ እግዜር አያደላም ትለያለህ? አንዱን አህያ አንዱን እብድ ፤ ሌላወን ደምወ ንጉስ አርጎ ሲፈጥር? ከዚህ የበለጠ ማዳላት ከየት ይምጣ?

“እያት እቺን ጥርስየን። አንድ አሽከር ነበረን። ጠረንገሎ የገደል ቅራፊ ፤ አካፋ እግር ፤ መጥረቢያ ጥርስ ጐመን ጠጉር። አቤት የብብቱ ግማት! ቁናስ! እንጨት ተሸክሞ ሲሄድ አፌን ቢለይ አንዷ ጥርስዬ--እቺ ወለቀች። ወሰድሁና ጓሮ ቀበርኋት። እንግዲህ አንዳንድ ቀን ትዝ ስትለይ እየኸድኸሁ ቆፍርዬ አወጣትና አይቻት ስቅስቅ ብዬ አለቅሳለሁ። ዛድያ አንድ ጥቁር ውሻ ነበረን። አንድ ቀን መልሽየ ስቀብራት አይቶ ኖሮ በልየለሁበት ቆፍሮ

አመጣትና በላት። እቼኛይቱ ጥርስየ ደምዎ ዝም ብላ ረገፈች ፤ ስስቅ። እውልይ ፤ ሰው በሸራፋው ይስቃል?”

አረቂያቸውን ፉት ብለው እያጣጣሙ “ግሩም አረቂ! አየለች መድሀኒቱን ያጠጣችይ ባረቂ ነበር። ለካ ነግርየሀለሁ። በጣም የምፈራው ምን መሰለህ? ብቻ ለሰው አትንገር። አሁን እንግድየህ ካበድሁ ስንትናስንት ዘመን ሆነይ። እብደቱን ለምጄዋለሁ። እንዲያውም ከንግድህ ያለ እብደትየ ልኖር አልችልም። ዛድያ አሁን አየለች እንደልማድዋ ምቀኝነት ይዟት ያንን እብደት የሚያረክስ መድሀኒት ብታጠጣይስ?”

“ትፍትፍ!” አሉና እያማተቡ ወደላይ እያዩ “ውይ ኣያርገው! ለቁልቢው ተስያለሁ። እስከሞት እብደትየን የጠበቀልይ እንደሆነ መጋረዣ እሰጠዋለሁ።

“እግርዬን አሳይችየሀለሁ?......... ጥርስየንሳ? እሱንማ እንዴት አሳይሀለሁ? የለምኮ። አየኸው? የለም። አላመንኸይ እንደሆነ ፈትሸይ። .......ጥርስዬ ከወለቀች ወዲያ አለም ቢቃይ አልሁ። ስበላ ወይም ስስቅ ጥርስየ ትዝ ትለይም የለ? ልታነቅ እላለሁ።

“ጥርስየ ነፀነቀ ምኑን ኖርሁት? ልሙት አልሁ። ልታነቅ አልሁ። ገመድ ቋጠርሁ። ” አሁን እንግዲህ ምን እንደሚሉ ጠፉችው። “እና ይኸውልህ--ዛድያልህ ልዥየዋ--ሰው አስጣለይ እንደልማዱ። እና ፍርድ ቤት ወሰዱይ።

“ምን ኣድርጋች?”

“ልትታነቅ ስትል ደረሰንባት”

“ትታነቃ! ትፈንጠር! ትሽቀንጠር! ትሽከርከረ!” እንዲይህ ነው የዛርየ ዘበን ዳኝነት እልሀለሁ። ምኒልክ ይሙታ!

“በል ለእራቴ ስሙኒ ስጠይና ልሂድ ልዥየ” አሉና ብድግ አሉ። ስሙኒ ስላልነበረኝ ፀሀይን የብር ምንዛሪ ጠየቅኳትና ሀምሳ ሳንቲም ሰጠኃቸው።

“ስሙኒ ይበቃያል ልዥየ ፤ እምብዛም መለገስ ያከስራል። ” ወደ ፀሀይ ዘወር ብለው።

“ልምከርሽ ልዥየ። ይህን ጐረምሳ አትልቀቂው። የሚያጠግብ ወንድ ባይኑ ያስታውቃል። ወይንየ ወጣት በሆንሁ!” ፀሀይ እንደልጃገረድ መሬት መሬቱን ማየት ጀመረች

“በሉ ደህና እደሩ ልዦችየ!”አሉንና ሄዱ። ካንድ አስር ደቂቃ በኋላ ተመለሱ።

“ከግማሽ መንገድ ተመልሽየ መጣሁ። አንድ ቆንዦ የጐንደር ተረት ልንገርህ እንድታስታውሰይ ፤

--አንተ ሰው ከየት መጣህ?

--ከግብጥ ፤

--ምን ይዘህ?

--ጭብጥ ጥጥ

--በምን አስረህ?

--በድንጋይ ልጥ

--ይኸስ ሰው ዋዘኛ ነው!

--ዋዘኛስ ክራር ነው

--ክራርስ ጥዝ--ንጥ ባይ ነው

--ጥዝ--ጥዝ ባይስ ንግብ ነው

--ንብስ ነዳፊ ነው

--ነዳፊስ ደጋን ነው

--ደጋንስ ጠማማ ነው

--ጠማማስ መንገድ ነው

--መንገድስ ወሳጅ ነው

--ውሀስ ብም--ብም ባይ ነው

--ብም--ብም ባይስ ጐሽ ነው

--ጐሽስ ዘላይ ነው።

--ዘላይ ፌቆ ናት

--ፌቆ ስትዘል አግኝቼ በልቼ መጣሁ።

---ሰባች ጐፈየች?

--ሳትታረድ መጣሁ

--የሆነስ ሆነና ስምህ ማን ነው?

--ላገር አይመች

--ማን አወጣልህ?

--ጉረቤቶች

--የናትህ ስሟ ማን ነው?

--ሳልወለድ ሞተች

--የሆነስ ሆነና እግዚሀርን አይተኸዋል አላየኸውም?

--አዎን አይቸዋለሁ

--ቀይ ነው ጥቁር?

--ተከናንቦ ነበር

--ረዥም ነው አጭር?

--ቁጭ ብሎ ነበር።

"በል ደህና እደር ልዥየዋ። ያችን ቆንዥወ አትልቀቃት። ዘማም ነች። ደሞ ፈልጋሀለች። ገንዘብ ከሰጠሀት ግን ነገሩ ተበላሸ። ስየት የሚተኛ ሁሉ ወንድ እንዳይመስልህ። ብቻ እኔን ከሰው የቆጠርኸይን ያህል እሷን ከስየት ቁጠራት። በል ደህና እደር። አሁንስ አልመለስም። መኽድየ ነው መሰናበትየ ነው፤ ችላው ምንድነው?" ብለው አንዴ አዜሙልኝ ሳይጮሁ።

"ደህና እደሩ" አሉ

ሄድ ኣሉ። መለስ አሉ። ቁጭ ካልኩበት ጐንበስ ብለው ግንባሬን ሳሙኝ። በኋላ ተፉብኝ።

"ትፍ--ትፍ--ትፍ! ክፉ አይንካህ እምዬ። አርባእቱ እንስሳት ይጠብቁህ!"

ጥሩነቱ ሰዉ ሲደንስ ሲጫወት ስለነበረ ይህን ያስተዋለ አልነበረም። ፊቴን በመሀረብ ስጠርግ ፀሀይ መጣችና

"ና ወሀ ልስጥህ ታጠብ" አለችኝ። ሲተፉብኝ አይታ ኖሯል። መኝታ ቤቷ ገባን። ውሀ የሞላ ጆግ ሳህን ውስጥ ቁጭ ብሎ ነበር። ፊቴን አስታጠበችኝ። አልጋዋ ግርጌ የተዘረጋውኝ ፎጣ ላነሳ እጄን ሰደድ ሳደርግ

"ተወው" አለችኝና ከመሳቢያ ውስጥ የታጠፈ ፎጣ ኣውጥታ ሰጠችኝ። ፈገግታዋ ያበራል።

"ያ ሁሉ ወሬ ስለምን ነበር?" አለችኝ።

«በኋላ ልንገርሽ» አልኳት።

«መሬት መሬቱን ኣየች።

# “ፍራሽ አዳሽ?”

አቶ ወንዳፍራሽ እኚህ ፍራሽ አዳሽ የዋዛ ሰው እንዳይመስሉዋችሁ። ሰሎሞን ራሱ ከጥበቡ ቆንጥሮ የሰጣቸው ሰው ናቸው።

ኣሁን ይኸ ልጃቸው አዝብጤ--ከነስሙም አዝብጤ በአምስት ዓመቱ የአንድ ሙሉ ሠራተኛ ሥራ ሲሠራላቸው ይውላል--የኔታ ትምህርት የለም ያሉ ለታ።

እንግዲህ በፍራሽ ሥራና እደሳ የሚኖሩ እንደሚያውቁት ሁሌ ትራሱን ጥጥ ሞልተው ጠቅጥቀው ከሰፉት በኋላ ሲያዩት ጠማማ ኳስ እንጂ ትራስ አይመስልም። በስንትና ስንት ትግል በስንትና ስንት ቡጢ ጥፊና ልዩ ልዩ ክርን መሳይ ጉሸማ ነው ልክ የሚገባው ትራስ የሚሆነው።

ታዲያ አዝብጤን መንገድ እየጠበቀ የሚመታው ተለቅ ያለ ልጅ አለ "መኮንን የሚሉት።

አቶ ወንዳፍራሽ ይህን ያውቃሉ ስለዚህ ትራስ ጠማማ ኳስ በሚመስልበት ሰዓት አዝብጤን ይጠሩትና እንደሚከተለው የወንድ ልጅ ወግ ያስተምሩታል ፤ በጥበባቸው።

ቀኝ እጁን ለቀም አርገው ይይዙና

“አንተ ማን ነህ?!” ይሉታል በሚያስፈራ ድምፅ።

“እኔ አዝብጤ!” ይላቸዋል ሳይፈራ ፥ እጁን እየጨበጠ ግን ለማምለጥ ሳይቃጣ።

“ኣዝብጤ ማ?!” ሲሉት

እንደ ነጐድጓድ ጩኸት “አዝብጤ ወንዳፍራሽ!”

ብሎ ያመልጣቸውና ቡጢ እንደጨበጠ በነብር መሳይ ዓይን ይመለከታቸዋል።

“ወንዳፍራሽ ፍራሻዳሽ?”

“እንዴታ!”

“ያ ጀግናው? ያ ሥርቶ የሚበላው?”

“አዎና!”

“እውነት አንዝብጤ ወንዳፍራሽ ፍራሽ አዳሽ ከሆንክ” ይሉታል ትራሱን እያሳዩት “ይኸውና ኣመፀኛው መኰንን። ትንንሽ ልጆች እየደበደበ ያስለቅሳል። መጫወቻቸውን ይነጥቃል። ንሳ ደብድበው ፤ ቅጣው ይህን አመፀኛ። የት የት እንደሚመታ ታውቅ የለ?”

“አውቃለሁ”

“በል እንግዲህ ሥራውን ኣሳየው”

“አንተ! ልጆች ለምን ትመታለህ?” ይለዋል ትራሱን።

ትራሱ ዝም።

“ይኸውልህ እንግዲህ፤ ማናለብኝ ብሎ ኵርቶ ዝም ብሎ ያይሃል”

አዝብጤ ሆዬ ዘሎ በጉልበቱ ትራሱ ላይ ያርፍና በቡጢ እየደበደበው “በል ተናገር!” ይለዋል።

“ዝም አልክ? እንካ ቅመስ!” እያለ ስንትና ስንት ቡጢና ክርን ሲያወርድበት ኣቶ ወንዳፍራሽ ሌላ ትራስ መሙላት መጠቅጠቅ ይጀምራሉ።

አዝብጤ ትራሱን እያገላበጠ ወዶ እስኪጠላ ድብድብ ካረገው በኋላ አቶ ወንዳፍራሽ “በቃው መሰለኝ፤ እንግዲህስ ሁለተኛ ደፍሮ አይማታም” ሲሉት።

“ሁለተኛ ትማታለህ? ሁለተኛ ሸንኮራዬን ትነጥቃለህ? እ? ይለመድሃል? ሁለተኛ ፈሪ ብለህ ትሳደባለህ!?! ት--ት--ትሳደባለህ?” እያለ ምራቅ ፡ ቡጢና ክርን ካወረደበት በኋላ!

“በቃው አይለምደውም። አታይም ያ ያሳበጠው ኩራቱ እንደለቀቀው?” ይላሉ አባትየው “በቃ ፡ በቃ ይበቃዋል። ኧረ በገላጋይ በሽማግሌ ይተዉት እባክዎን!” እያሉ በብዙ ልመና ይገላግሉታል ትራሱን። አሁንማ ጠማማ ኳስም አይደለ ፥ መኰንንም አይደለ። ትራስ ነው ዳውላ ሊሆን ምንም አልቀረው።

አዲሱን ትራስ በቡላ ክር እየሰፉ

“ይኼ አሁን የምሰፋው ደሞ ማን ይመስልሃል?” ይሉታል አቶ ወንዳፍራሽ

“ማን ነው?”

“ጭራቅ ነው። ክፉ ሀይለኛ ጭራቅ። ስንትና ስንት ልጅ የበላ። ይህን ታዲያ ይዞ በቡጢ አፈር ማስጋጥ።”

“አፈር አስግጠዋለሁ ቶሎ ጨርሰው”

“ተው ይበላሃል”

“ኧረ! እሱ ሊበላኝ? እኔ ደሞ ዘልዬ ሆዱ ላይ ቁጭ! አይኑን እሽት! በሸንኩርት እሽት! ማየት ሲያቅተው በጉጠት ጐጥጥ! እውር ሲሆን በሾኬ ጥልፍ! ሲወድቅ ርግጥ! በጭቃ እግሬ ርግጥ! ከዛ በመዶሻ አፍንጫውን? በእሳት ፀጉሩን! ደሞ ፀጉሩ ሲቃጠል ይገማል አይደል?

“አዎን። ግን ማቃጠል አያስፈልግም። እሳት መጥፎ ነው። አቃጥል የተባለውን ትቶ ያልተባለውን ያቃጥላል። መደብደብ ይሻላል። ”

“እደበድበዋለሁ። ደሞ ከፈለገ እንደ ወረቀት እቦጫጭቀዋለሁ። ብጥስጥስ አድርጌ ስወረውረው፡ ነፋስ ደሞ ወስዶ ጭቃ ውስጥ ጭምር!

ሰዎች ደሞ ሲያልፉ በእግራቸው ጭፍልቅ ጭፍልቅልቅ ያደርጉታል። እንደማማ የማነሽ ሚጩት። አባባ?”

“እ” ይላሉ አቶ ወንዳፍራሽ

“አሁን እማማ ዠማነሽ_እኔን ቢራራ ፈልቁኝ እንደሚጩትዋ ጭጭ ያረጉኛል?”

“ምነው?”

“እንደዚች ሚጩት ነው ጨፍልቄ ጭጭ” ማረግህ አሉኝ። ይችላሉ ሊጨፈልቁኝ?”

“ሊጨፈልቁህ ቢመጡ ምን ታረጋለህ?”

“ኧረ! ሊፈልቁኝ እንደ ሚጩት? እኔን? እኔ ደሞ በቢላ እግራቸውን ቁርጥ? እጃቸውን ቁርጥ ጣታቸውን ቁርጥ! ደሞ አፍንጫቸን ጉምድ! ምላሳቸውንም ካፋቸው አውጥቼ ቁርጥ! ደሞ እንጥላቸውን ቁርጥ! አባባ?”

“ወይ” አሉት አቶ ወንዳፍራሽ ፡ ሰፍተው ክሩን ቋጥረው በጥርሳቸው እየበጠሱ።

“የማማ ዠማነሽ እንጥል ይህን ያክላል?”

“እኔ እንጃላቸው። እኚወልህ እንደሚጩት ጨፍልቃቸው” አዝብጤ ወንዳፍራሽ እማማ ዠማነሽን እያገላበጠ በቡጢ በክርን ሲደበድብ አቶ ወንዳፍራሽ ወደ ፍራሽ ሥራቸው ተመለሱ፡-- እቺን ጥያቄ እየመረመሩ።

እቺ አሁን የምሰፋት ፍራሽ ስንት ነገር ልታይ ልትሸከም ይሆን? ኣዝብጤ የሚመታትስ ትራስ ስንት ነገር ልትሰማ ይሆን? አቶ ወንዳፍራሽ ይህን እያሰላሰሉ ዓይናቸውን ወደ ሰማዩ አቀኑ። “አዎን ፡ ከሁሉም በላይ ያለ ሰማይ ነው። ከሰማይ በታች ያለው አሮጌ ቆርቆሮ ነው። ከቆርቆሮ በታች ኮርኒስ ፡ ከኮርኒስ በታች አልጋ። ካልጋ በላይ ፍራሽ ፡ ከፍራሽ በላይ ሹክሹክታ ነው። ከሹክሹክታው ውስጥ ምስጢር ነው። ሁሉም ምስጢር

ነው።" ኣሉ ኣቶ ወዳፍራሽ በጥበባቸው እየሡፉት ያንን ፍራሽ። ፍራሽ ለመጋደም ፡ ፍራሽ ለሹክሹክታ ፡ ፍራሽ ለእንቅልፍ ፡ ፍራሽ ለህልም.....

1967

# እኔ ደጀኔ

አጋፋሪ ደጀኔ ስልብ ናቸው። ሚስቲቱ ወንድ ሲቀያይሩ ዝም አሉዋቸው። ሴትዮዋ ግን የድፍረታቸው ድፍረት አረገዙ። መች ይኸ ብቻ? ዘጠኝ ወር ቆይተው ጠብ አደረጉት'ዪ ከነቃጭሉ።

አጋፋሪ ደጀኔ ተንኰለኛ ቂመኛ ናቸው። ልጁን "እኔ" ብለው ስም አወጡለት። እናቲቱ፡ የወንድወሰን ሊሉት ሞከሩ። አጋፋሪ ግን በእልህ ልጁን ከህፃንነቱ ጀምረው "እኔ" እያሉ እየጠሩት አሳደጉት።

ልጁ ቀውላላ ጐባጣ ሆነ።

ሰዎች "እኔ ደጀኔ" እያሉ ይስቁበት ጀመር ከልጅነቱ ጀምሮ። እናት ይህን እየሰማች ልብዋ እርር አንጀትዋ ቅጥል።

በዕድሜ ከፍ ሲል "እኔ"

"አባዬ ሰዎች በሄድኩበት ይጠሩኛል" አላቸው።

"እና ዘወር ስትልስ?"

"ዘወር ስል አልጠሩኝም"

"በስመአብ በል ልጄ። ማበድህ ነው። ያቺ አዋላጅ አቢሾ አጠጣው ስትለኝ እምቢ ብዬ ልጄን አሳበድኩት?" አሉ በመቆጨት ራሳቸውን እየነቀነቁ።

"እኔ" እብደት ጀመረው። አጋፋሪ በእብደት አዳራሽ ኣስተናገዱት ፤ የእብደት ድግስ ኣበሉት አጠጡት። እናት ይህን እያየች እርር ድብን። አንድ ቀን አጋፋሪ ደጀኔ አብሾ ኣጠጡት። ጤና ይስጥልኝ ኣለ በጅልነቱ ላይ እብደት ጨመረ። እናት ይህን እያየች ተከትላው ማበድ። እብደት አጋፋሪ ላይም መጋባት።

"እኔ ደጀኔ" ይሉና ፤ ልጃቸው "ኣቤት" ሲላቸው ፤

"ማን ጠራህ?" ይሉታል።

እናቲቱ "ኧረ ይተዉት ይህን ልጅ" ሲሉ፤

"በገዛ ልጄ ምን አገባሽ?" ሲሉዋቸው

"እንዲህ አርጎም የለ!" ይሏቸዋል።

**1967**

# እትዬ አልታዬ

እንዳጋጣሚ ቀኑ የተሟላ ዕለት ጊዜና ገንዘብ እኩል የፈቀዱ ዕስት ፥ ብርሃኑና ጥላዬ ከወደ ውህው ለማለት፡ እና ተዝናንተወም ለማውጋት ለመጫወት ፤ ተያይዘው ወደ እትዬ አልታዬ ቤት።

እትዬ አልታዬ ቤት የኩላሊት ሰፈር መገናኛ መደሰቻ ነው። ትሰሜ እቺ በክራር የምትዘፍነው "እንጦጦ ላይ ሆኖ ይታያል ኩላሊት ፤ የትያልታዬ ቤት የሁከት መድህኒት" ያለችውም ሳቅና ጨዋታ ስለሚበዛበትና ሰው ውስጣዊውን ሁከትና ብቸኝነት ለመሸሽ ስለሚጎበኘው ነው።

የትዬ አልታዬ የቀኝ ጐረቤት "ዕድሜ ቀጥል ጣፋጭ ክትፎ ቤት" የሚል በቢክ እስክሪብቶ የተጣፈባት ካርቶን ወረቀት።

የትዬ አልታዬ የግራ ጐረቤት “ልዩ ልዩ በያይነቱ ጠቅላላ የሬሳ ሳጥን መሸጫ መደብር ቤት አስተያየት እናደርጋለን” የሚል በቀይ የተጻፈበት ቆርቆሮ ከበሩ በላይ ተሰቅሎ ፤ አንድ ጥቁር የሬሳ ሳጥን ግድግዳውን ተደግፎ ዘብ ቆሞአል።

ብርሀኑ በግማሽ ስካር፡ “እዚች ክትፎ በልተን ፡ ዕድሜያችንን አሳጥረን ወደዚያ መደብር ገብተን የሬሳ ሳጥናችንን መርጠን አዘን ፣ ካረቄ የተረፈውን ገንዘብ ቀብድ አስይዘን ስናበቃ ወደቤታችን” አለ።

ጥላዬ “ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት” እንዲሉ አባቶች” አለ።

“ምጣድ አይቶ ጠሃይ ፡ እንጐቻ አይቶ ጨረቃ እንዲሉ እናቶች”

“አይ የስካር ሞቅታ ፤ የጠላ ጠብታ እንዲሉ ፈረንጆች”

ሁለቱ ጐረምሶች በዚህ እየሳቁ እትዬ አልታዬቤት ጥልቅ። እትዬ አልታዬ ፈገግ ብለው ጥርሳቸወን ብቅ።

እትዬ አልታዬ የእትየነቱን ዘመን የትና የት ጥለውት ሄደው ፥ የእማማነቱንም ዘመን እንደ ወደ ማለፉ ብለው ፡ ሊያከትሙ ሲኒያቸውን ሊደፉ አንድ ሓሙስ ቀርቷቸው ፤ እንዲሁ በዘልማዱ እትዬ እየተባሉ ፤ ወርቅ ጥርሳችወን ብልጭ ድርግ እያደረጉ ፤ ጠላ እየጠመቁ አረቄ እየሸጡ፡ ገንዘብና ጊዜ. እየቆጠሩ........ ምናባትዋንስ ይቺ ኑሮ ፣ ሞት ይህ ከፉ ተንኮለኛ ድመት፤ አይጥ ሆነ ቢጠሩት ቢጠሩት አይል አቤት...... እትዬ አልታዬ ሞትን “ውርርርርር” እስኪሉትና “ሚያው” እስኪላቸው እኛ ስለወርቅ ጥርሳቸውና እንዲሁም ስለፈገግታቸው እንናገርላቸው እግረ መንገዳችንን ሌሎችንም እናነሳ እናወሳ ይሆናል።

እትዬ አልታዬ ፈገግ ሲሉ ሲታዩ ፡ ጊዜ በስውር እጅ ይዞ በጭካኔ ሳይሆን እየሳቀ በዝግታ እንደወረቀት ጭርምትምት ያደረጋቸው ይመስላል። ፊታቸው የሚስቅ መዳፍ ይመስላል። (መዳፍ እንደማይስቅማ

የታወቅ ነው። ግን አንድ ቀን ሳት ብሎት ቢስቅስ?) ታዲያ የትዬ አልታዬ ፈገግታቸው ሲታይ ልብ ይሰውራል።

በተለይም ከብርሀኑና ከጥላዬ ጋር ሲቃለዱ የሚታየው ፈገግታቸው የሺ ኣመት ደግነትና ፍቅር የተከማቸበት ይመስላል።

እንግድያማ ብርሀኑና ጥላዬ ወይ አንዳቸው ወይ ሁለታቸው ልጆቻቸው ናቸውን? ቢባል ፡ “ሊሆንም ይችላል ላይሆንም ይችላል” ይሏል ባዲሳባ አነጋገር።

ሁለቱ ገብተው እንደተቀመጡ እትዬ አልታዬ በገዛ እጃቸው እናትና ልጅ ቀዱላቸውና ጠርሙሱን ይዘው ቆመው ያዩዋቸው ጀመር። እናት ለልጆችዋ አንድ አንድ መለኪያ ደስታ ለከታ የምታጠጣቸው ይመስላሉ። ብርሃኑ እንደመነሳት ብሎ እጅ ነስቶ በሁለት እጅ ተቀብሎ ሲያበቃ የመለኪያዋን ከንፈር በፍቅር የሚስም ይመስል በዝግታ በጥቂቱ ሳበ ፡ አይኑን ጨፍኖ ሲከተላት አረቄዋ አፉን ሙቀት ሞላች ፤ በጉሮሮው ዘመተች ፥ ወደ ቆላ ወረደች።

“እሰይ! እዚህ ደረሰች” አለ ሆዱን በመዳፉ እያሻሸ። ቀና ብሎ አያቸው ሳቅ ሳቅ በሚለው ፊቱ።

“ሙቀት! ሙቀት! ሙቀት!” አሉት እትዬ አልታዬ። ወርቅ ጥርሳቸው ያረቄውን ነበልባል መልሶ የሚወረወር ይመስል አንጸባረቀ።

“ያረቄና ያንቱ ፍቅር ሙቀት!” አላቸው። ሁለቱ ሁሌ እንደተቃለዱ።

“አይ አንተ! የዛሬ ሰላሳ ዓመት ተገኝተህ በሆነ” አሉት።

“ያኔማ አይመችም ነበር። የለሁም ነበር” አላቸው።

“እሱ ላይ ነው ጉዱ ይኸውልህ። እኔ ደሞ አሁን የለሁም።” ፈገግታቸው ከፊታቸው ላይ መሸ። ወርቅ ጥርሳቸው እንደ ማታ ጸሐይ ተደበቀ። እርጅናቸው ሲጨልምባቸው ታየ።

ጐረምሳው ብድግ ብሎ በትከሻቸዉ እያቀፈ ካንገት በላይ እየቀለደ "ሰማህ ልጅ ጥሳዬ ፡ እትዬ አልታዬ እዚህ የሉም። ፖሊስ የጠየቀህ እንደሆነ እትዬ አልታዬን አላየንም በል!

አግድም ወንበር ላይ አጠገቡ እያስቀመጣቸው ፡ መለኪያውን አንስቶ ፉት እያስደረጋቸው ፡ "መለኪያዬን ከማጋራት በላይ ምን የፍቅር ምልክት አለ?" አላቸው።

እትዬ አልታዬ ሊናገሩ ሲሉ ባለሬሳ ሳጥኑ የግራ ጐረቤታቸው ከተፍ። ሰካራም። ትልልቅ ዓይኖቹ በስካር ልማድ ቀይ ሆነው ቀርተዋል። ስሙ ገላጋይ ተስፋዬ ሲሆን የኩላሊት ሰፈር ሰዎች ገላጋይ በርበሬ ይሉታል። "ና ዚህ ገላጋይ" አሉት እትዬ አልታዬ "ኧረ ስምህን ለውጥ። የሬሳ ሳጥን እየሸጥክ ገላጋይ መባል ደሞ ምን ፈሊጥ ነው? እኛ መገላገል ፈልገናል አልንህንዴ። ኧረዲያ"

አዛለች መዝዋዜ እንደዘንባባ እየተወዛወዘች ሄዳ እየተወዛወዘች ተመልሳ ሳትወዛወዝ አረቄውን ስትሰጠው በፈዛዛ በርበሬዎቹ ሲከተላት ቆይቶ በስማብ ለማለት እንኳ ያህል ጊዜ ሳይወስድ ዥው አድርጎ ወዳፉ ወረወራት አረቄዋን። ጉሮሮውን አቃጥላ ስትወርድ አይኑን ጨፈነ። ፊቱን አኮማተረ።

"ቀስ ብለህ ጠጣ ትሰክራለህ። ሬሳ መሰለው?" አሉት እትዬ አልታዬ።

አዛለች ሁለተኛውን ስትቀዳለት ፡ ጥላዬ "ታዲያስ ገበያ እንዴት ነው?" ኣለው ገላጋይን።

"ይህን ሰሞንማ ስምንተኛው ሺ መድረሱ ነው መሰለኝ ሰዉ መሞት እየተወ ሄዷል

"ምናባህ ታየኛለህ?" አሉት እትዬ አልታዬ ፡ "እኔ እንደሆንኩ አልሞትልህ። ደሞ ብሞትም በሳጥን አልቀበር። እኔ አልታዬ ወርቅ አፈር

ፈርቼ ነው ወይስ ተጠይፌ ነው ሳጥን ውስጥ እምታፈን? አልታዬ ማን እንደሆነች ባታውቅ ነው ልጄ። ሰሌኔን ለብሼ ነው ምተኛው ልንገርህ"

"እኔማ ሰሌንም መሸጥ ልጀምር ወይ እያልኩ ኣስባለሁ።" ከት ብለው ሳቁ እትዬ አልታዬ ፤ ወርቅ ጥርሳቸው ቦግ ብሎ ታየ። እንግዲህስ ያ ወርቅ ጥርሳቸው ሊያሸንፉቸው ምንም አልቀረው። ድሮ ድሮ የበሰሉ የሞሉ ጋለሞታ ሳሉ ነበር ይህን ወርቅ ከጥርሳቸው መሃል ያስተከሉ። እንዲያጌጣቸው ነበር ሐሳባቸውማ። አሁን ግን ይበልጣቸው ይከልላቸው ጀመረ። ከውበታቸው ቀድሞ ጐልቶ እየታየ። ምናባቱንስና ፤ ይህን ወርቅ አውጥተው ወዲያ ቢጥሉት። ከጣሉትማ ተረታሁ ተሸነፍኩ ማለት ይሆንባቸዋል። አላወልቅውም ይሁን ፤ እኔ አልታዬ ነኝ በወርቅ ምሸነፍ?

አልታዬ ሳሉም በወርቅ አልተሸነፉ በፍቅር ነው እንጂ። እትዬ አልታዬ ሳሉም ለወርቅ ብለው ኣልተወሰዱ ለአምሮታቸው ብለው ነው እንጂ። እና አሁን ካረጁ በኋላ ለወርቅ ሲሸነፉለት? ለዚህ ለብጫ ድንጋይ? ባይሆን ለዚህ ለወጣት ይሸነፉለታል እንጂ። ውስጡን ሳቅ አሉ። ቢወልዱ ኖሮ እንደሱ ያለ ሳቅ ሳቅ የሚ ለውን ነበር የሚወልዱ። ትዝ አላቸው ቅድም ገላጋይ ሳይመጣ አዝኖላቸው ተነስቶ ሲያቅፉቸው።

ወደሱ ዘወር እያሉ ያስለመዱትን ቀልድ እየጀመሩ።

"ብርሽ ብሪቲሽ!" አሉት።

"የስ ላብ" አላቸው።

"ይኸ ገላጋይ ሰው እንዳይመስልህ"

"ምን አረግኩ?" ኣለ በርበሬው ፡ አዛለች እየተወዘወዘች ስትሄድ በበርበሬዎቹ እየተከተለ።

"ምን አረግኩ? አሁንስ የሌባ ዓይነ ደረቅ ሆንክብኝ። ኣላውቅብህ መሰለህ? በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች ደህና ለብሰው ሲያልፉ ስታይ በዓይንህ ስትከተላቸው ስትጐመጃቸው ኣላይህ መሰለህ?

“አንተ ሟርተኛ! ደሞ እንደሱ አትየኝ ብየሃለሁ ዋ!” የስካርም የጨዋታም ሲስቁ ብርሃኑ ፊት ላይ ፍርሃት ብቅ ሲል አይተው አዘኑለትና ወደሱ ዘወር ብለው በዚያ በርህሩህ ገጻቸው አይዞህ እያሉት ፥

“ብርሽ ብርዬ ብርጭቆ ብርሌ!” አሉት።

“ወይዬ አልታይዬ!” አላቸው ብቅ ብሎ የነበረው ፍርሃት ተመልሶ ሲሰጥም እየተሰማው።

“እርጅና ምን እንደሆነ ልንገርህ?”

“ምንድነው?”

“አይን መክፈት ነው። ያ በልጅነት ችኮላ ነፋስና በጉርምስና ፍላት ትኩሳት ይሰማን የነበረው ፍርሃት ስጋት ብስጭት ኀዘን ፤ ያ ሁሉ ብድግ ፍርጥ ፤ ያ ሁሉ ተስፋ ያስቀርጥ አንጀት ይበላ ደም እንባ ያስለቅስ የነበረው ጭንቀት ለካስ ያልነበረ ኖሯል። ያ ሁሉ መረበሽ መሸበር ከንቱ ሁከት ኖሯል። ትንሽ ልጅ በጭለማ የሚሰማው የጅብ ጩኸት ኖሯል። ከንቱ ጋጋታ። ከንቱ!” አሉና መለኪያቸውን ብድግ አርገው ግልብጥ አደረጉት።

**1967**

# ተከታትለው ሸው ወደ ብሾፍቱ

ማንም ሳይሰማቸው በውስጥ ልባቸው ሁልጊዜ የሚዘፍኑ የእውነት ሴት ወይዘሮ ያልሆኑ፤የኮሩ የተንቀባረሩ፥ አፍንጫ ጐራዳ ፥ አንገተ ቆራጣ ሴት ወይ ዘሮ ቸርችል ጐዳና ቁልቁለት ላይ ቆመው አቀበቱን በናፍቆት አይን እየቃኙ ፥

“ትመጣለህ ቢሉኝ ከጋራው በላይ
አንገቴ ረዘመ ማዶ ማዶ ሳይ”

እያሉ እየዘፈኑ ቆዩና፥ ሰይቼንቶ ሲመጣ በእጃቸው ምልክት ሳይሆን አቆሙትና ፡

"ፖፖላሬ" አሉት እየገላመጡት።

"በዚህ ዕድሜዎ?!" አላቸው ጮሌው ባለታክሲ ውስጡን እየሳቀ።

በደንብ ሳይሰሙት "ትሄዳለህ ወይስ አትሄድም?? እዚህ መንገድ አላፊ አግዳሚው ሊያየኝ አልወጣሁም ይቅርታህን" አሉት።

"ይግቡ እሜቴ"

አስነሳ ባለታክሲው በዜሮ ፈጨው ቁልቁለቱን እግረኛ እያስበረገገ ባለመኪና እያስፈራራ ፥ በሀሳቡ ሲጫወት ፈረሱን በሌሎች ፈረሶች መሀል እያሾላለከ ሁሉንም እየቀደመ። ትልቁ ከቡ ንግድ ባንክ ሲደርሱ "ያስር ብር መልስ አለህ?" አሉት ወይዘሮዋ።

"አይጠፋም"

"የሚጠፋውኮ ቢኖር ነው። ሳይኖር ሊጠፋ ይችላል?" አሉት ኮስተር ብለው።

"አለ ማለቴ ነው እሜቴ"

ካለ ታዲያ አለ ማለት"

ትንሽ ሄደው ባለታክሲው አንድ ሁለት ጥሩንባ ተነፍቶበት ፤ ሶስት አራት ግልምጫ ተወርውሮበት ፤ አምስት ስድስት ስሞታ ተሰንዝሮበት ፤ እሱ ቀኙን የእግረኛ መንገድ በአዳኝ አይን እያሰሰ ለቀቀው ቤንዚኑን ፈጨው መንግዱን። ሠንጋ ተራን እልፍ እንዳሉ፤

"እዚያጋ ነው ይኸውልዎት ሴትየዋ የተዋረዱት" አለ።

"ውርደት? ምን ዓይነት ውርደት? ማን ላይ የወረደ ውርደት ነው እሱ ወዳጄ? እናንተ ሸሸንቶችኮ አታዩት አትሰሙት የለም።

“ይኸውልዎት የቀበጡ ሴት ወይዘሮ ከታክሲው ወረዱና ታክሲው አገር ጤና ብሎ ዕቃቸውን አውርዶ ትቶላቸው ሲሄድ ፤ እንዲያው እንደ ፌንጣ ቅልል ሲሉ ያን የመሰሉ ወይዘሮ ጮሁ። እንደ እብድ ከተማውን ሰነጠቁት። ምንም ሳይሆኑ “ኮ ነው።

“አንት ባለጌ! አንት ውሻ! ይድፋህ እንደ ድስት ክዳን! ያን ፍሬንህን የሚበጥስ ይላክብህ ሊቀመላኩ!” እያሉ ሲጮኹ ፤ ጨዋታ ፈላጊው ከበባቸው። ታዛቢው ራሱን እየነቀነቀ አለፈ። ሴት ወይዘሮ ኮ ናቸው ፤ ምን ልበልዎት ፀሐይ የመሰሉ እንደርሶ ክብር ያላቸው።”

“በቃ እዚህ አሉ እሜቴ በድንገት።

በኃይል ፍሬን ረገጠ። የሜቴ ጉትቻ ረገፈ። ከኋላ የነበረው ባለማርቼዲስ ፈረንጅ መኪናውን ፂፅ አርጎ አስጮኸ። ወደ መሀል መንገድ ዘውሮ በሌባ ጣቱ ራሱን እየወጋ አይኑን ቁልጭ ኣረገበትና አለፈው ታክሲውን።

“አይ ፈረንጅ! ጣት በአንጐል ክራባት በአንገት ኣሉ እሜቴ ጉትቻቸውን መልሰው እያንጠለጠሉ ፤” “ፈረንጅ ይግደለኝ”

እሜቴ ወርደው ጥቁር ቦርሳቸውን ከፍተው ቀይ አሥር ብር ኣውጥተው ሰጡት። ሰውየው ጥፍራም እጁን ሰዶ ሥጋ እንደሚያነሳ ጭልፊት አሥር ብሯን ሞጭለፍ አረገና ለቀቀው ፍሬኑን ረገጠው ቤንዚኑን ፡ ታክሲዋ እንደተቆጣ በሬ መንገዱን ቧጨር ፋቅ አረጋው አቡዋራውን እሜቴ ኣጠገብ በትናው ጉማዬ ኣውጪኝ አለች ፣ ተጨለጠች።

እሜቴ ሊጮሁ አፋቸውን ከፈቱና ፥ ባለታክሲው የነገራቸው ታሪክ በሀሳባቸው ድቅን ሲልባቸው ጊዜ አላፊ አግዳሚው እንዳይከባቸው በሳቅና በመሳለቁ ክብራቸውን እንዳይገፋቸው ፈርተው ተዉት መጮሁን። አፋቸውን መክፈታቸውን ስላላወቁ መዝጋቱንም አላሰቡትም።

ልክ የቅድሙ ታክሲ የለቀቃትን ቦታ ሌላ ታክሲ ሲጢጢጥ ብሎ ሌላ አቧራ አስነስቶ ቆመባት።

በሩ ተከፈተ።

“ይግቡ እሜቴ ፤ አሳድጄ እደርስበታለሁ። ይህን ወንበዴ እኔ ምስክር ሆኜ ይከሱትና ይታሰራል። ይግቡ! ይግቡ! ቶሎ ሳያመልጠን” አላቸው አንዱ ቀጫጫ ቁጡ ባለቀይ ዓይን ባለ ብዙ ጥርስ።

በልባቸው “በህልሜ ይመጣል ዓይንና ጥርስህ” እያሉ እየዘፈኑ ግን አፋቸውን ሳይዘጉ ገቡ።

ታክሲዋ አይጥ ያየ ድመት ይመስል ዘለለች ፤ተፈተለከች። ሴትዮዋ የቅድሙን ዘፈን በልባቸው ሲቀጥሉ፤

“ትመጣለህ ቢሉኝ ለበጋ ለሠርግ ፡

ነጠላ ፍለጋ አልኩኝ ከፍ ብድግ” አሉ።

“እንዲህ ዓይነት ሌቦች ናቸው ስማችንን የሚያጠፉን” አላቸው አዲሱ ባለሰይቼንቶ። “እንጀራችንን ሊዘጉብን ‘ኮ ነው እሜትዬ ዚሀር ያሳይዎት። እናስገርፈዋለን ፤ እናስጠፍረዋለን ፤ ምናለ በሉኝ። ሁለት ዓመት ፅኑ እሥራት ባላስፈርድበት እኔ አይደለሁም። ባላስገርፈው ባላስላጨው እኔ ዳኛቸው ቁጭ ብዬ እሸናለሁ ያያሉ።

“እረ ማየቱስ በቀረብኝ። ብቻ ቀይዋን ነጠቀኝ እንጂ”

“እሱ ሲያማታ ነው ሚውለው። እርስዎን ብቻ መሰለዎት? ታክሲዋንም ከሰው ሞጭልፎ ኮ ነው እንጂ እሱ እንኳን ሰው ሆኖ ታክሲ ሊነዳ የመንጃ ፈቃድ የለውም።

ከው አሉ እሜቴ። እረ የቁልቢ ያለህ ምን ታሰማኛለህ። እንዳበደ ፍቅር ቁልቁል ይዟቸው የተወረወረው ለካ መንዳት የማይችል ዱርዬ ኖሯል?

ሁለቱ ታክሲዎች ተከታትለው ሲበሩ ያየ ትራፊክ ዘወትር ዝግጁ የሆነችውን ቀኑብሽ የተባለች አይናማ ዱቅዱቄውን ዘሎ ወጣባትና ፤ “ዱቅ! ዱቅ! የኔ ዱቅዱቄ! ድረሺበት ጥፋት አለበት” ብሎ ጉንዋን አንዴ ሲረግጣት ጊዜ እንጣጥ አለችና እንደ መትረየስ እየተንጣጣች

“ዱቄት-ዱቄት- ዱቄት»” እያለች ፈጨችው መንገዱን ተከተለቻቸው የተከታተሉትን ታክሲዎች። ሦስቱም ተከታትለው ጨርቆስን አልፈው ቢሾፍቱ መንገድ ሲደርሱ ወደቀኝ ታጠፉና ማርቼዲስዋን አለፉዋት።

ረዣዥም ጉትቻ አንጠልጥላ ትነዳ የነበረችውን ሽንቅጥ ዘናጭ ወጣት እጉንዋ ተቀምጦ ሲጃራ ያጤስ የነበረው ጐፈሬ ጐረምሳ ወንድምዋ ፡

“እቺን ይወዳል ተከተያቸውና ጉዱን እንይ እንጂ” አላት

“ዳዲና ማሚና አንቲ ላቲ ይጠብቁናላ”

“እንደርሳለን። ካልደረስንም አይስ ቲ እንጠጣለን። ፍጪው ቤቢያ” አላት።

ቤንዚኑን በውብ እግሮችዋ ረገጥ ስታረገው ማርቼዲስዋ እንደ ውሀ ፈሰሰች። ሴት ወይዘሮዋም በማርቼዲስ ያለውን ወጣት አይተው በልባቸው ዘፈኑን ቀጠሉ፤

“እፍረትና ድፍረት ውስጤ ተናነቁ”

ታክሲው ታክሲውን ተከትሎ

ዱቅዱቄ እነሱን ተከትላ

ማርቼዲስ ዱቅዱቄን ተከትላ

ተከታትለው የቢሾፍቱን መንገድ ሲፈጩት ፡ የትላንትናው ፓርቲ ላይ ውቢቱን ባለማርቼዲስ ፍለርት ሲያረጋት አምሽቶ የነበረ ጠብዚራ ፈረንጅ ጢስ መውጫዋ ተጎርዶ የሄደ አንዲት ፊያት ውስጥ ሆኖ ቢያያቸው። ፡

“ማማሚያ ሳንታማሪያ!” አለና ሰፊ ቀበቶ በታጠቀ እጁ ማርሹን ቀየር ፣ በባለ ታኮ ቦቱ ቤንዚንዋን ረገጥ ረገጥ ሲያረጋት ጊዜ እንደራበው አንበሳ ሀኝ! ሀኝ! እያለች ሰማዩን በጩኸትዋ እያናከች ማርቼዲስዋን አሳደደች።

ደራሲው ቁንጥ እየበላ ማስቲካ እያኘከ ሲጃራ እየጠጣ ከቡና ቤቱ ፊት ለፊት “መጨረሻ” የሚል የትራፊክ ምልክት ኣጠገብ ቆሞ ጫማውን እያስጠረገ ሲያይ ሰይቸንቶዋ ቀድማቸው ደረሰች። ሁለተኛ ታክሲዋ ፤ ሶስተኛ ዱቅዱቄ፤ አራተኛ ማርቼዲስ ፤ አምስተኛ ፊያት ፤ ስድስተኛ ነጠላ የለበሱ ሴትዮ ፤ ሰባተኛ ኳስ ይዞ ለብቻው የሚነጋገር ልጅ።

ደራሲውም ለቀዳሚዎቹስ ምን ሽልማት ልስጥ። በቴሌቪዥንስ ምን ዲስኩር ልናገር? እያለ ሲያስብ ሲያሰላስል፡ ለካስ እነሱ ደራሲው ዳኛ መሆኑን ሳያስቡ “መጨረሻ” ማለት መድረሻ ማለት መሆኑንም ሳይገነዘቡ፥ አልፈውት ሄዱ። እሽቅድምድማቸውን ቀጠሉ ፈጩት መንገዱን በሽክርክር ጐማ።

ከወዲህ ማዶ አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ ልትል ስትል ፥ ከወዲያ ማዶ አንዱ ኣንዱን ሲያሳድድጐማ እልቅ ልትል ስትል ጠምዝዝ ገልመጥ ሲሉ “ጐማ እንሰራለን” አላቸው የቢሾፍቱ ጐሚስታ የማቾኒ ጌታ

አልፈውት ሄዱ እንደተከታተሉ ፡ ወይዘሮዋ በልባቸው ዘፈናቸውን እየዘፈኑ ፥

“ቢሾፍቱ ይደርሳል ፍቅር ፈላጊማ ፡

በሶስት ሊትር ቤንዚን በሽክርክር ጐማ።”

(ጥር ፤ 1966)

# ለጉድጓድ

በግንቦት ልደታ ጠላ ሰዓት እንስራ ሙሉ ተረት አለኝ። እስቲ አንዳንድ ዋንጫ ልበላችሁ።

እትያልታዬ ቤት ጠላ እየተጠጣ ቆሎ እየተቆረጠመ የሞቀ ወግ ተይዟል። በመሀሉ ወይዘሮ ላቀች እንደ ልማዳቸው መርዶ ተናገሩ። ማንም ሰው የትም ቢሞት ወይዘሮ ላቀች ወሬውን መበተን ይወዳሉ።

“እትያልታይዬ ረስቼ ሳልነግርሁ። እዚህ ከኛ ሰፈር እልፍ ሲሉ እሪ በከንቱ እንደደረሱ ሶስት ጠላ ቤቶች የሉም? የኮሬንቲ እንጨት አጠገብ እንኳ ትንሽ ሱቅ አለች። እዚያ ያለችው ፋናዬ ሚሉዋት የለችም? አራስ ልጅዋ ሞተችባት አሉ ልጄ። እምጵፅ!”

“እምጵፅ! እኔን ይድፋኝ!” አለች ዘነበች።

“ምን ሆነች? ታፈነችባት?”

“ኸረ በሽታ ነው አሉ”

ሞት የወይዘሮ ላቀችን ጥሪ ሰምቶ ላንዳፍታ እትያልታዬ ቤት ገብቶ ህጉን ገድሎ ቁጭ አለ። ሁሉም ዝም ዝም አሉ። ወደየሀሳባቸው ሸሹ።

ቆይቶ ቆይቶ ፤

“እሪ በከንቱ ብትይ ጊዜ አስታወስሽኝ” አሉ አቶ ለውጤ እኚህ ድሮ አስተማሪ የነበሩ። እዚያ የነበሩ ሁሉ የቅድሙን ሞት ለመርሳት ስለፈለጉ ዓይንና ጆሮዋቸውን ወደ አቶ ለውጤ አዞሩ። አቶ ለውጤ የሚከተለውን ተናገሩ።

ከሰዓት በኋላ ነው ፥ ይሞቃል ይወብቃል። አንድ ሰውዬ ሰዎች እየተጫወቱ የሚጠጡበትን ጠላ ቤት ትቶ ለጥቆ ካለው ባለጠላዋ ብቻዋን ፍዝዝ ብላ ከተቀመጠችበት ቤት ገባ። ሴትዮዋ ተነሳችና ምን ፈልጎ

እንደመጣ ያላወቀች ይመስል ስታየው ከቆየች በኋላ ጠላ በጣሳ አምጥታ በብርጭቆ ቀድታ ፊቱ አስቀመጠች። ጐረቤቶቹ ንግግራቸው ሳይሆን ድምፃቸው ይሰማል።

ሰውየው ጠላውን አንዴ ተጐንጭቶ አፉን እያጣጣመ ብርጭቆውን ሲያስቀምጥ ፤

“ዛሬ ምን ነካህ ሰውየው! እምቢ ስል ግድ አለብኝ እንዴ?” አለች ሴትዮዋ በቁምዋ። በንዴት ይመስላል ግን ድምፅዋ ከሹክሹክታ ምንም ያህል ከፍ አይልም። ሰውየው ቀና አለ። ማንም ሌላ ሰው የለም በቤቱ።

ሴትዮዋ “እምቢ በቃ እምቢ! ወይ አንቺ አዲሳባ ፥ ኣታሰሚው የለሽ! በሉ ጠላሁን ጠጡና ውጡልኝ” አለች ሰውየውን በንዴት እያየችው። ተቆጥታለች ግን ኣትጮህም። የውጭ ሰው ሊሰማት አይችልም። ሰውየው ግራ ገባው ፍርሃትም ያዘው። እብድ ትሆን እቺ ሴት?

ሴትዮዋ በኩራት እጅዋን ወገብዋ ላይ አርጋ ቆማ በሌላው እጅዋ በንዴት ወደ መውጫያው በር እያመለከተች “እሺ ይቅር ኣትክፈሉ” አለች “ብቻ ውጡልኝ።”

“እኔን ነው?” አላት ሰውየው እየተደናገጠ። (“እቺ ሴት ትያትር ሠራተኛ ትሆን?” የሚል ሃሳብ ገባው)

“ሆ! ምንስ ቸግሮኝ ጠላ ብሸጥ ነብሴን ሸጥኩ “ንዴ ‘ንድህ ዓይነት እርኩስ ነገር ምሰራው? ለምን ሺ ብር አይኖርህም። ጐረቤት ጠይቅ ይነግሩሀል። በላይነሽ እናቶቿ ማይሰሩትን ትሠራለች ሚልህ ኣታገኝም። ሆ! ምን ፈረደብኝ እናንተ!”

ሰውየው ገርሞት ሲያያት ንዴቷን ከፊትዋ አራግፋ ትክ ብላ በደረቅ አይን እያየችው ዝግ ባለ ድምፅ እንዲህ አለችው ፥

“አሁኑኑ ሃያ ብር ከኪስሁ አውጥተው ካልሰጡኝ አሁን ቀስ ብዬ የተናገርኩትን ሁሉ ጮክ ብዬ ሰው እንዲሰማ አድርጌ እናገረዋለሁ።”

“የማነሽ ደፋር! ማን መሰልኩሽ አንቺ?” አላት የውሸት ድፍረት ድምፁ ውስጥ እያሰማ።

“እኔ አላውቅሁም። ደሞ ማንም ብትሆኑ ግድ የለኝ። ሃያ ብሯን ቁጭ!”

የሚያረገውን በማጣት ሳቅ እያለ የጠላ ብርጭቆውን ሊያነሣ እጁን ሲሰድ “ምነው ሰውየው! አብደኋል?” አለች ጮክ ብላ። ዝግ ባለ ድምጿ ደሞ “ሃያ ብሯን አሁኑኑ ካላወጡ ጮኬ እቀጥላለሁ።”

ክው አለ ሰውየው። ገንዘቡ ሳይሆን ነገሩ አስደነገጠው። የገንዘብ ቦርሳውን ከደረት ኪሱ እያወጣ ፡

“አሁን ውሰጂው። በኋላ ፖሊስ ይዤ እመጣና እንነጋገርበታለን” አላት።

“እንኳን ፖሊስ ሽጉጥ ይዘሁ ኑ። ኧረ ገመድ አምጡ። ያውም ሞት ተገኝቶ ነው?

እቺ ነገር ኣታዋጣም ብሎ ሃያ ብሩን ሰጣት። ተነስቶ ሊወጣ በሩጋ ሲደርስ “አይ አይ አይ!” ብላ ስታለቅስ ሰማት። ሊመለስ ኣለና ቀፈፈው። መንገዱን ቀጠለ።

ሴትየዋ በረዥሙ ካለቀሰች በኋላ ተነሣች። ነጠላዋን ተከናነበች። ወጣች። በሩን ቆለፈች። ሄደች። ብዙ መንገደ ሄዳ ኪዳነ ምህረት ቤተስኪያን ደረሰች።

ቤተስኪያኑ ደጀሰላም ስትደርስ ተደፍታ መሬቱን ተሳለመች። ተነሳች ገባች።

ቤተስኪያኑ ደረጃ ስትደርስ ተደፍታ ደረጃውን ተሳለመች። ተነሣች ደረጃውን ወጣች።

ቤተስኪያኑ በር ሥር ተደፍታ ተሳለመች። ተነሳች በሩን ተጠጋች።

ተንበርክካ በሩን ደጋግማ ደጋግማ ተሳለመች። እምዬ ማርያምን የሙጥኝ እንደምትል ሁሉ በሩን ተጠግታ ራሷን ደፋች። አይኗን ዘጋች። ብዙ ብዙ ብዙ ጊዜ ቆየች።

"ይቅር በይኝ ይቅር በይኝ ይቅር በይኝ" ብላ አይኗን ጭፍን አድርጋ እዚያው ቆየች።

ቤተስኪያኑን እየዞረች እያንዳንዱ በርጋ እንደዚሁ አዛኝቱን የሙጥኝ ካለች ይቅር በይኝ ካለች ከለመነች በኋላ ከቤተክርስትያኑ ራቅ ያለ መንገድ ሄዳ ካንድ ሬሳ ሳጥን መሸጫ ቦታ ስትደርስ ገብታ ለሰውዬው ሃያውን ብር እየሰጠችው "በዚህ የትንሽ ልጅ ሣጥን ይገኛል?" አለችው ፡ ብለው ታሪካቸውን ጨረሱ አቶ ለውጤ። ሞት ተመልሶ እትያልታዬ ቤት ገባ። ሰዉ ሁሉ ኣንገቱን ደፋ፤ ወደየሃሳቡ ሸሸ።

**(የካቲት ፤ 1966)**

# ዘር

የ8ኛ ክፍል ፈተና 3 ወር ሲቀረው ብርቄ ጧት ጧት ሊያቅለሸልሻት ጀመረ። ተማሪ ቤት ለመሄድ ስትተጣጠብ ስትበጣጠር እማዩ እንደሁልጊዜያቸው ከትላንት ጠላ ጠጪዎች የተረፈውን ቆሎ ለቁርስዋ ሲያቀርቡላት እንዳያስታውካትና እንዳያጋልጣት በመፍራት ሰዓት ደረሰብኝ ብላ ቆሎውን በቁራጭ ጋዜጣ ጠቅልላ ትወጣለች። መንገድ ላይ ልትቆረጥመው ከጀመረች በኋላ ሆድዋ ከፍ ዝቅ እያለባት ትተፋውና የተረፈውን ቆሎ ለጓደኞችዋ ለነአዜብ ትሰጣቸዋለች።

እማዬ ለሷ ብለው ቁርስ ሳይበሉ እንደሚውሉ ስለምታውቅ አንዳንዴ ይህ የቆሎ ነገር ይቆረቁራታል።

የቆሎው ሐሳብ ከደቀቀ በኋላ ያ ትልቁ አስፈሪው ሐሳብ እንቅ ያረጋታል። ውሎ አድሮ አንድ ቀን እማዬ ማርገዝዋን ሲያውቁ ምን ይሉ ይሆን? ይሉዋታል።

እሳቸው ጠላ እየጠመቁ ፥ ጥጥ እየፈተሉ ፥ ዶሮዎቻቸውን እየሸጡ ፥ ፍዳ አይተው አሳድገው ከስምንተኛ ክፍል ያደረሱዋት ለዚህ ኖሯል? ምን በደሉዋት? ከናት የበለጠ ሆነው ባሳደጉ ይኸ ይድረስባቸው? ምን ይሉ ድንገት ጉድ ወለል ብሎ ሲታያቸው? ምን ያረጉ ይሆን? በብስጭት ኣያብዱም? ዕድላቸውን አይረግሙም?

የዚህን ሐሳብ ሸክም ለብቻዋ መሸከም ስላልቻለች ለዳምጠው ነገረችው። ወይ ያገባኛል ወይ እሱ በመሰለው መንገድ ያግዘኛል መስሏት ነበር። አጅሬ ታዲያ ሲጃራውን እያቀጣጠለ ፡ “ከኔ ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለሽ?” አላት። የድሮ ቀልዱ ፊቱም ላይ አይታይም ፤ ድምፁም ውስጥ አይሰማ።

ብርቄ ግራገባት። “ማስረጃ ያስፈልገኛል?”

“አዎን”

“ይኸ አልጋህ አይመሰክርም?”

“ስንትና ስንት አልጋ አለ

“ስንትና ስንት ምስክር አለ” አላት።

ቃል ሳትናገር ተነስታ ልብስዋን ለብሳ ወጥታ ሄደች።

አሁን እግዚሐር ወይ መልክ ባይሰጣት ወይ ወንዶችን አታላዮች አርጐ ባይፈጥራቸው ምን ቸገረው ነበር?

አንድ ቀን ትምህርት አልቆ ልጆች ተበታትነው እስዋ ብቻዋን ክፍል ውስጥ ቀርታ አዜብ ውጭ ፈልጋ አጥታት ኖሮ ብትመለስ ስታለቅስ አገኘቻት።

ኣዜብ “ውይ ምን ሆንሽብኝ ብርቅዬ? እኔ ላልቅስልሽ። ምን ሆነሽ ነው?” ብላ አቀፈቻትና ፡ ብርቄ ሆድ ብሷት በረዥሙ ካለቀሰች በኋላ ችግርዋን ስትነግራት አዜብ ኣብራት አለቀሰች። በኋላ ቤትዋ ድረስ ሸኘቻትና “አይዞሽ እሱ ሚካኤል ያውቃል” አለቻት። ብርቄ ሐሳብዋ በመጠኑ ቀለል አለላት። ጓደኛ አታሳጣኝ እያለች ፡ በኀዘንዋ ጭለማ ውስጥ የደስታ ጭላንጭል እየታያት ቤትዋ ገባች።

በአዜብ ኣይዞሽ ባይነት ብርቄ እርግዝናዋን ለአንድ ወር ተኩል ያህል ቻለችው። በኋላ ግን እያሰበችበት ስትሄድ ባንድ በኩል የ8ኛ ክፍል ፈተና ደርሷል። ስለ እርግዝናዋ እየሰጋች ልታልፈው አትችልም። ባንድ በኩል እማዬ ጉድዋን ቢያውቁ አንጀታቸው ቁርጥ የሚል መሰላት። “ላስወርደው?” አለቻት አዜብን።

“አደገኛ ነው ይላሉ ይቅርብሽ” አለቻት

“ሌላ ምን ላርግ አዜብዬ? ለማዬ ያለኋት እኔ ብቻ ነኝ”

“ከፍሬ የበለጠ ፡ አንቺን ሰጥቶኛል እኅቴንም ቢወስድብኝ አንቺን ተክቶኛል። አላማርረውም” ሲሉዋት ትዝ አላትና በሐሳብዋ ተሸማቀቀች።

አንድ ቅዳሜ ጧት ተነስታ እንዶድ ጠጣች። እስዋ ተስፋ ያደረገችው ጣጣው ቅዳሜና እሑድ አልቆ ሰኞ ተማሪ ቤት እውላለሁ ብላ ነበር።

ቅዳሜ አሟት ዋለ። አዜብ አብራት ዋለች። እሑድ ባጣም ሲብስባት ጊዜ አዜብ ፈራችና እውነቱን ለእማዬ ነገረቻቸው።

የእማዬ ኮሳሳ ሰውነት ቀሚሳቸውን አንቀጠቀው። ብድግ ቁጭ ኣሉ ፤ ውጭ ወጡ። ተመልሰው ገቡ። ቀጫጭን እጆቻቸውን አስር ጊዜ አንቋቁ

ብርቄ አልጋ ላይ ተጋድማ በደከመ መልክ ወደላይ ዓይንዋን እያንከባለለች በፍርሃት ስታያቸው

“አንቺ ቆሻሻ ባለጌ!” አሉዋት። “ደግሞ ላንቺ ብዬ ማሽላ መቁላቴ እጣን ማጨሴ። ድብን ክንችር አትዪም ለኔ ብለሽ? አንቺ ጨካኝ አረመኔ!

እኔ ፍሬዬ ነሽ ስል የሰጠኝን ፍሬ ታጠፊብኝ? አንች ቡዳ!" አሉና ድንገት ጸጥ አሉ። እንባቸው እየወረደ ከሣጥናቸው ላይ ቁጭ አሉና ራሳቸውን እጃቸው ውስጥ ደፍተው ፤

"የኔ ብርቅዬ ፥ አንድ ዓይኔ ነሽ እንዳትጠፊብኝ። እንዳይጨልምብኝ። እናትሽ ስትሞትብኝ የሞትኩት ይበቃል። አትግደይኝ። ዳኚልኝ። ብርቅዬ ፥ ዳኚልኝ......." ሲሉ ፡ ብርቁ እጅዋን ሰዳ እጃቸውን ስትስብ አዜብ ቶሎ ትታቸው ወጥታ በሩን ዘጋችላቸው።

እዚያው ቆማ ብዙ ቆየች። አንድ ባለባርኔጣ ሰውዬ ሲያልፍ በር በሩን ሲያይ ጊዜ "ጠላ የለም" አለችው። መንገዱን ቀጠለ። ቆይቶ ቆይቶ በሩ ተከፈተ።

የብርቁ እናት "ግቢ እንጂ። ቡናው "ኮ ቀዘቀዘ" ኣሉዋት። ፊታቸው ላይ ኀዘን የሚሉዋት የለችም።

እማዬ ለክፉ ቀን አጠራቅመዋት የነበረውን ገንዘብ አውጥተው ብርቁን ሐኪም ቤት ወሰዱዋት። አንድ ቀን እንኳ ሳያቋርጡ አንዲት ሰዓት እንኳ ጊዜ ሳያጓድሉ እየተመላለሱ ሀያ አንድ ቀን ሙሉ አስታመሙዋት።

8ኛ ክፍል ፈተና መጣ፤አለፈ፤ ብርቁ አለፈችው። ግን ወደ ዘጠነኛ እንዳትቀጥል እስዋም አፈረች ፤ እማዬም እስከትገላገይ አርፈሽ ተቀመጪ አሉዋት። በዚሁ ቀረ። አዜብ ግን በበኩልዋ ትምህርትዋን ልትቀጥል ትፈልግ ነበር ፤ ፈተናውን ወደቀች። "ምነው በኔ ፈንታ አንቺን ባሳለፈሽ?" አለቻት ብርቁ። ክፋት" አለች ኣዜብ።

እማዬ የቤት ኪራይ ስለበዛባቸው አነስ ያለች ቤት ፈልገው ገቡ። አዲሱ ሰፈር ቆሸሽ ያለ ሆኖ ቤቶቹ ቦታ ጠቧቸው እርስ በርስ የሚጋፉ የሚጓሸሙ ይመስል አንዳንዶቹ ወደ አንድ በኩል ሌሎቹ ወደ ሌላ በኩል ተንጋደዋል። ሰፈሩ ደስ አይልም ፤ ግን ጠላው ደህና ይሸጥ ጀመር።

አንድ ቀን እማዬ ሲፈሩ ሲቸሩ ብርቄን ፣ “የልጅሽ አባት ማን ነው?” አሉዋት

“ልጄ አባት አይፈልግም” አለቻቸው።

በመጠየቃቸው ያፈሩ ይመስል ዝም አሉና ደጃፉ ጋ ይንጫጩ የነበሩትን ሶስት ጫጩቶች ትክ ብለው ያዩዋቸው ጀመር። እሷም ጫጩቶቹን ስታይ ቆይታ “አረገዝኩ ስለው ጊዜ “የኔ ልጅ መሆኑን እንዴት አውቃለሁ?” አለኝ። ይኸ ምላጭ ሌባ!” አለች።

“ግድ የለሽም” አሉ ለራሳቸው የሚናገሩ ይመስል።

“አሽከሞኝ ዘወር ሲል እንዴት ግድ የለሽም ትይኛለሽ?

ሳቅ እንደማለት ብለው “መጥፎ ሽከም መስሎሻል?!” አሉዋት።

“እንዴት አድርጌ ላሳድገው ነው?””

“እሱ ያለው ላይቀር እሱ ያላለው ላይሆን........ እኔ እንዴት አድርጌ ነው ያሳደግኩሽ?”

“ውይ እማዬ! ሁልጊዜ ልጅ ለምን ታረጊኛለሽ? ይህን ሁሉ ዘመን ምን ያህል ሸክም እንደሆንኩብሽ አላውቅ መስሎሻል? እይው እንዴት እንዳረጀሽ”

“እና ማርጀት ሊቀርልኝ ኖሯል? ድንቄም!”

“እኔን ማሳደግ ባይኖርብሽ አሁን በምቾት ትኖሪ አልነበረም?” አለቻቸው።

“እና አሁን ከማን ጋር ቁጭ ብዬ እጫወት ነበር?” አሉዋት። “ከሶፋው ወንበር ጋር ነው ወይስ ከናይለን ቀሚስ ጋር ነው ወይስ ወርቅ አንባርና ጉትቻ እያማታሁ እጫወት ነበር?”

ከባልሽ ጋር ትጫወቺ ነበር?

ከየት የመጣ ባል?

"እኔ ተማሪ ቤት ልገባ ሰሞን አቶ በየነ ልጅሽን ለዘመዶችሽ ስጪያቸውና ላግባሽ ብለውሽ እምቢ አላልሻቸውም?"

ደነገጡ። ዘወር ብለው አይን ፥ አይንዋን እያዩ ፥ በዚያውም ድንጋጤውን እየሸሸጉ ፤

"ማን ነው ይህን የዋሸሽ? ያቺ ቀላዋጭ ማናህሴናት?? መቼስ ስትዋሽ ለነገ አትል። መጥኔ!"

"አታጭበርብሪ ተይዘሻል!" አለቻቸው ሳቅ ብላ።

"ኧረ እኔ አላጭበረብርም! ካልሽስ እንግዲያው አንድ ሳይሆን ሶስት ባል ነው እምቢ ያልኩት። በይ ምን ትሆኚ?"

"ለምን እምቢ አልሽ?"

"ሳልፈልግስ ልጄ። በመንግሥት አገር ማን ያስገድደኛል?"

"ለምን አልፈለግሽም? በኔ ምክንያት ነው?"

"አንዱን ባንቺ ምክንያት ነው። ሌሎቹን በኔ ምክንያት ነው"

"እንዴት ባንቺ ምክንያት?"

በረዥሙ እየተነፈሱ "ምኑን አውቄው ብለሽ? እንዲያው ሆድ ይፍጀው ነው እንጂ፥" አሉዋት። ሊናገሩ እንዳልፈለጉ አወቀች። አጭር ዝምታ ሆነ።

ዓይናቸውን ወድያ ሩቅ ባዶ ቦታ ተክለው በሐሳባቸው ሲዋኙ፤ "እማዬ" ብላ በድምጿ ገመድጐትታ መለሰቻቸው።

"ወዬ ፤ ብርቅዬ ወርቅዬ" አሉዋት እየሳቁ ፡ ድሮ ልጅ ሆና እንደሚሉዋት።

"እኔ ስወለድ አንቺ የት ነበርሽ?"

ከተማ ነዋ ልጄ። እከተማ ከጠላና ከጐረምሳ ስዳራ ነው መወለድሽን የሰማሁ። አቤት እንዴት ደስ አለኝ! በልቤ እልል እያልኩ እየበረርኩ ሄጄ ኦቶቡሴን ተሳፍሬ ከቸች አልኩ።”

የትዝታው ሳቅ ከፊታቸው ጠፋና እንደገና ዓይናቸው ሐሳባቸውን አስከትሎ ሩቅ አገር ደረሰ።

“በምን የተነሳ ነበር ካገር ቤት ጠፍተሽ የሄድሽው?”

“ከጥጋብ የተነሳ ነዋ!”

ከዚያ ሐሳባቸው ካለበት ከሩቅ አገር ሆነው የሚናገሩ ይመስል፥ ለሷም ለራሳቸውም የሚያወሩ ይመስል ፥

“ባሌ ነጋዴ ነበር ፡ ይኸውልሽ ፡” አሉ “ወጥም አልሰራ ልብስም አላጥብ ፡ ሁሉ በገረድ ነው። እሱደሞ ይወደኛል ያከብረኛል። ያስጌጠኛል። እንዲህ አይምሰልሽ። ለንግዱ ከተማ በሄደ ቁጥር ወይ ሻሽ ወይ ቀሚስ ወይ ሽቶ ወይ ጌጥ ሳይዝልኝ ይመለሳል ማለት ዘበት ነው።

“አይ ያ ጊዜ! እውነት ነበረ ያ ጊዜ?!” ዝም ብለው ቆይተወ ቆይተው

“መሀን ናት ፍታት እያሉ ልቡን ያወልቁት የነበሩ እህቶቹ ከውጭ ወለደ ሲሉኝ ጊዜ ቀንቼ ተቃጥዬ ልሞት። ለካስ ከተማ ከተማ እሚያሰኘው ሽቀጡ ብቻ አልነበረም። ዕቃዬን ጠቀለልኩና አባቴ ቤት።....... ለምን ወለደ ብዬ አይደለም “ኮ። እሱማ ለኔ አልሰጠኝምና አንተም ይቅርብህ አልለውም። ያውም ፍሬን የመሰለ ጠጋ ፈጣሪ ሰጥቶት ነው እኔን እሚከፋኝ? እንዲያውም ከሌላ ወለድ ልበለው ይሆን? እያልኩ ብዙ ሳስብ ነበር። ምንስ ቢሆን ሰውን አትውለድ ይባላል?”

“እንግዲያው ምንድን ነው ያስቆጣሽ?”

“ደብቆኝ የሰው መሳለቂያ አረገኝ ብዬ ነዋ! ሞኝ አይደለሁ? እንጂ እሱማ ይወደኝ ነበር እግዜር ይስጠው። አማላጅ ሽማግሌ ላከብኝ። እናትሽን ሳይቀር ላከብኝ። የፈለገችውን እከሳለሁ አለ።”

“እና ምን አልሽው?”

“አፍንጫህን ላስ አልኩትና ከተማ ወጣሁ። የሰው ገረድ አልሆንም አልኩና ጠላ እጠምቅ ጀመር። ከልክ ያለፈ ቆንጆ ነበርኩ መቸስ። የጊዜው አለባበስ ሌላ ነበር እንጂ እንዳንቺ ነበርኩ።”

ሁለቱም ሳቁ።

“ታዲያ ያ ባሌ እግዜር ይስጠው ስንትና ስንት ዓመት አልፎ ስንትና ስንት ነገር ከደረሰብኝ በኋላ እንኳ ነይ ቤትሽ ተመለሺ እያለ ይልክብኝ ነበር

“ለምን አልተመለስሽም? መታረቁ አይሻልም ኖሯል?”

“ይሻል ነበር። እምቢ አልኩ”

“ለምን?”

“ጓደኛዬ ነበረች የወለደችለት። በሱ ተቀየምኩት። ስንትና ስንት ሴት ሞልቶ ተርፎ ከጓደኛዬ ወለደና አንጀቴን ቆረጠው። እንዲህ ነው እልሻለሁ።”

ሁለቱም ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ

“እማማ ከሞተች በኋላ ምን አንቺ ወሰድሽኝ?” አለቻቸው።

“እስዋ ናት ለኔ እንድትሆኚ የተናዘበች። ምን ያህል ልጅ እንደምመኝ የምታውቅ እሷ ነበረች። አጐቶችሽማ ሊወስዱብኝ ዶልተው ነበር። ሞቼ እገኛለሁ አልኩና በግድ ወሰድኩሽ እንጂ.... እንዲህ ነው ይኸውልሽ። አንቺንም እናትሽን ነጠቀሽና እኔን ሰጠሽ። እኔንም ልጅ ከለከለኝና አንቺን ሰጠኝ። አሁን ሳስበው እንኳንም አልወለድኩ። ሸክም ቀረንጂ ምን ቀረ?”

እውነታቸውን እንዳልሆነ ስለተሰማቸው ዓይኗን ሸሹት። እስዋም ስላወቀች ዓይናቸውን ሸሸች።

ወንድ ልጅ ወለደች። እማዬ ስሙን አሸናፊ አሉት። እንዶድን አሸነፈ ፥ ገና ድህነትን ያሸንፋል ምናለች በይኝ አሉዋት።

አራስ እንዳለች አባትዬው አማላጅ ላከና መጣ። አብረን እናሳድገው አለ።

"ልጅህ መሆኑን እንዴት ታውቃለህ?" አለችው

"አምንሻለሁ?" አላት

"እንግዲያው እመነኝ ያንተ አይደለም ፤ አባቱ ሌላ ነው። ስንትና ስንት ኣልጋ አለ መሰለህ?"

"እከስሻለሁ" አላት።

እምቢ አለችው። ለጊዜው ተስፋ ቆርጦ ሄደ። በኋላ እማዬ ሊመክሩዋት ሞከሩ። ሁለተኛ ስሙን እንዳታነሺብኝ ባሽናፊ ሞት ይገቡሻለሁ አለቻቸው።

ገረማቸው። እምቢ ከማይወጣት እኅታቸው ተወልዳ ልክ እንደሳቸው እልኸኛ እምቢተኛ ናት። ልጃቸው ናት። ሳቅ ብለው ፥

"ኧረ አሸናፊም አባት አያስፈልገውም! ለራሱ ወንድ ነው!" አሉዋት።

አቶ ዳምጤን ግን በምስጢር ከጥቂት ጊዜ በኋላ አባ ዘርአ ያዕቆብን አማላጅ ይዘህ ና ብለው ላኩበት።

**ኅዳር ፡ 1966**

# እናት

ያለፈው ቅዳሜ ማታ ካራት ኪሎ ፒያሳ ለመሄድ "ሰይቼንቶ" ተሳፈርኩ። ነጂው አጠገብ ያለውን በር ከፍቼ ገና በደንቡ ቁጭ ሳልል ፤

"ጋሼ ፥ ስሙኒ ክፈሉልኝ" አለችኝ።

በሩን ዘጋሁና ወደኋላዬ ተመለከትኩ። አንድ ቆብ ያደረገ ሰውና አንዲት የሀገር ልብስ የለበሰች ሴትዮ ቁጭ ብለዋል። እኔ በሩን ስዘጋ ፡ ነጂው መኪናዋን ሲያስነሳ እና ሴትዮዋ ስትናገር እኩል ስለነበረ ያልሰማኋት መሰሏት ደገመች ፤

"ጋሼ ስሙኒ ክፈሉልኝ።"

"እሺ" አልኳት።

"በል ይኸውልህ። ስሙኒህን እሳቸው ይከፍሉሀል።

ቀይ ነች። እንደ መስከር ብላለች። ወደ ወንበሯ ጫፍ ተንፏቀቀች። የኔ ወንበር መደገፊያ ላይ ክንዷን አስደገፈች እና ደከም ባለ ለስላሳ ድምፅ እንዲህ አለችኝ

"እስቲ እዩት ጋሼ ፡ ወዳጄ ኣመጣኝ። ጥቂት እንደሄድን ሌላው ወዳጄ ተሳፈረና እንዴት ዋልሽ አለኝ። የግዜር ሰላምታ ነው መቸም እኔም እንደት ዋልክ አልኩት። ይኸኔ ሁለቱም መፋጠጥ ጀመሩ። መውረጃችን ቦታ ስደርስ እኔ አልወርድም አልኩ። ከሚጣሉ ብዬ ነው። ይፈረድብኛል?"

"ሰውየውን ደሞ የራሱን ብቻ ከፈለና ከኔ ጋር ካልወረደች የሷን አልከፍልላትም ብሎ ሄደ ፡" አለ ሰይቸንቶ ነጂው።

ሴትየዋ ፡ ልክ ነጂውን እንዳልሰማችው ያህል ቀጠለችልኝ ፤

"አየህ ፡ ጋሼ ፡ ሁለቱም ወዳጆቼ ናቸው። ለምን ይጣሉ ብዬ አልወርድም ፡ አልኩ እንዲያውም አንደኛው ግልፍተኛ ነው።"

"እንግዲህ ሁላችሁ ለኔ ስሙኝ" አለ ነጂው። ከማርያም በታች ያለው ቀይ መብራት አቁሞናል።

ባለቆቡ ሰካራም ልክ ነጂውን እንዳልሰማው ያህል ወሬውን ቀጠለ ፤

“ወዳጇ ከሆነች ፤ የምወዳት የምመኛት ወዳጇ ከሆነች ፤ ሰይቸንቶ ውስጥ ባገኛት ፤ አብሬያት ገደል መግባት አለብኝ። ደሞ ከማንም ጋር ብትሆን አልለቃትም” --አረንጓዴ በራና መኪናዋ ተነሳች። --“ለምን ስድስት ኪሎ ያለው ኣንበሳ ራሱ እያጓራ መትረየሱን ጠምዶ አይመጣም? አልለቅለትም! የትም ብትሄድ አብሬያት መሄድ አለብኝ። ለምን በሉኝ። ለምን ማለት መልካም። ምክንያቱስ? ፍቅር ነዋ!

“ፍቅር ፍቅር አሉት ስሙን አሳንሰው

ከደንጊያ ይከብዳል ለተሸከመው ሰው

አለ ትልቁ ናፖሊዎን። ... እኔ ግን እሷን በእህትነት ነው ማውቃት። እቺን ሌሊት አያንጋልኝ! ከናንተ ከወንድሞቼ ምደብቀው ነገር የለኝም--

“እውነቱን ነው። ወዳጇ አይደለም። ወንድሜ ነው። ታዲያ ይኸውልህ ጋሽዬ_

“እዚህ ነው ምወርደው። አቁም አቁም አ! አ! አቁም አልኩት- እዚህ አውርደኝ።”

ይኸኔ አዲሱ አርቲስቲክ ፎቅ ደርሰናል። ሴትዮዋ ልትወርድ ስትል ፥

“በል ስሙኒህን እሳቸው ይከፍሉህል” አለችው።

“ሌላውስ ስሙኒ?”

“የምን ሌላ ባክህ?”

“እንዲያውም ሰባ አምስት ነበረ”

“እሱን ተወው!”

“አሁን ጭቅጭቁ ይቅርና ሀምሳ ሳንቲም እፈልጋለሁ”

“ስንት ነው ያለባቸው?” አልኩት።

“ሀምሳ ሳንቲም”

ከፈልኩላት የራሴንም ከፈልኩ ፡ እና ከመኪናው ወጣሁ። ፂሜን ለመላጨት ወደ ፀጉር አስተካካይ ቤት አመራሁ።

....ከሰአት በኋላውን ከስህነ ጋር ነበር ያሳለፍኩት።

“ሰሞኑን ብዙ ሳጠና ነበር። ዛሬ ማታ አባባ የፈቀዱልኝ እንደሆነ ሲኒማ ትወስደኛለህ?” ብላኝ ነበር።

“በደስታ”

“የት ነው ምንገባው?”

“የትም ጥሩ ፊልም የለም። ዝም ብለን ብሔራዊ ቲያትር እንግባ”

“ከሁሉም እሱ ይሻላል?”

“አይ! መሻሉንስ ኢትዮጵያ ይሻላል”

“ታዲያ ለምን ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ አትወስደኝም?”

“ወንበሩ ይቆረቁረኛል ባክሽን። ብሔራዊ ግን ሶፋው”

“ቀበጥ ነህ”

“ውሸቴን ነው። ለሶፋው አይደለም”

“ታዲያ ለምንድነው?”

“ሚስጥር ነው። ለልጆች አይነገርም”

“ንገረኝ”

“እእ!” – ራሴን እያነቃነቅኩ

እባክህን” በፈገግታ

“እእ!”

“ተው!”

“እእ!”

“ተወዋ! ይቅር። እኔ ደሞ ካልነገርከኝ አብሬህ ሲኒማ ኣልገባም”

“እሺ-ሺ! እነግርሻለሁ”

“ንገረኝ”

“ቲያትር የገባን እንደሆን ፎቅ ወጥተን ወደ ኋላ መጨረሻ ተርታ ያለው ወንበር ጋ እንቀመጥና አንቺ ፊልሙን ታያለሽ”

“አንተስ?”

“እዚህ ላይ ተንተርሼ እተኛለሁ”

“ኢድ!” (“እዚህ ላይ” ስል ደረቷን እያመለከትኩ ነበር።)

“ምን አለበት? አልከብድሽ።”

“መክበዱንስ አትከብደኝም። ብቻ ጢምህ ይኰሰኩሳል። አሁን’ ንኳ ይኸው ፊቴን ያቃጥለኛል”

“እላጨዋለሁ”

ልክ ፀጉር አስተካካዩ ቤት ስደርስ ፥

“አንቱ! ጋሼ ፤ አንቱን ነው!” አለችኝ። ሴይቼንቶው ውስጥ የነበረችው ሴትዮ ነች።

“ምነው?” አልኳት በመብሸቅ። ስለ ስህነ ሳስብ ሰው ሲያቋርጠኝ አልወድም።

ኑ ሽልንግሁን ልክፈልሁ”

“ግድ የለም”

“የለም እከፍላለሁ”

“የለም ምንም አይደለም”

“እሺ ቤቴን ላሳይዎ”

“እቸኩላለሁ”

“አንዳፍታም አይፈጅ ፤ እዚችው ነች።”

ሴትዮዋ ሀሳቧን ቆርጣለች። እምቢ ብላት ጭቅጭቅ ማብዛት ይሆናል። በዛ ላይ ደሞ ቤቷን ማየት ፈለግኩ። ሰሞኑን በስህነ ፍቅር ምክንያት ተኝቶ የነበረው የደራሲነት ስሜቴ ተቀሰቀሰ።

ወደ ሴትዮዋ ቤት ለመሄድ አርቲስቲክ ህንፃ ፊት ለፊት ያለችውን ወደ ጎርጊስ የምታወጣ ዳገት መንገድ ይዘን መራመድ ጀመርን።

“ቤቴንም ልጆቼንም ታያለህ” አለችኝ።

**** ***** *** **** ***

ከሲኒማ አምፒር ወደ አገር ፍቅር የምታስኬደውን መንገድ አለፍ ብለናል በግራና በቀኛችን ሴተኛ አዳሪዎች እንደ ደንባቸው በየበራፋቸው ቁመው ወይ ቁጭ ብለው ቀይ መብራት ተጎናፅፈው ፡ አላፊ አግዳሚውን ይመለከታሉ። እጇን ካፖርት ኪሴ ውስጥ ከትቼ ነበር። ታዲያ ቀኝ እጅዋን አምጥታ ከግራ እጄ ጋር አቆላለፈችው “ሶቶ ብራቾ” ---ፈረንጆቹ ባልና ሚስቶች ንፋስ ለመቀበል ሲወጡ እንደሚያያዙት። በግራና በቀኝ የተሰለፉት ሴተኛ አዳሪዎች እንዲያዩላት ብላ ነው። እጅዋን ወዲያ ልወረውርላት ነበር ፡ ምን ቸገረኝ ብዬ ተውኩት።

ሴትዮዋ “ወርቅ የመሰሉ ሁለት ልጆች አሉኝ” አለችኝ።

አንድ ሰላሳ እርምጃ እንደ ሄድን ፡ “እዚህ ነው” አለችና አንድ ጠጅ ቤት ውስጥ አስገባችኝ።

በሩ ፊት ለፊት አንዲት ቀይ ሴትዮ --ጥቁር ሻሽ ያሰሩ የሀበሻ ቀሚስና ጥቁር ሹራብ የለበሱ --በርጩማ ላይ ተቀምጠው ቡና ያፈላሉ። ምድጃው

አጠገብ ሌላ በርጩማ ላይ ሁለት ትንንሽ ሴት ልጆች ቁጭ ብለው እሳት ይሞቃሉ። በግራ በኩል ያለው ግድግዳ ጥግ ርዝመቱ ከግድግዳው እኩል የሆነ አግድም ወንበር አለ። የጠጅ ቤት ወንበር። የእንጨት። ሁለት ሰዎች ብቻ ተቀምጠወበታል። ኣጠገባቸው መሬት ላይ ሁለት የተጠጣበት ብርሌ ተቀምጧል። በቀኝ በኩል አንድ የባልና ሚስት አልጋ ተዘርግቷል።

ልክ እንደገባን ሴትዮዋ በርጩማ ላይ ያሉትን ልጆች ሳመቻቸው። እኔ ወደ አልጋው አጠገብ ሄድኩና ቆምኩ። (እዛ ሆኖ ከውጭ አይታይም። ) ሴትዮዋ ወደኔ መጣች ፤ "እኚውልህ ልጆቹ ፤ ወርቅ አይደሉም? ቁጭ በል እሱ አልጋ ላይ" አለችኝና ፤ እንደገና ሄዳ ትንሽቱን ልጅ አቅፋ አመጣቻት።

"እቻትልህ ትንሿ። ጋሼ በይው አንቺ። ጋሼ! በይው እንጂ ጋሼ! ሶስት አመቷ ነው። ወርቅ አይደለችም?"

አለችና ፤ ልጅቷን ከንፈሯ ላይ ሳመቻት።

"ሳሚኝ ፋንቱ ፤ በሀይል ሳሚኝ" አለቻት። ከንፈር ለከንፈር ተማጠጡ። ቀፈፈኝ። ለምን እንደሆነ እንጃ። ምናልባት እናትና ልጅ ስለሆኑ ፤ ወይም በቀይ ሙብራት ስላየኋቸው ይሆናል። "እንደገና" አሁንም ተማጠጡ።

"ዐይናበባ!" ታላቂቱን ጠራቻት። "ኣንቺ ዐይናበባ! -- አሁን እንግዲህ ቀንታለች። ዐይናበባ!?"

ቀስ ብላ መሬቱን እያየች መጣች። አምስት ዓመት ይሆናታል። ጠይም ነች ፤ አይኗ ትልልቅ ፤ ፀጉሯ ዞማ። በጣም ቆንጆ ነች።

"ጨብጪያቸው ጋሼን።"

እኔና ዐይናበባ ተጨባብጠን። ከዛ ቶሎ ብላ ሄዳ በርጩማዋ ላይ ተቀመጠችና ጉልበቷን አቅፋ የተጣደውን የቡና ጀበና ፊዛ መመልከት ጀመረች።

እናትዮዋ ትንሽቱን ፋንቱን እንዳቀፈች

“ቁጭ በል “ንጂ” አለችኝ።

“እቸኩላለሁ።”

“ገና ነው። ቁጭ በል ትንሽ። ፋንቱ ፤ ቁጭ በል በይው። በይው!”

“ኩች በል” አለችኝ። ድምጿ በጣም ይጣፍጣል።

ኣልጋው ግርጌ ተቀመጥኩ።

እናትዬዋ “ጠጅ ግዛልኝ ለራስህም ጠጣና እንሄዳለን” አለችኝ። (የት እንደምንሄድ እንጃ።)

“አልጠጣም”

“አንዳንድ ብርሌ ብቻ! ምነው ጥሩ ጠጅ ነው ኮ”። የማር ጠጅ ነው። ”

“የለም ራሴን ያመኛል”

“እኔ በጣለሁ ግድ የለም”

“ገንዘብ አልያዝኩም”

“አንድ ብርሌ ብቻ!”

ብሽቅ ቅጥል አልኩ።

“ገንዘብ የለኝም አልኩሽ”

“ስሙኒ!?”

ከመበሳጨቴ የተነሳ ጭንቅላቴን በማነቃነቅ እሽ አልኳት። ብተፋባት ፈቃዴ ነበር።

“ጠጅ በብርጭቆ ስጪኝ እትዬ” አለቻቸው ቡና ሚያፈሉትን ሴትዮ። ከገባን ጀምረው ሲመለከቱን ነበር ፤ ጠጁን ቀድተው አመጡላት።

“ለሳቸውስ?” አሉ ወደኔ በኩል። ድምፃቸው ደስ አይልም። ፊታቸው ላይ ክፋት ወይም መከፋት ያደፈጠ ይመስላል።

“ተማሪ ነው አይጠጣም” አለቻቸው።

በንቀት አይናቸውን ጣል አደረጉብኝና ወደ በርጩማቸው ተመለሱ። ሴትየዋ ከጠጁ አንዴ ፉት አለችና ህፃኗን ፋንቱን ፉት አስደረገቻት። አሁንስ አልበሸቅኩም። አዘንኩ። ይኸ እንዳይበቃት! ሌላ ብርጭቆ አመጣች ፤ ሩብ ያህሉ ጠጅ ገለበጠችበት እና ለዐይናበባ ሰጠቻት። ትልቋ ሴትዮ ብጭቆውን ከዐይናበባ ቀሙ ፣ ለይስሙላ ትንሽ ውሀ ጠብ ኣደረጉበትና መልሰው ሰጡዋት።

እናትዮዋ ፋንቱን እንደታቀፈቻት እንደገና ጠጅ ፉት ኣስደረገቻትና ፥

“ዳቦ መብላት ትፈልጊያለሽ?” አለቻት

“አው!” አለች። ድምጿ መጣፈጡ!

“ጋሸዬን ግዛልኝ በይው -- በይው --አይዞሽ አትፍሪ--ጋሸዬ ዳቦ ግዛልኝ በይው”

ፋንቱ አየችኝና ፤ ኣፍራ መለመኑን ተወችው።

ኣሳዘነችኝ።

“ድንቄም የኛ አይናፋር! በይ ንቺ!” አለችና ከጠጁ አጠጣቻት።

“ኣስር ሳንቲም አለህ? ለልጆቹ ዳቦ መግዣ?” አለችኝ። አውጥቼ ሰጧኋት። እዛው በዛው ፤

“ሌላ ኣስር ሳንቲም የለህም? ሻይና ስኳር መግዣ። የዛሬ ልጆች ዳቦ ያለሻይና ስኳር አይወዱም።”

ለሷ አፈርኩላት። ከዚህ ጋር ደሞ ንዴቱ ውስጤ ገነፈለ። ሰው አንዴ ደግ የዋለለትን ሰው ለምን ቂል በግ ያደርገዋል? እዛ ሰይቸንቶ ውስጥ “ጋሼ

ስሙኒ ክፈሉልኝ” ስትለኝ “የማነሽ ቆንጆ?” ብላት ኖሮ ይኸ ሁሉ ባልመጣ።

ቤቴን ላሳይህ ስትለኝ እቸኩላለሁ ብዬ ሄጄ ብሆን ኖሮም ባጭሩ በተገላገልኩ። እንዲህ እያሰብኩ “እሺ እሱን አስር ሳንቲም መልሽ” አልኳትና ሀያ አምስት ሳንቲም ሰጧት። ፋንቱን ፥

“እግዜር ይስጥልኝ በይው” አለቻት።

ፋንቱ ዝም ብላ አየችኝ። አፍራለች። አንዳንድ ትንሽ ልጅ ነገሩ ሳይገባው እንዲያው ያፍራል። ወይስ ይገባዋል??

“በይው ንጂ!” አለቻት።

ፋንቱ በእፍረት እናቷ አንገት ስር ተደፋች።

ሰአቴን አየሁ። ቀጠሮዬ ደረሰብኝ። ልሄድ ተነሳሁ።

ሴትዮዋ “ምነው ቆይንጂ” አለችኝ።

“እቸኩላለሁ።”

“አንድ ሲኒ ቡና ልጠጣና እንሄዳለን።

እቸኩላለሁ ኣልኩሽ”

“አንድ ሲኒ ፉት እስክል”

“አ!”

“እሽ ‘ንግድያው ክፈልና እንሄዳለን”

“የት ነው ምንሄደው?”

“ቤቴን ላሳይህ ነዋ! ይኸ ቤቴ መሰለህ” ንዴ? የህቴና የጓደኛዋ ነው። የኔ ቤት ሌላ ነው።”

“እንግዲያው ሌላ ቀን ብታሳይኝስ?”

"እዚችው ነች 'ኮ። ከፈልና ንሂድ

ከፈልኩ። ዐይናበባንና ፋንቱን ሳመቻቸው ፤ እኔ ጨበጥኳቸው። ወጣን። አሁንም ሴተኛ አዳሪዎቹ ተርታ ስናልፍ እጅዋን ከእጄ ጋር አቆላለፈች።

አንዲት በጣም ጠባብ ክፍል። ቀይ ወረቀት የጠመጠመች አንዲት ትንሽ አምፑል የክረምታቱ ዝናቦች የደመናዎችን አገር ካርታ ያነሱበት አሮጌ ኮርኒስ መካከል በገመድ ተንጠልጥላ ለግብር ይውጣ ያህል የሴትዮዋን ቤት ታበራለች። አንዲት በጣም ጠባብ ክፍል ፤ ወለሏ ላይ ሳንቃ የሌላት ፤ ግድግዳዋ የደረቀ የተሰነጣጠቀ ልስን ጭቃ በልዩ ልዩ ባለስእል ወረቀቶች የተደረተ ግድግዳ። አንዱ ግድግዳ ስር አንድ ያልተነጠፈ የብረት አልጋ

"ይቅርታ አልተነጠፈም" አለችና የተጨረማመተውን ብርድ ልብስ ዘርጋ አድርጋ ፤

"ተቀመጥ" አለችኝ። ተቀመጥኩ።

በሩን መለስ አደረገችው። አልጋው አጠገብ (በራስጌው በከል) አንድ ትንሽ ሳጥን አለ ፤ላዩ ላይ ጥቁር ኣጐዛ ፤ እሱ ላይ ቁጭ አለች። እና መናገር ጀመረች።

ለምን መናገር እንደጀመረች አላውቅም። ግማሽ ስካሯ በቂ ምክንያት አይደለም። ምናልባት ፊቴ ላይ ያየችው ነገር ይኖር ይሆናል። ወይም ደሞ በዛ ሁናቴዋ ማንም ሰው ቢያጋጥማት ትናገር ነበር ይሆናል። ነብሳችንን ስቃይ ሲያፍናት ምላሳችን ምን ያህል እንደምትንጨረጨር ማን ለክቶ ያውቃል? የሆነ ሆኖ ሴትዮዋ መናገር ጀመረች። እኔም አንድ ቃል ሳልተነፍስ እስከ በመጨረሻው ሰማኋት።

"ልጆቼን አየሀቸው? ወርቅ አይደሉም? እኔ ምወደው ትንሿን ነው። አይ! ግን ውሸት ምን ያረጋል ፤ ትልቋን ነው "ምወደው። እሷም እነሱ

ሲያዩዋት ማትወደኝ ትመስላለች ንጂ፤ በጣም ነው ምትወደኝ። እንዲህ አይምሰልህ።

(“እነሱ” ስትል ፡ ቅድም የነበርበት ጠጅ ቤት ውስጥ ያሉት ቀይ ሴትዮና ፤ እኔ ያላየኋቸው አብረዋቸው፡- የሚኖሩ ጓደኖቻቸውን ማለቷ ነው። ሴትየዋ እህቷ ናቸው።)

“ውይ! በጣም ነው ምወዳቸው ልጆቼን--ምክንያቱም ሁለቱ ብቻ ናቸው ያሉኝ። ዘጠኝ ወልጄ ሰባቱ፡ ሞቱብኝ። ስወልድ ሲሞቱብኝ ፤ ምነው ምን ሃጢአት ሰራሁ ብዬ አምላክን አማረርኩት

“እና ይህን አመጣብኝ ይኸውልህ።

“መውለድ ጣጣ ነው። እኔ ለናቴ ምን ሰራሁላት? አንተ ለአናትህ ምን ታረግላቸዋለህ? – እናት አሉህ? ጐሽ! ጥሩ ልጆቼስ ለኔ ምን ያረጉልኛል? ስቃይ ብቻ!

“እዛ በሄድኩ ቁጥር የመጣውን ሁሉ ጠጅ ግዛልኝ እያልኩ ካላስቸገርኩ ካላሰለቸሁ ልጆቼን በደንብ አይይዙልኝም እያልኩ እፈራለሁ። እና ይኸውልህ ለልጆቼ ስል ጠጅ ለማኝ ሆኜ ቀረሁ። መለመን እንዴት ይቀፋል መሰለህ? የራበው፡ “ንኳ ቢለምን ያምርበታል። ግን ጠጅ ልመና! አይ ኣንታ” አምላክ! አሁን አሁንማ ጠጁ እየጣመኝ ሄደ። ሰካራም ልሆን ነው።

ረዣዥም ጣቶቿን ማቆላለፍ መፈታታት ጀመረች። በልዩ ጥንቃቄ የተቀረፁ እጆች ፤ የእብነ በረድ ውበት ያላቸው።

“ታድያ ያየኝ ሰው ልጆቼን ወልጄ የጣልኩ ይመስለዋል። እኔ እንደውሻ አንጠባጥቤ ሄጄ ፤ እነሱ ለግዜር ሲሉ የሚያሳድጉ ይመስላሉ።

“ለላም ቀንዷ ይከብዳታል? የትኛው አንገት ነው ራሱን የማይሸከም? የራስህ አጥንትህ ይቆረቁርሀል? ልጅዋን “ማትወድ እናት የለችም ልንገርህ። አንዲት እናት ልጅዋን እንኳ አንቃ ገደል ብትጥል ልጅዋን

ጠልታ አይምሰልህ። ለልጁ ሞት ይሻለዋል ብላ ነው። እኔ ልጆቼን ጠጅ ቤት የምተዋቸው ከነሱ መራቅ ፈልጌ መሰለህ? እኔማ” ዚሁ አቅፌያቸው ብውልና ባድር ፈቃዴ ነበር። ግን እዚች ምኗጋ ይጫወታሉ?

ያለንባት ክፍል ቁመቷ ሶስት የቀስታ እርምጃ ወርዷ አራት ይሆናል። ሲሶውን ቦታ የተቀመጥኩበት ኣልጋ ይዞታል። ኣልጋው ፊት ለፊት ሌላውን ግድግዳ ተጠግቶ ኣንድ ተለቅ ያለ የእንጨት ሳጥን ተቀምጧል፤ የተቦጫጨቀ ፕላስቲክ የጠረጴዛ ልብስ ለብሶ አንድ አምስት የሚሆኑ ባዶና ግማሽ ባዶ ጠርሙሶች ከጥቂት የተደፉ ብርጭቆዎች ጋር ተሸክሟል። ሳጥኑና አልጋው መካከል አንዲት ምድጃ በሶስት እግሯ ቆማለች። ካልጋው ግርጌ በኩል አንድ መደገፊያው የጠፋበት የእንጨት ወንበር አለ ፤ አንዲት ባዶ የቢራ ጠርሙስ አፏን ከፍታ ቂጢጥ ብላበታለች። በቃ። ሌላ እቃ የለም። ሌላ ቦታ የለም። ቤቷ ይህን ያህል ጠባብ ናጥ

“ለዚች የውሻ ጐጆ ለምታክል ክፍል በወር ሰላሳ ሁለት ብር እከፍላለሁ። መንገድ ዳር ስለሆነች ነው። ኧረ መዝለሉ መጨፈሩስ ይቅር ፥ እዚች ምኗ ላይ ይተኛሉ? ሌላ ኣልጋ እንኳ ብከራይ የት እዘረጋዋለሁ? ደሞ ወንዱ ሲገባ ወንዱ ሲወጣ ምን ይመስላችዋል? እንዲያውስ እኔ ውጭ ያደርኩ እንደሆነ ከማን ጋር ያድራሉ?

“ደሞ እንደሰባቱ እንዳይሞቱብኝ እፈራለሁ። የመውለድ ነው እንጂ የማሳደግ እድል የለኝም። ቢሞቱብኝስ? ኣይ እዛው ቢጐዱ ይሻላል። ጉዲፈቻ ከመስጠት ለዘመድ መስጠት ይሻላል።”

“እና ይኸውልህ ፡ ስለዚህ ነው እዛ “ምተዋቸው። አይ እናት መሆን! ጣጣ ነው እልሀለሁ።

እሷ ስታወራ ረዣዥም ጣቶቿ ያለማቋረጥ ይቆላለፋሉ ይፍታታሉ ፤ ይቆላለፋሉ ይፍታታሉ። የጥፍር ቀለም አልተቀባችም። በዛች በሙትቻ ቀይ አምፑል ብርሃን እንኳ ጥፍሮቿ ውስጥ ቆሻሻ እንዳለ ያስታውቃል።

“ደሞ አሳደግን ይላሉኮ። አይ ማሳደግ! በቀን ሁለት ሶስት ብር ካልሰጠኋቸው ልጆቼን የሚያረጉዋቸውን አታቅም። .... ወይኔ ልጆቼ! ሆዴን ይበሉኛል ይኸውልህ። ግን ምን ማድረግ ይቻላል?

“ስራ እንዳልይዝ ያዲሱን ዘመን ስራ ምኑን አውቄበት። ደሞስ ስራው ከየት ተገኝቶ? እንዳላገባ እንደምታየው ነው። ሰላሳ አመት አልፎኛል። ዘጠኝ ወልጃለሁ። መልኬ መርገፍ ጀምሯል። እንዲያውስ ሽርሙጣን ማን ያገባል? ያውም ሁለት ልጆች ያሉዋት!

“እና ይኸውልህ ፡ ጎርጊስ አንዱን አምጣልኝ እያልኩ ነው ምውል ማድረው። መቸም ጎርጊስ እንደማይሰማኝ አቃለሁ ፤ ብቻ እንዲያው ጎርጊስ አምጣልኝ እላለሁ። ሌላ ምን ልበል? አምላክ ግን የድሀን ፀሎት አይሰማም።

ካልጋው በላይ አንድ ትልቅ የመልአክ ስእል ግድግዳው ላይ ተለጥፏል። መቀነቱ ነጭ የሆነ ቀሚስ ለብሷል። እንቁላል የሚመስሉ አይኖቹ ብጫ ፊቱን ሞልተውታል። ወደ በሩ ይመለከታሉ። በቀኝ እጁ ሰይፍ ይዞ ፤ ሴጣን እንዳይገባ ፤ ክፉት እንዳይገባ በሩን የሚጠብቅ ይመስላል። ብጫ ፍልጥ በሚመስሉ እግሮቹ መካከል ኣጣጣሉ የቄስ የሚመስል ፅሁፍ ፡ አለ።

ቅዱስ ሚካኤል።

ሊቀ መላእክት

ይላል።

ሌላዎቹ ግድግዳዎች ላይ የሆሊዉድ እክተሮችና የፓሪስ ልብስ ሞድ አሳዩዎች ተሰጣጥፈዋል።

“ወርቄን ጌጤን ሁሉ ሸጬ ይኸው እቺ መስቀልና ሀብል ብቻ ቀሩኝ። በዘበኔ ግን ያላየሁት ጌጥ የለም።

ሙዳይ ሙሉ ጌጣጌጥ ነበረኝ። አንዷም አርተፊሻል አይደለች። ሴቶቹ እዚህ ያሉት ሲለብሱ ሲያጌጡ አያምረኝም መሰለህ? ግን ልጆቼ ካልለበሱ ይበርዳቸዋል ፤ ጫማ ካላረጉ ይታመሙብኛል እያልኩ ነው። ልጆቼ የሌላ ልጅ ብስኩት ሲበላ እያዩ ብስኩት ያምራቸዋል ፤ የሌላ ልጆች ሲቀብጡ ሲያዩ ይቀኑ ይሆናል እያልኩ ነው። ልጆቼ ምንም ኣይጡ ብዬ ነው።

“በጣም ያምረኛል መልበስና ማጌጥ። ሴት አይደለሁም? ግን ምን ይደረግ ፤ ወለድኩ።

ውብ ጣቶቿ አሁንም ይቆላለፋሉ ፤ ይፍታታሉ! ይቆላለፋሉ ይፍታታሉ።

“እዛ ሄጄ ልጆቼ ብዬ ከልጆቹ ጋር የተጫወትኩ እንደሆነ ፤ እኛ እያሳደግን ልጆቼ ትላለች ይሉኛል። ግን ውስጡን ብታይ!

“በቀን አንድ ሁለት ብር ካልሰጠሁ ልጆቼን ያሳድጉልኝ መሰለህ? “ምን በወጣን ከማንም ዲቃላ ጋር እንዳረቅ” ነው ሚሉኝ ልንገርህ። ደግሞ ሂጄ እዛ ወይም “እንካችሁ ለልጆቹ ወተት ግዙበት” ብዬ አንድ አስር ብር በየጊዜው መስጠት አለብኝ። ግን ለልጆቹ ወተት አምስት ብር ብቻ እንደሚወጣ ፡ የተረፈን አምስት ብር ለራሳቸው እንደሚያረጉት አጥቼ አይምሰልህ።

“አሳደግን ይላሉኮ! ልጆቹ እዛ ስለሚተኙ ነው ‘ዒ፤ የሚያሳድጋቸው ማን ነው? ታውቃለህ? ቡና “ንኳ ሳላፈላ ምውልበት ጊዜ አለ።

መሬቱ ላይ ፡ ባለሶስት እግሯ ምድጃ አጠገብ፡ ባንድ ሰባት ሲኒ የተከበበች የቡና ጀበና የያዘ ረከቦት አለ። በሩ ስር አንድ የተገጣጠበ ከድሮ ነጭነቱ ወደ ግራጫ የተለወጠ የፊት መታጠቢያ ሰሀን ውስጥ ፡ ውሀ የሞላ ጣሳ ተቀምጧል።

“ውይ! ልጆቼን ወድ -ዳቸዋለሁ!

“ትልቋ ያለፈው ጥቅምት ኪዳነ ምህረት አምስት ዓመቷ ነው። ግን ብልጥ ነች!”

ትላንት ወይ ከትላንት ወድያ ቤቱ ሲጠረግ አንዲት የቄጠማ ቁራጭ መጥረጊያውን እንደኖህ አምልጣው ተርፋለች። ሴትዮዋ እቺን ቄጠማ አነሳችና በጥርሷ እየበጣጠሰች ብጣሹን “ጽ!” ከሚመስል ድምጽ ጋር እየተፋች ንግግሯን ቀጠለች።

“ምላጭ! እዛ ሂጂ ነይ ወይንዬ ስላት አትመጣም። ዝም ብላ ታየኛለች። በትልልቅ አይኗ።

“ታዲያ ይከነክነኛል። ላይላዩን እየሳቅኩ ውስጥ ውስጡን አላቅሳለሁ። ከተማሪ ቤት በዚህ በኩል ስትመለስ ብቻችንን ስንሆን “እማዬ ካንቺ ጋር ልቀመጥ፤ ቤት እጠርግልሻለሁ ፣ ቡና አፈላልሻሁ ፥ አልጋ ኣነጥፍልሻለሁ ፥ ካንቺ ጋር ልቀመጥ” ትለኛለች። ታዲያ እዛ ቤት እነሱ ሲያዩ ልክ እንደማትፈልገኝ ነገር ትርቀኛለች። ያምስት አመት ልጅ እንዲህ ሲሆን አያሳዝንህም? እኔማ በቃ ብስጭት ጭት ጭት! እልና ዘልዬ እይዛትና እስማታለሁ። ወይም እመታታለሁ። ታድያ ቀስ ብላ ትጠፋለች። ውስጠኛው ክፍል አጭበርብሬ እገባና ቁጭ ብላ አገኛታለሁ። መትቻት እንደሆን እያለቀሰች ትቆየኛለች። ደሞ ስታለቅስ ጭብጥብጥ ብላ ጉልበቷን አቅፋ እየተወዛወዘች ነው። ሆዴ ቦጭ ቦጭ ይላል። እቅፍ አረጋትና አብረን እንላቀሳለን። እነሱ እያዩ እዛ ስሜያት እንደሆነ ደሞ ፤ ወይ ዝም ብላ አይኗን ከፍታ እያፈጠጠች ወይ ደሞ ፎቶዬን አቅፋ አገኛታለሁ። አሁንም አቅፋትና አለቅሳለሁ። እንባዬን በእጅዋ እየጠራረገች “አይዞሽ እማዬ ዝም በይ” ትለኛለች። የባሰው እንሰቀሰቃለሁ።

“ውይ ዐይናበብዬ! እሷ ምታየው ስቃይ! እንኳን ለልጅ ላዋቂም አይስጠው!

“ወደ ተማሪ ቤት ለመሄድ ጧት በዚህ ስታልፍ “እማዬ ከተማሪ ቤት ስመለስ ቆሎ አቆዪኝ ትለኛለች። ስትመለስ ቆሎውን እየቆረጠመች

ትሄዳለች። ቆሎ ያጣሁ እንደሁ ቤቱን እዘጋና እንደሌለ ሰው ከውስጥ ሆኜ ኣያታለሁ። በሩን ቁማ ታይ ታይና መለስ ብላ ራሷን ደፍታ መሬት መሬቱን እያየች ትሄዳለች። ፊደሏን ይዛ። ታዲያ ሆዴን ይበላኝና አልጋዬ ላይ ወድቄ እንሰቀሰቃለሁ። ግን ቆሎ ስጪኝ ምትለኝ እየራባት ብቻ እንዳይመስልህ። እኔ ስሰጣት ደስ ስለሚላት ነው። እኔም ማለቅሰው ልጄ ራባት ብዬ አይደለም። እንዲያውም በደንብ ነው ሚያበሏት። እኔ ማለቅሰው ልጄ እናት እያላት እናት እንደሌለው ልጅ ትሰቃያለች እያልኩ ነው።

"ታዲያ እነሱ ይህን ሁሉ መች ያውቃሉ? ቢያውቁስ የት ይገባቸዋል? አይገባቸውም እልሀለሁ። በፍጹም ኣይገባቸውም።"

ሴትዮዋ ቂጠማዋን በጣጥሳ ተፍታ ጨርሳት እጅዋን ባዶወን ስለቀረ እንደገና ጣቶቿን ማቆላለፍ መፈታታት ፤ ማቆላለፍ መፈታታት ጀመረች።

"እኔ'ዛ ሆኜ ትንሽ የማይፈልጉትን ነገር የሰራች እንደሆነ "እናትሽን አይተሽ ነው?" ይሏታል። እስቲ እግዜር ያሳይህ ፡ ልጅ እንዲህ ይባላል? ደሞ እኔን ኣይታስ ቢሆን እናቷ አይደለሁም ንዴ? ዘጠኝ ወር አርግዤ ሶስት ቀን አምጬ የወለድኳት እኔ አይደለሁም? ጡቴን ያጠባኋት እኔ አይደለሁም? ሳያት ሆዴ ቡጭ የሚልላት እኔ አይደለሁም? ለምን እናትሽን አይተሽ ነው ይሉብኛል? ለምን? ለምን?

"አይ መውለድ! መውለድ ስቃይ!

"እናትህ ላንተ ሲጨነቁልህ እንዲህ አይምሰልህ። ታዲያ ኣንተ ምን ታረግላቸዋለህ? እኔ ለናቴ ምን ሰራሁላት? ለኔ ልጆቼ ምን ያረጉልኝ መሰለህ?

"የመውለድ ትርፉ መሰቃየት ብቻ ነው።"

ምን እንደ ነካኝ እንጃ ፤ ፊቷን በእጄ ነካሁት። ከቋንቋ አቅም በላይ የሆነው ጥልቅ ነገር አይናችን ውስጥ ያበራል ፣ ፊታችን ላይ ይታያል ፣

በእጃችን ይተላለፋል። .....የሴትዮዋ ፊት ለስላሳ አይደለም።....ሳቅ የሌለበት ፈገግታ አሳየችኝ። ግንባሯ ላይ ሳምኳት። አልተንቀሳቀሰችም። ሳቅ የሌለበት ፈገግታዋም አልተለወጠም። ዝም ብለን ተያየን ፤ ቋንቋ አያስፈልገንም። ሴተኛ አዳሪና ገንዘብ ከፋይ አይደለንም።

“ውይ! ሞት ይርሳኝ ረስቸው። ትቸኩላለህ ለካ። እንዳሮጊት ስለፈልፍ ጊዜህን አጠፋሁብህ። ማርጀቴ ነው መሰለኝ። ግን ሁሌ ንዲህ አልለፈልፍም። እንዲያውም ዛሬ የነካኝን እንጃ። ትልቅ ሰው ስለሆንክ ችግሬን ባጫውትህ ይገባሀል ብዬ ነው።

“ዝም ብለህ ሰማኸኝ ፡ የሚሰማ ሰው የለም። በል ሂድ እማዬ ሳይመሽብህ።”

ከተቀመጥኩበት አልጋ ተነሳሁ ፤ ከሳጥኑ ተነሳች። አየኋት። ወፍራም አይደለችም ፤ ግን ሆዷ ወደ ውጭ ገፍቷል ፡ ቅርጿ ተበላሽቷል ፤ ማርገዝ መውለድ መቅበር ፤ ማርገዝ መውለድ መቅበር። አፉ ዙሪያና አይኖቿ ውስጥ ተስፋ ያልተቀላቀለበት ሀዘን ይታያል ፤ መስከር ወንድ መሄድ ማልቀስ ፤ መስከር ወንድ መሄድ ማልቀስ። ስለልጆቿ መጨነቅ ፤ ስለእርጅናዋ መስጋት። እድሜዋንና መከራዋን ተሸክማ ሳያት ወጣትነቴና ነፃነቴ ቀፈፈኝ። ፈጣሪ ለኔ ያደላ መሰለኝ።

የሆሊዉድ አክተሮችና የፓሪስ ሞድ ሴቶች በዙሪያችን ቁመው ወይ ቁጭ ብለው ይስቁብናል። የውነት ሳቅ ይሆን? ቅዱስ ሚካኤል ግን አያየንም በሩን ይጠብቃል።

ኪሴ ውስጥ አምስት ብር ነበረኝ፤ ሶስቱን አወጣሁና ለሴትዮዋ ሰጠኋት።

እጄን ሳመችኝ።

በጣም አፈርኩ። ፊቴ ላይ ምን እንዳየች እንጃ፡ “ለገንዘቡ አይደለም ፤ ለሀሳቡ ነው” አለችኝ።

የባሰውን አፈርኩ። ተደናገረኝ። በሩን ከፈትኩና ስወጣ ፤

“ደህናደር” አለችኝ።

“እሺ” አልኳት። በጣም ተደናግሮኝ ነበር።

ተለይቻት አንድ ሀያ እርምጃ ከተራመድኩ በኋላ ገልመጥ ብዬ አየኋት።

በሯጋ ቆማ ቀይ መብራቷን ተጎናፅፋ ትጠብቃለች – እንደሌሎቹ ሴተኛ አዳሪዎች።

መንገዴን ቀጠልኩ።

(የካቲት 6 1954 ዓ ም)

# ሞትና አጋፋሪ እንደሻው

አጋፋሪ እንደሻው የትም ቢሄዱ የሳምንት ስንቅ ተጭኖ የሚከተላቸው በቅሎ ነበራቸው።

ኣጋፋሪ እንደሻው ካደባባይ ፡ ከችሎት ፡ ከቤተስኪያን ወይም ከጉዞ ሲመለሱ ፥ ገና ከበቅሎ ሳይወርዱ አሽከሮቻቸውን፡

“ሰፈር ደህና ነው?” ይሉዋቸዋል

“ደህና”

“ሁሉም ደህና ነው?” ይላሉ ለማረጋገጥ።

“ደህና። ብቻ የወይዘሮ ደብሪቱ ልጅ ራሴን አመመኝ ብላ ተኝታለች”

“በሉ ደህና ቆዩኝ” ይሉና ውልቅ –አጋፋሪ እንደሻው።

ወንድማቸው ግራዝማች አየለ ቤት ይሄዱና አሁንም ከበቅሎኣቸው ሳይወርዱ ፡ አሽከሮቹን

“ሰፈር ደህና ነው?” ይሉዋቸዋል

“ደህና”

“በሰፈሩ የሞተ የለም?”

“ኧረ የለም”

“የታመመ የለም?”

“ኧረ የለም”

“መርዶ የሰማም የለ?”

“ብቻ የልጅ ገላጋይ እህት ድሮ የፈቱዋቸው ባላቸው ሞተዋል ተብሎ ለቅሶ ተቀምጠዋል”

“በሉ ደህና ሁኑ” ይሉና መንገዳቸውን ይቀጥላሉ።

እንዲህ ሲሉ አጋፋሪ እንደሻው ፡ ሞትን ሲሸሹ ፡ ስድሳ ስድስት አመት ሆናቸው።

አንድ አርብ እለት ከሰፈራቸው ሸሽተው ወዳጃቸው ደጃዝማች ዳኛቸው ግቢ ሄዱና ፡ አሁንም ከበቅሎአቸው ሳይወርዱ ፥

“ሰፈር ደህና ነው?” አሉ

“ደህና” አሉዋቸው የደጃዝማች አሽከሮች

“የሞተ የለም በሰፈሩ?”

“ኧረ የለም”

“የታመመም የለ?”

“የለም”

“መርዶም አልተሰማ በሰፈሩ”

“የለም”

“ደግ” አሉና ከበቅሎአቸው ወርደው ሲገቡ ደጃዝማች እየተቀበሉዋቸው እንደ ልማዳቸው ትንሽ ቀለዱባቸው። ዛሬ ደሞ ምን እግር ጣለህ? በሰፈርህ ሞት ብቅ አለንዴ” አሉዋቸው

“ተወኝ እባክህ ስሙን አትጥራብኝ” አሉ አጋፋሪ እንደሻው።

“ኧረ ለመሆኑ እዚህም አለ ቢሉህ የት ትሄድ ነበር?”

“ወደ አንዱ ጋ”

“እዚያም አለ ቢሉህስ?”

“ወደ ሌላው ጋ። የሳምንት ስንቅ ይዣለሁ። ቢያስፈልግ ውጭ እያደርኩ ኣሽከር ልኬ ማስጠየቅ ነው። አንዴ’ኮ ሶስት ሳምንት ሙሉ በድንኳን እንጦጦ አፋፍ ላይ ተቀምጫለሁ”

“ምን እየበላህ ፥ በል?”

“ከቤት ስንቅ እየተላከልኝ”

“እና እንዲህ እየሸሸህ ትዘልቀው ይመስልሃል?”

“ይኸው እስካሁን ዘልቄዋለሁ”

“እና እስከ መቼ ሸሽተህ ትችለዋለህ?”

እስከተቻለኝ። እንዲያውም ኣሁን መሄዴ ነው”

ብለው ብድግ አጋፋሪ እንደሻው።

“ወዴት?”

“እንጃ። ግን መሄዴ ነው።”

“አሁን መጥተህ አሁን መሄድ ምን ይባላል?”

“ቀፈፈኝ ባክህ። ሞት ሞት አለኝ።”

“ሞትም በሽታም መርዶም የለ በሰፈሩ። አይዞህ አረፍ በል”

“የለም እሄዳለሁ”

“እሺ ጠላ ጠጥተህ ትሄዳለህ ፡ ቁጭ በል

“ተው ብሄድ ይሻላል”

“አረፍ በልና ትሄዳለህ አልኩህ”

አጋፋሪ እንደሻው እየቀፈፋቸው ተመልሰው ተቀመጡ። ጠላው መጣ። ሁለቱም ወዳጆች ዋንጫ ዋንጫቸውን ይዘው ፉት አሉ።

“ግሩም ጠላ” አሉና እንደገና ተጐነጩ አጋፋሪ። እና ትን አላቸው። ደጋግመው በሃይል ሲስሉባቸው ጊዜ

“ትን ኣለህ እንዴ?” አሉዋቸው ወዳጃቸው “ንሳ ማንነህ? ውሃ አምጣ ቶሎ!”

ውሀው እስኪመጣ የትንታው ሳል ባሰባቸው። ጨነቃቸው። መተንፈስ አቃታቸው። ፊታቸው ተለዋወጠ። ውሃውን መጠጣት አልቻሉም። በመጨረሻ ትንፋሻቸው ፥

“ከንቱ! --ኡሁ ኡሁ ኡሁ! ከንቱ ያ ሁሉ አሉ።

አጋፋሪ እንደሻው በብዙ ሕዝብ ታጅበው የመጨረሻውን ጉዞ ወደ ጊዮርጊስ ጓሮ ሲጓዙ የጭን በቅሎአቸውም የሳምንት ስንቅ የተጫነ በቅሎአቸውም ተከትለዋቸው ነበር።

*************************

አጋፋሪ እንደሻው ሞተው ሰዎች እየተላቀሱ እንባ በዋንጫ እየተራጩ ሊቀብሩዋቸው በመሶብ ውስጥ የወሳንሳ ተሸክመው ሲወስዱዋቸው

ከመቃብር እንደ ደረሱ አጋፋሪ ከተጋደሙበት ብድግ ብለው የመሶቡን ክዳን ከውስጥ ብርግድ አድርገው ከመሶቡ ብቅ ሲሉ--

ሞት ዘወር ብሎ ጦሩን ሲወረውርባቸው--

እሳቸው የመሶቡን ክዳን እንደ ጋሻ እየመከቱበት ዘለው በቅሎአቸው ላይ ወጥተው ሲጋልቡ--

ሞት "የምናውቅብሽ ጉግስ ጨዋታ!" እያለ የስንቅ በቅሎአቸው ላይ ወጥቶ እየጋለበ ሲያሳድዳቸውና "መክት!" ሲላቸው--

እሳቸው "ዘራፍ! እንደሻው አባ መክት! ሽሽት ጋሻው ከሞት ይመክት! ዘራፍ!" ብለው እየፎከሩ ዘረው በመሶቡ ክዳን ሲመክቱ

እሱ ደሞ ከፊት ፊታቸው እየጋለበ እሳቸው ጦር ወርውረው ማጅራቱን ሲወጉት ፡ ድንገት የአክሱምን ሀውልት ሆኖ ይቆምና በወፍ ቋንቋ በተረት ዜማ ፡

"ሞት የያሬድን ቅዳሴ አፈነ

"የካሌብን አክሱም አሳለፈ፥ በጊዜ ወንዝ እያንሳፈፈ

አንተንም--- አንተንም-- አንተንም!" ይላቸዋል።

አጋፋሪ በበቅሎአቸው እየተንሳፈፉ ትተውት እልፍ ሲሉ የላሊበላን ቤተክርስቲያን ሆኖ ቆሞ ይቆያቸውና አሁንም በወፍ ቋንቋ በተረት ዜማ ፡

"ሞት ጠራቢውን ንጉስ ሸፈነ

የዛጉዌንም ሮሐ አሳለፈ ፡ በጊዜ ወንዝ እያንሳፈፈ አንተንም፡አንተንም ኣንተንም!" ይላቸዋል።

አሁንም በበቅሎአቸው እየተንሳፈፉ ትተውት እልፍ ሲሉ የፋሲልን ግንብ ሆኖ ቆሞ ይቆያቸውና በወፍ ቋንቋ በተረት ዜማ ፡

"ሞት የተዋነይን ቅኔ ቆለፈ

የበካፋን ጐንደር አሳለፈ ፡ በጊዜ ወንዝ እያንሳፈፈ

አንተንም--- አንተንም-- አንተንም!" ይላቸዋል።

አጋፋሪ በበቅሎአቸው እየተንሳፈፉ ትተውት እልፍ ሲሉ አራዳ ጎርጊስ ያለው ያጤ ምኒልክን ፈረሰኛ ሀውልት ሆኖ ቆሞ ይቆያቸውና በወፍ ቋንቋ በተረት ዜማ ፥

ሞት የገብረ ሀናን ሳቅ ሰየፈ

ያባ ዳኘውን ኣዲሳባ አሳለፈ በጊዜ ወንዝ --"

"አይ!! አሁን ገና ባይኔ መጣህ!" ብለው ጦር ሲወረውሩበት

ሞት እየመከተ "የምናውቅብሽ ጉግስ ጨዋታ!" ብሎ ጦሩን ሲወረውርባቸው--

ኢጋፋሪ በመሶቡ ክዳን እየመከቱ በበቅሎአቸው እንደ ነፋስ እየሸመጠጡ "ዘራፍ! እንደሻው አባ መክት ያሸሸት ጋሻው ከሞት ይመክት! ዘራፍ!" እያሉ ሲያመልጡ --

ሞት ሲደርስባቸው--

እሳቸው ሲፈተለኩ--

እሱ ሲደርስ--

ብንን ሲሉ ከህልማቸው አጋፋሪ እንደሻው ዘብሄረ አዲሳባ......

ሞትን ሸሽተው ሸሽተው ከቤታቸው ውጭ ሲያድሩ የሚያዩት ተመላላሽ እና ተመሳሳይ ህልም ነው እንግዲህ ይኸ። ላንድ ህልም አዋቂ ቢያጫውቱት ታዲያ ፥

"የህልሙ ፍቺ ከሞትክ በኋላ እንጀራ ትበላለህ ማለት ነው" ብሏቸዋል ፥ "የፍቺው ፍቺ ግን ለኔ ምስጢር ነው።"

ኢጋፋሪ ይህን ህልማቸውን ከነመመሳሰሉና ከነመለዋወጡ ለብዙ ዓመታት ካሰላሰሉበት በኋላ የቅርብ ወዳጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ሁሉ አንድ በአንድ እንዲህ እያሉ አስማሉዋቸው

“ቀድሜአችሁ የሞትኩ እንደሆነ ኑዛዜዬ ይህ ነው። ስትገንዙኝ እንዳታስሩኝ። በጨርቁም እንዳት ጠቀልሉኝ። በጥጡም እንዳትወታትፉኝ። እንዲሁ ብቻ ለበስ አርጉኝ።”

አንዳንዶቹም ውስጡን እየሳቁባቸው አንዳንዶቹቹም ውስጡን እያዘኑላቸው እሺ አሉዋቸው።

የቅርብ ወዳጃቸው ደጃዝማች ዳኛቸው ግን እንደ ልማዳቸው እየቀለዱባቸው

“ልክ ለመተኛት ጋደም ያልክ ይመስል?” አሉዋቸው

“ኣዎን” አሉ ኢጋፋሪ

“ምናልባት መገላበጥ ቢያሰኝህ እንደልብህ እንድትገላበጥ?”

ዝም አሉ ኢጋፋሪ

“ምናልባት ለሽንት ወይ ለሽርሽር ብድግ ብለህ መሄድ ብትፈልግ ከፈኑ እንዳይከለክልህ?”

ዝም

“አሁን ይህን ሁሉ ምን አሳሰበህ? ሳትሞት እንዳትቀበር ፈርተህ ነው?”

“መቀለዱን ቀልድ። ኑዛዜዬን ግን ሰምተሃል” አሉ ኢጋፋሪ ባጭሩ።

“አይ እንደሻው! ምነው በተቻለኝና ሞትህን በሞትኩልህ” አሉ ጓደኝየው የምራቸውን።

....አለፈ ጊዜ እየከነፈ ...አለፈ ብዙ አሳለፈ እያንሳፈፈ

ኣጋፋሪ እንደሻው ሞትን ሲሸሹ ኖረው በስድሳ ስድስት ዓመታቸው አንድ ዓርብ ዕለት ከወዳጃቸው ከደጃዝማች ዳኛቸው ጋር ጠላ ሲጠጡ በትንንታ መሞታቸውን ቀደም ሲል ተናግረናል። አሁን ወደዚያች ሰአት እንመለሳለን።

........በመጨረሻ ትንፋሻቸው፡

"ከንቱ! - ኡሁ ኡሁ ኡሁ? ከንቱ ያ ሁሉ ሽሽት!" አሉ አጋፋሪ እንደሻው።

የተሰሩት ጉድ ድንገት ወለል ብሎ ታያቸው። ለካ አብሯቸው ጠላ የጠጣው መልአከ ሞት ራሱ ኖሯል የወዳጃቸውን የደጃዝማች ዳኛቸውን መልክ በገዛ ስልጣኑ ለብሶ ነው እንጂ።

"ምናባክንስ! አንት መናጢ!" አሉት ሞትን አጋፋሪ፥ "እኔ እንደሻው! ብትይዘኝም በሚገባ አልፍቼህ ነጭ ላብ ኣስረጭቼህ ሳበቃ ነው።

ዝም አላቸው መናጢው።

"አይደለም?" አሉት።

ፈገግ አለ።

"ገና በልጅነቴ ኩፍኝ ሆነህ ስትመጣ የጀመርኩ። ሳመልጥህ ፡ ሳመልጥህ ገና አሁን ደረስክብኝ። አንት ጥፍራም!"

ዝም አለ ጥፍራሙ።

"ስድሳ ስድስት ዓመት ሙሉ ፈጀብህ። አንት ጅራታም!"

ዝም ኣለ ጥፍራሙ ጅራታም።

"ድሮውንስ ጅል ኣይደለህ? ቀንዳም!"

ዝም አለ ጥፍራሙ ጅራታም ቀንዳም።

"አፈር ብላ! ኮቲያም!"

“ዝም አለ ያ ጥፍራሙ ጅራታም ቀንዳም ኮቲያም።

ዝም-ፍጥጥ።

“መሸነፍህ ሲገባህ ጊዜ የወዳጄን መልክ አበስክ። መምጫ ሲጨንቅህ ጊዜ ትንታ ታህል ኢምንት ነገር ውስጥ ገብተህ አደፈጥክ”

ዝም ፡ እንደ መቃብር።

“እንጂ እንደ ወንድ ፊት ለፊት ለመምጣትማ የወንድ ሀሞት ከየት አምጥተህ? ለራስህ ጅል የጀልክ ጅላጅል!”

ዝም-ፍጥጥ። እንደ ሬሳ።

“አሳዳጊ የበደለው ባለጌ ባትሆን በእፍረት በሞትክ”

ከት ብሎ ሳቀ መልአከ ሞት። አጋፋሪም ከትብለው ሳቁ የገዛ ነገራቸው ሆዳቸውን ኮርኩሯቸው

“የማይቀርልህን እንግዳ አጥብቀህ ሳመው ፡ ነው ምትሉት እናንተ ሀበሾች?” አላቸው ያ አሳዳጊ የበደለው ባለጌ።

“ነው ምንለው” አሉት ራሳቸውን እየነቀነቁ፥ ትክ ብለው እያዩት። መልኩ ይህን ያህልም አያስጠላም ለካ ይኸ ሞት ሚሉት ነገር። ታድያ አጋፋሪ ለምን ይህን ያህል ጠሉት ይሆን?

(“መስሎሃል እማይቀር እንግዳ የሆንክ?” አሉት በልባቸው፥ “ሰማይ ቤት እመግቢያው እደጀሰላሙ እስክንደርስ ባላመልጥህማ እውነት እኔ እንደሻው አይደለሁማ!”

አጋፋሪ እንደሻው የጭን በቅሎአቸውንም የሳምንት ስንቅ የተጫነ በቅሎአቸውንም አስከትለው በብዙ ሕዝብ ታጅበው “የመጨረሻ” የተባለውን ጉዞ ወደ ጎርጊስ ዳሮ ሲጓዙ ኣንድ ነገር አስተዋሉ። ሬሳው ለፍትሐት በቆመ ቁጥር መልአከ ሞት “መጣሁ ብሎ ለሽንት ዘወር የሚል ይመስል ይሄድና ፍትሐቱ አልቆ ልክ ሬሳው እንደገና ሲነሳ ይመለሳል።

እና ሬሳው ቆሞ ለስምንተኛ ጊዜ ሲፈታ ፡ ልክ መልአከ ሞት "መጣሁ" ብሎ ዘወር እንዳለ

አቡነ ተክልዬ ከተፍ!

ባንድ እግራቸውና ባለባበሳቸው ፥ እንዲሁም በፂማቸው አወቁዋቸው አጋፋሪ።

(ክርስትና ስሜ ተክለሃይማኖት ስለሆነ ይሆን? አሁን "ታድያስ ሞክሼ" ቢሉኝስ? ብለው ሲያስቡ)

"ታዲያስ ሞክሼ" አሉዋቸው።

"ብፁእ አባታችን ሆይ! ተነስቼ እጅ እንዳልነሳዎ ነገሩ እንደሚያዩት ነው"

"ማን እንደሆንኩ ቢያውቁ ግን እጅ ሊነሱኝ ባላሰቡ" አሉ አቡን ተክልዬ (?) አቤት ፈገግታቸው ውስጥ የሚጫወተው ሳቅ!

"ማን ነዎታ?"

"አንቱታውንም ባልጫኑብኝ"

"እኮ ማነህ"? አሉ ኣጋፋሪ የፈገግታው ሳቅ እየተጋባባቸው።

"እንደ አገሩና እንደ ዘመኑ ስሜ ይለዋወጣል"

"እንግዲህ በዚህ አገርና በዚህ ዘመን ስምህ ማን ይባላል?"

"ቆሪጥ"

"በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!"

"አይዞዎ ኣይፍሩ"

“አይፍሩ?” አሉና ከት ብለው ሳቁ አጋፋሪ “እኔ እንደሻው ነኝ ቆሪጥን እምፈራ? አፄ እንትናን መሰልኩህ እንዴ? ይልቅ ንገረኝ እስቲ። ለምንድነው አቡነ ተክልዬን መስለህ የመጣኸው?”

ቆሪጥ ተራውን እየሳቀ “ይልቅ ለምንድነው እሳቸው እኔን መምሰላቸው?” አለ ፡ “ለዚያውም እኔ ያለኝ እግር ይኸኛው ፡ እሳቸው ያላቸው እግር ያኛው ነው። እሳቸው ሲጠመጥሙ ወደ ቀኝ እኔ ስጠመጥም ወደ ግራ ነው። የሳቸው ጥምጥም ጨርቅ ፡ የኔ ግን” ብሎ ወደ ጥምጥሙ ቢያመለክታቸው ለካ ዘንዶ ነው። የጠመጠመው።

“ብቻ እሱን እሱን ሌላ ጊዜም ልንጫወተው እንችላለን” አለ ቆሪጥ “አሁን የመጣሁት ለኔም ለርስዎም የሚበጅ አንድ ጉዳይ ላማክርዎ ብዬ ነበር” ኣጋፋሪ ዝም ብለው ቆዩ።

“እድሜዎን ብቀጥልልዎ ምን ያረጉልኛል?”

አጋፋሪ ሬሳ ባይሆኑ ልባቸው በድንጋጤ በቆመ። ቀጥሎም በደስታ በዘለሉ። ቀጥሎም ቆሪጥን አቅፈው በሳሙት። ግን ጆሮአቸውን ለማመን እየፈለጉም ኩምታውን ስለፈሩ። ፤

“ምን አልክ?” አሉት ለማረጋገጥ።

“እድሜዎን ብቀጥልልዎ ምን ያረጉልኛል?”

“የፈለግከውን” አሉት ባጭሩ (“ኧረ የልቤን ማን ነገረህ?” እያሉ ውስጡን)

“ሀብትዎን በሙሉ ይሰጡኛል?”

“ውሰደው”

“ሚስትዎን ብፈልግስ?”

“መርቄልሀለሁ ብቻ እድሜዬን ቀጥልልኝ”

“ነብስዎንም ይመርቁልኛል?”

ኣጋፋሪ ላንዳፍታ አሰቡና ፡

“ነብሴንማ ከወሰድክ ምኑን እድሜ ቀጠልክልኝ?” አሉት

“እድሜዎን ከጨረሱ በኋላ ነውኮ ነብስዎን እሚሰጡኝ። ረዥም እድሜ ብሰጥዎ ነብስዎን ይሰጡኛል?”

“በምኖርበት ዘመን ግን ነብሴ የራሴ ናት?”

“እንዴታ!”

“እንግዲያው ውሰዳት”

“ምነው ያለማመንታትዎ ያለመከራከርዎ?”

“ከህይወት ከሞት ሲሉኝ ህይወትን መምረጤ ይቀራል?”

“እና ህይወት ምንድነው?”

“መኖር ነዋ!”

“መኖርሳ ምንድነው?”

“ምኑን አውቄው ብለህ? ሲኖሩት ግን ይጥማል ፤ ማር ማር ይላል ፤ ሽቶ ሽቶ ይላል ፣ ሙቀት ሙቀት ይላል ፤ ኑሮ ኑሮ ይላል። በኑሮ ለመቆየት ያለኝን ሁሉ እከፍላለሁ። እሚቀበለኝ ባገኝ የሌለኝንም እከፍላለሁ”

“የማያወላውል የማያመነታ ሰው ገና ዛሬ ገጠመኝ” አለ ቆሪጥ አድናቆት በተቀላቀለበት የትዝብት ፈገግታ።

“ግን እድሜ መቀጠል ትችላለህ ወይ?”

“እችላለሁ። ግን እኔና እርስዎ ውል መግባት ይኖርብናል እንጂ”

“በል ቶሎ እንግባ ወዳጄ። ከዘገየን መቃብር መግባቴ ነው”

“እኔ ዛር ነኝ። አልፎ አልፎ ዛር ፈረስ ይሆኑኛል”

“ቶሎ እሺ አሉሳ? ቢያስቡበት አይሻልም?”

“እድሜዬን ሙሉ ኣስቤበታለሁዋ-- መሞት አልፈልግም መኖር እፈልጋለሁ። ሌላው ትርፍ ነው ፤ ኣጀብ ነው። ይልቅ እምታረገውን አርግና ቶሎ ኣስነሳኝ »

“ከሞት ጋር ጉግስ መግጠም ይኖርብኛል። ብቻዬን ከገጠምኩት ወይ አሸንፈዋለሁ ወይ ያሸንፈኛል። እርስዎ ካገዙኝ ግን ያለ ጥርጥር አሸንፈዋለሁ።

“እንዴት ላግዝህ?”

“ግራ ጐንዎን ያውሱኝና ከግጥሚያው በኋላ እመልስልዎታለሁ።

“የተሸነፍክ እንደሆነስ?”

“ይስሙኝ ኣጋፋሪ። እኔ ቆሪጥ ቀኝ እጅ እሆና--ለሁ ወርዋሪ። እንኳን ጦርን የመሰለ ግዙፍ ነገር ቀርቶ ጨረር ወይም ጭራ እወረውራለሁ። መመከቱን ደሞ በዚህ በግራ ጐንዎ እመክታለሁ። የእንደሻውን ምከታ የማን ውርወራ ይበግረዋል?”

ዘራፍ! አባ መክት!” አሉ ኣጋፋሪ

“ብቻዎን ሆነው ስድሳ ስድስት አመት ሙሉ አመለጡት። ለሁለት እየተጋገዝን ከዚያ የበለጠ አናመልጠውም?”

“ኧረ የትና የት?” አሉ አጋፋሪ፡ የእድሜያቸው ርዝመት የትና የት ደርሶ እየታያቸው። (አጋፋሪ ውስጡን እንደ ትንሽ ልጅ በደስታ ዘለሉ ዘለሉ ዘለሉና ድንገት ቀጥ ብለው እየቆሙ።) “ሰማህ ወይ ፡ ቆሪጥ?” አሉት “ይህን ጉግሱን ሞት ቢያሸንፈንስ? ”

“አያሸንፈንም። ሊያሸንፈን አይችልም”

“እሱማ የታወቀ ነው። እንዲያው ለነገሩ ማለቴ ነው እንጂ። ቢያሸንፈንስ?”

“ያኔማ ግራ ጐንዎን ለሞት መልቀቅ ይኖርብኛል”

አጋፋሪ ሊናገሩ ሲሉ በእጁ ምልክት እየገታቸው “ይቆዩኝ ልጨርስ አለ።” እኔ ከተሸነፍኩ አቡነ ተክልዬ ይመጡና የእርስዎን ቀኝ ጎን ተውሰው ሞትን ሰንጠረዥ ይገጥሙታል። ይረቱታል። ይዞት የነበረውን ግራ ጐንዎን ይለቃል።”

“እሳቸው ቢሸነፉስ?” አሉ አጋፋሪ ፡ ያቆለቆለችውን የተስፋቸውን ፀሐይ ጭለማ ሊውጣት እየቃጣ።

“አይሸነፉም። ተሸንፈው አያውቁም”

“ግን ግጥሚያ ካለ ማሸነፍም መሸነፍም አለ። ቢሸነፉስ?”

“ያኒማ አለቃ ገብረሀና ይመጡና ሞትን ይሟገቱታል። ይረቱታል። እርስዎ ነፃ ወጡ ማለት ነው”

“እሱ ቢረታቸውስ?”

“ተረትተው ኣያውቁማ”

“እረ ለነገሩ ማለቴ ነው። ቢረታቸውስ?”

“ያኔማ መምህር ኢየሱስ ይመጣና ሞትን ግብ ግብ ይገጥመዋል ፥ ጌታዬ! ይጥለዋል የታወቀ ነው። ግን ትግሉ ሁለት ቀንና ሁለት ሌሊት ቀጥሎ ሶስተኛው ቀን ሲነጋጋ ነው የሚያልቀው። ስለዚህ እርስዎ ያን ሁለት ቀንና ሁለት ሌሊት በሞት እጅ መቆየት ይኖርብዎታል እመቃብር ውስጥ።”

(አጋፋሪ በህይወታቸው ለጓደኞቸው በጠጅ በጨዋታ ሰአት የሚደረድሩላቸው የበገና ስልት ናፍቆቱን ለብሶ ትዝ አላቸው፡-

ሰማይን ያህል ዳገት

መቃብርን ያህል ቁልቁለት

እንዲያ ስንደክም ስንታክት ...)

“እንደ ገበጣ ጨዋታ ይቁጠሩት” አለ ቆሪጥ “እርስዎ እንግዲህ አንዲት ጠጠር ነዎ። ለጊዜው ሞት ከወጋው ጉድጓድ ውስጥ ስለገቡ እኛ ዞረን በሌላ ጠጠር እስክናወጣዎ መታገስ ይኖርብዎታል ማለት ነው። አሁንም ሞት ያሸንፋል እንበል”

“ኧረ አንበል! በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!”

“ኧረ ለነገሩ ለጨዋታው ማለቴ ነው” አላቸው ቆሪጥ በአሽሙር ሲነካቸው፡ “በትግሉ ሞት ቢጥል ደሞ እርስዎ የሞት ጠጠር ሆነው ጨዋታው ይቀጥላል። ጨዋታውንኮ እድሜዎን ሙሉ ሲጫወቱት ኖረዋል። አይፍሩ፤ በሞት በኩል ሆነው ብዙ ጊዜ ተጫውትወታል”

“እኔ እንደሻው? በጭራሽ!”

“ሳይታወቅዎ ነው እኮ”

“በጭራሽ ስልህ! ጤናም አልያዘህ?”

“ለፋሲካ በግ አርደው ወይም ኣሳርደው አያውቁም?”

“አሳምሬ እንጂ! ኧረ ለቅዱስ ዮሐንስም :- ለመስቀልም፡ ለጥምቀትም! ኧረ ላዘቦት ቀንም!”

“በጉን ገደሉት ወይም አስገደሉት። የሞት እጅ ሆኑ”

“ወይ ጉድ!” አሉ አጋፋሪ የሚሉትን ቢያጡ።

“ቅጠል ሸምጥጠው ሳር በጥሰው ያውቃሉ”

“ቅጠሉም ረገፈ ሳሩም ደረቀ” አሉ አጋፋሪ በንዴት እየተቀበሉት “ህይወት አለፈ። ገዳይ ሆንኩ ፤ የሞት እጅ ሆንኩ። እህል ቢዘሩት ይበቅል ነበር ህይወት ትታደስ ነበር ፤ ግን ስንቅ ሲዘጋጅልኝ ለጭብጦ የተቆላው ኑግ ሞተ ፤ ገደልኩት ወይም አስገደልኩት። የበሶ ገብሱንም እንደዚሁ።

የእንጀራ ጤፉንም እንደዚሁ። ብቻ ምን አለፋህ? እኔ ለመኖር ብዬ አንድ ጉርሻ ባኘከሁ ቁጥር ለሞት ገድዬለታለሁ። አቤት ስንቱን ፈጀሁት!! ወይኔ እንደሻው! ይህ ቶስቷሳ የመንደር ውሻ! ናቅኩት ጠላሁት ስል ፡ ለካስ ታጥቆ ሳገለግለው ኖሬአለሁ። ዋ!!"

ከአጭር ዝምታ በኋላ "አሁን ወደኔ እንመለስ" አሉ አጋፋሪ "እቺን የመቃብር ወሬህን በጭራሽ አልወደድኳትም። አንተ ብታሸንፍ ወደ ሰው ኑሮ ልመለስ እችል የለም? እምልህ ፀሀይ፡ ነፋስ ፡ እህል፡ ጠጅ ፡ የሴት ልጅ ውበትና የወንድ ልጅ ወግ ወዳለበት ኣለም ለመመለስ እችላለሁ?"

"እንዴታ! ብቻ ግራ ጉንዎን ያውሱኝ"

"ይኸውልህ ውሰደው"

ቆሪጥ ያጋፋሪን ግራ ጉን ከገዛ ቀኝ ጉኑ ጋር እያቀናጀ "ጉኔን እያዩ፤ ምናልባት ሌባ እንዳይወስደው" አላቸው

"አይ አቶ ቆሪጥ! ከሬሳ አንሼ ግማሽ ሬሳ ሆኜ እያየኸኝ ጠብቅልኝ ትለኛለህ?"

ቆሪጥ የገዛ ግራ ጉኑን ከቀኝ ጉናቸው ጋር እየገጠመ

"አሁንስ?" አላቸው።

"በል እስቲ ይቅናህ ፡ ወዳጄ"

"አይጠረጠርም!" አለና ቆሪጥ ፡ እንደ ፉከራም እንደቀልድም

"ዘራፍ!

የሆራው ዳኛ ቆሪጥ ዘለቀ!

ሞትን ከተረት የደባለቀ!

ዘራፍ!" ብሎ ሞትን ጉግስ ሊገጥመው በመውጣቱ ላይ እንዳለ--

“ቆይ እስቲ ጐሽ!” አለ አንድ ደስ የሚል ድምፅ። አጋፋሪ ወደ ሰሙበት ዘወር ቢሉ ፡-

አቡነ ተክልዬ ራሳቸው ባንድ እግራቸው እዚያ ቆመዋል

“አንተ ሞክሼ!” አሉ ኣቡነ ተክልዬ

“አቤት ብፁእ ሆይ!”

“አንተ እዚህ ተጐልተህ ቆሪጥ እሚዋጋልህ ስለምን? በል ተነስና አንተው ግጠመው። አገር አታሰድብ”

“ሞቻለሁዋ?”

“ሞቻለሁዋ ይለኛልኮ ደሞ። ይልቅ ተነስ! አሰዳቢ!”

(“ኡኡ! ሽማግሌው ምን ነካቸው?” እያሉ ውስጡን)” ሞቻለሁ አልኩዎ። በጠላ ትንታ ሞትኩ”

“እንኳን በጠላ ትንታ ለምን በጠበል ትንታ አይሆንም? በልኮ ተነሳ!”

“ሞቻለሁ እያልኩዎ!?”

“ታዲያ ብትሞት ምንድነው? ብድግ ብለህ መሄድ ያቅትሀል? በዚህ እድሜህ ሞት ትልቅ ነገር መሆኑ ነው? በል ለዛሬ እንተወው። የሆነው ሆነ። ከተነሳህ በኋላ ትገጥመዋለህ?”

“አፈር አበላው! ብቻ ልነሳ”

ኣቡነ ተክልዬ ወደ ቆሪጥ ዞረው “አንተ መቸስ ሞትን ጉግስ ለመግጠም ከቻልክ ማንንም ብታታልል ግድ የለህም ፤ አደለም? በል አሁን ግራ ጐኑን መልስለት”

ቆሪጥ በዝምታ ያጋፋሪን ግራ ጐናቸውን መለሰላቸውና የገዛ ቀኝ ጐኑን ወሰደ።

አቡነ ተክልዬ እያማተቡ “በስምአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!” ብለው ያጋፋሪን ሬሳ መስቀል ካሳለሙት በኋላ “ተነስ!” አሉት። ኣጋፋሪ ብድግ ሲሉ የሬሳ ሳጥን ክዳኑ ግንባራቸውን መታቸው የተሰማቸው ደስታ! አቡነ ተክልዬ ምንም እንዳልሰሩ ያህል መንገዳቸውን ቀጠሉ ፤ አለፉ።

አጋፋሪ እንደ ተጋደሙ ቆዩ ቆዩና ፤

“ቆሪጥ ፥ በኔ ፋንታ ሞትን ጉግስ ትገጥመው ትፈልጋለህ?” አሉት

“እርስዎ ኣይገጥሙትም?”

“ስራ አጥቼ! እንደሻው ከዚህ የተነሳ ወንዝ እስኪሻገር እንኳን ለጉግሥ ለሽንት ቆም አይልም ልንገርህ”

“ግን'ኮ ኣሁን ሞት ጉግስ ሊገጥምዎት ተዘጋጅቶ ይጠብቃል። መላ መምታት ይኖርብናል”

“እንዴት ያለ መላ?”

“ልብስና መልክ እንለዋወጥና እርስዎን መስዬ ልግጠመው”

“ደግ”

ቆሪጥ ያጋፋሪን መልክ ለብሶ ለጉግስ ሲታጠቅ እሳቸው የገዛ መልካቸውን ከውጭ ሆነው አዩት ፤ የገዛ ሰውነታቸውን በውጭ አይን ተመለከቱትና “አይ መልክ! አይ ቁመና! አይ ሰውነት! አይ ጥላ!” ብለው ካሞጋገሱት በኋላ ፤

“እኔ ምልህ ቆሪጥ” አሉት።

“አቤት አጋፋሪ” ኣለ ጋሻውን እያነሳ

“መልኬን ኣደራ”

“አያስቡ”

“እንግዲህ እኔ መሄዴ ነው”

“ይሂዱ። ከግጥሚያው በኋላ እደርስብዎታለሁ”

“በል ይቅናህ”

“አሜን!” አለና ቆሪ? በታላቅ ድምጽ ጮሆ “ዘራፍ! እንደሻው ሞት ገዳይ!” እያለ እየፎከረ የሬሳ ሳጥኑን ከውስጥ ብርግድ አድርጎት ወጣ።

አጋፋሪ ቀስ ብለው ጭንቅላታቸውን ብቻ ብቅ አርገን ቢመለከቱ!

ሞት ከወዲያ በኩል ጥቁር በጥቁር ለብሶ ጋሻና ጦሩን ጨብጦ፤ ፍንጃል በመሰለ ነጭ ጅብ ላይ ተቀምጧል። አቤት ሲያምርበት! አዬ ግርማው! አይ ኣቀማመጡ! ሞት በዝግታ ወደ አጋፋሪ ገልመጥ ሲል ጊዜ መልኩ ቁርጥ እሳቸውን! በስመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! አጋፋሪ በቅጽበት ጥልቅ ወደ ሳጥናቸው። የፈራች እንሽላሊት ይመስል። አይ! እሳቸው እንኳ ፈርተው አይደለም ፤ ላስብበት ብለው ነው እንጂ።

“እንዴ! ያ ቆሪጥ መልኬን ለሞት ሰጥቶብኝ ይሆን ንዴ? ድሮውንስ ዛር ማመን! ከዛርም ዛር አንካሳ ዛር ፤ እያሉ እያሰቡ ፥ አሁንም ቀስስስስ ብለው አንገታቸውን ብቻ ብቅ አርገው ቢያዩ ፡

ቆሪጥ መልካቸውን እንደለበሰ በጭን በቅሎኣቸወ በጠጂቱ እየጋለበ ይሸሻል ፤ ሞትም ያንኑ መልካቸውን ለብሶ በነጭ ጅብ እየጋለበ ጦሩን ይሰብቃል።

“ዘራፍ! አባ ጎተራ! ሞት አባ ሰብስብ!

ሁሉን በተራ የሚሰበስብ! ዘራፍ!” ብሎ እየፎከረ ወረወረ።

ቆሪጥ መከተ። እፎይ! ......እፎይ? እንደሻው ሲወረውር እንደሻው ሲመክት እንደሻው ተመለከተ እንግዲህ እፎይ የሚለው ማነው? ...

አጋፋሪ ይህንን ሲያስቡ ሞትና ቆሪጥ ተራ ተለዋውጠው ኖሮ ፤ ሞት በነጭ ጅቡ እየሸሸ ፤ ቆሪጥ በጠጂቱ እያሳደደ ወደዚያ ርቀው ሄዱ፤

እንጦጦን ረገጡ፤ ጋራውን ወጡ ፤ አድማስን ተጠጉ። ዘለቁ፤ አድማስን አለፉ ፤ ካጋፋሪ ኣይን ተሰወሩ።

አጋፋሪ የሳጥኑን ጐን ተደግፈው ይህን ሲመለከቱ ቆዩና ፡ እነቆሪጥ ሲሰወሩባቸው ጊዜ ደረታቸውን ከግራ በኩል ሲጐረብጣቸው እንደቆየ ታወቃቸው።

እጃቸውን ሰደው ደባብሰው ከለበሱት የቆሪጥ ቀሚስ ከውስጥ በኩል ከተለጠፈች ትንሽ ኪስ ውስጥ

አንዲት ጭብጥ የማትሞላ ጠጣራ ነገር ኣወጡ። ቢያዩዋት በጣም ትንሽ ግን በጣም ውብ ብርሌ ናት ብሩህ ቅጠልያ ነገር ይዛለች-አፉ እንደ ጠጅ ጋን በጥንቃቄ ታሽጓል።

አጋፋሪ በቀስታ ከፈቱዋት ብርሌይቱን።

እንደገና አዩዋት። ቀስተ ደመና እንኳ ከነህብረ ቀለማቱ የሷን ያህል አያምርም።

ኣሽተቱዋት አቤት መአዛ!!

ቀመስ

ዥው አርገው ጠጡዋት አጋፋሪ እንደሻው ዘብሄረ አዲሳባ። ከጨለጡዋት በኋላ አፋቸውን እያጣጣሙ ፥ መአዛው በትናጋቸው አርጎ ሲሸታቸው እየተደሰቱ “መርዝ ቢሆንስ?” ብለው አሰቡ ፡ በጨረቃዊ ሳቅ እየተንከተከቱ “ቂቂቅ!”

አይችልም! ከፉ ነገር እንደዚህ ደስ ሊል አይችልም!። ግን ትንሽ እንኳ ሳላስብበት ጭልጥ ማድረጌ ምን ይባላል? እያሉ ሲያስቡ

ሆታ ተሰማቸው። ከሩቅ ብዙ ጎረምሶች ዱላቸውን እያማቱ ለቡሄ ሲጨፍሩ ይመስላል። “ዛሬስ በበጋ ሆነንዴ ቡሄው? ሆ!” እያሉ በግማሽ ልብ ሲያስቡ፡ ጉግሰኞቹ ኣሁንም አዞረው ኖሮ ፤ ቆሪጥ በጠጂቱ እየሸሸ

ሞት በጅቡ እያሳደደ ከእንጦጦ አድማስ ወጥተው ወደ አጋፋሪ በኩል ሲጋልቡ

አጋፋሪ ተመልሰው ወደ ሳጥናቸው ጥልቅ!

ታድያ-እንዴ!-- እንዴት ነው ይኸ ነገር? የሳጥኑ እንጨት እንዴት ነው እማይከልላቸው? ጉግሰኞቹ አሁንም ወለል ብለው ይታዩዋቸዋልሳ? ያቺ ብርሌ አይን ከፋች ኖራለችንዴ?

ቆሪጥ ሲሸሽ አድማስን እየታከከ ፡ የተራራዎቹን ጫፍ እየተከተለ አዲሳባን እንዲህ ወዲህ ትቶ ጋለበ ፥ ሽመጠጠ ኤረርን አለፈ ጋለበ ዝቋላን ዘለለ አድማስ ሸሸገው። ሞት ፍንጃል ነጭ ጅቡን እየጋለበ ሲከተል ፤ ዝቋላን እዘላለሁ ሲል ጅቡ ተደናቀፈና ወደቀ፤ ሞት በዝቋላ ቁልቁለት ተንከባለለ። አጋፋሪ ውስጡን በደስታ እየሳቁ ፥

“እሰይ! እንኳን ምነው አቦዬ ጣዲቁ አግኝተውህ በክርን በደቆሱህና ላንበሶቻቸውና ለነብሮቻቸው እራት ባደረጉህ!” እያሉ ሲያስቡ ፥

ያ ቅድም ከሩቅ የሰሙት ሆታ ኣሁን ኣጠገባቸው ደርሶ ተሰማቸው። “ሆያ ሆዬ” ሆኖ ቃላቱ ለየት ያለ ነው። አውራጅ በጐረና ድምጽ ፤

“እዚያ ማዶ” ሲል

“ሞት!” ይላሉ ተቀባዮቹ።

እሱ ኖሯል ኣጋፋሪን ሆታ የተሰማቸው የመሰላቸው።

‘ጣን ይጨሳል

ሞት!

አጋፋሪ

ሞት!

ይደግሳል

ሞት!

እያሉ ብቅ አሉ በምድሩ ውስጥ ለውስጥ ፡ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ትሎች በህብረት እጥፍዘርጋ ፎቀቅ--ጠጋ እያሉ እየጨፈሩ ለአጋፋሪ ተብላ ወደ ተቆፈረው መቃብር ቀረቡ ሆታቸውን እየቀጠሉ፡

ያቺን ድግስ -

ሞት!

ውጩውጩ

ሞት!

በመቃብር

ሞት!

ተገልብጩ

ሞት!

ያች መቃብር

ሞት!

አመለኛ

ሞት!

ያላንድ ሬሳ

ሞት!

ኣታስተኛ

ሞት!

ሆያ ሆዬ ጉዴ! ስጋ ስጋ ይላል ሆዴ!

ሆያ ሆዬ ጉዴ! ስጋ ስጋ ይላል ሆዴ!

ሆያ ሆዬ ጉዴ! ሬሳ ሬሳ ይላል ሆዴ!

ሆያ ሆዬ ጉዴ! ሬሳ ሬሳ ይላል ሆዴ!

ብለው እየተቀበሉ በእልፍ እምአእላፍ የሚቆጠሩ ትሎች ግንባር ቀደም ሆነው ሬሳው ሊጋደም ከነበረበት ስርፉ ደረሰ።

እና ድንገት ዝምታ ሆነ።

"ስጋውስ?" አለ አንዱ ቾኩል ትል

"አጋፋሪ ይጣልላችኋል አልተባልንም ነበር እንዴ?" ብሎ ጨመረ ሌላው ገብጋባ!

"ኸረ ዘራችሁን የሚጥል ይጣለው! ሟርተኞች ጠኔ ይሞረሙራችኋል እንጂ አጋፋሪ እንደሁ አይገኝ! ሸቃባ ትላትል ሁሉ! ኩምታ ይባላችኋል እንጂ ፤ ገና ነኝ እኔ እንደሻው። ገና ገና ገና!" ሲሉ

ትሎቹ በበኩላቸው ሁሉም እኩል መነጋገር ስለጀመሩ ንግግራቸው ታላቅ ማጉረምረም ሆኖ ተሰማ።

ከጥቂት ማጉረምረም በኋላ አንዳንዶቹ ከማጉረምረሙ በላይ ጮክ ብለው "እሽሽሽ! እስቲ ዝም በሉ ኧይ! እንደማመጥ ጎሽ!" ሲሉ ዝምታ ሆነ። እና አንድ በእርጅና የሚንቀጠቀጥ ድምጽ እንዲህ አለ ፥

ፁሙ ፀልዩ ስንላችሁ ቸላ ስትሉን ንሰሀ ግቡ ስንላችሁ ስትስቁብን ፡ በአላት አክብሩ ስንላችሁ ስትጥሱ ፤ ይኸው መአቱን ጀመረዋ! ገና ምኑን አይታችሁ! የከፈተውን ከርስ ሳይሞላው ኣያድርም የተባለውኮ ትእዛዛቱን ስትጠብቁ ነው እንጂ ፤ አለዚያማ" ሲል

የህፃን ትል ድምጽ አቋረጠው

"ይኸው ስጋ!"

ትሎቹም አጋፋሪም ቢመለከቱ፡

ከቁርጭምጭሚቱ ትንሽ ከፍ ብሉ የተቆረጠ እግር እዚያ ተጋድሟል። ጉረምሶቹ ትሎች ያንን እግር ሲሻሙ ፤ ያ በእርጅና የሚንቀጠቀጠው ድምጽ "ተዉ ይኸ እግር አደገኛ ነው" አለ። ሌሎቹ ትሎች ግን ማስጠንቀቂያውን ከምንም ሳይቆጥሩት ያን እግር ወረሩት። አጋፋሪ የገዛ እግሮቻቸውን በእጃቸው ዳሰሱ -

አንድ እግራቸውን ሲያጡ ደነገጡ። "እንደሻው ተበላሸህ!" ሲሉና የቆሪጥን መልክ መልበሳቸውን ሲያስታውሱ እኩል ሆነ። ቢያጤኑት ግን ያ ትሎ፣ የሚሻሙት እግር ሌላ ፤ ያ እሳቸው የሌላቸው እግር። ደግመው እፎይ አሉ ተነፈሱ።

"ወይ ያዲሳባ ተረት!" አለ ያ ደስ የሚል ሳቂታ ድምጽ። ደራሲው ከወረቀቱ ቀና ቢል ኣቡነ ተክልዬ እመቃብሩ አፋፍ ላይ ካጋፋሪ ማዶ ቆመዋል። የሚመለከቱትም ወደ ደራሲው ነው ፡ የሚያናግሩትም እሱን ነው።

"ለቀባሪው አረዱት አነሰና ለሟቹ አረዱት ሆነ 'ንዴ?" አሉ ፡ "ይኸ የትሎቹ ሆያሆዬና የእግሩ ነገር ትንሽ ኣይበዛም? አሉት ደራሲውን በቁጣ ሳይሆን በትዝብት ወይም በሂስ።

ደራሲው በእፍረት አቀረቀረ ፤ በልቡ ይቅርታ ብፁእ ሆይ አለ።

"እኔ ምን ቸገረኝ?" አሉ አቡነ። "ተረት መስማት ስለምወድ ተረትህን አታበላሸው አልኩህ እንጂ።"

"ሌላም ይንገሩኝ ብፁእ ሆይ" አለ ደራሲው በትህትና

"አታብዛ አታንዛዛ። ተረትህን በዚህ ምዕራፍ ትጨርስ እንደሆነ ጨርስ። እኔ እንደሆንኩ ከንግዲህ ተመልሼ በዚህ በኩል አላልፍልህም ልባርግ ፡ ተረት ውስጥ ከመመላለስ ሌላ ስራ የለኝም መስሎህል እንዴ?"

"ይቅርታ ብፁእ ሆይ" አለ ደራሲው በልቡ።

“ምነው ሁላችሁም ብፁእ ሆይ ባትሉኝ! እንዴት እንደሚሰለች ባወቃችሁ!” እያሉ አቡነ ወደ ኢጋፋሪ በኩል ዞሩና።

“እንደሻው ፡ አንት ፈሪ ፍርፋሪ ምድጃ ቆፋሪ!” አሉዋቸው “ሞትን አንተው ራስህ ግጠመው ስልህ ሺ አላልከኝም ነበር?”

“ሳይሆንልኝ ቀረ ብፁእ ሆይ ፡ አይቀየሙኝ”

“ምን እቀየምሀለሁ? ታስቀኛለህ እንጂ”

“ምኔ ነው ሚያስቅዎ ብፁእ”

“ሞት መፍራትህ ነዋ! ደሞ ብፁእ አትበለኝ”

“ታዲያ ምን ልበልዎ ፡ ብፁእ?”

“ብፁእ አትበለኝ አልኩህ!”

“ታዲያ ምን ልበልዎ በ”አሉና አፋቸውን ያዙ ኢጋፋሪ

“ሞክሼ በለኝ”

“እሺ ሞክሼ ሆይ”

“ሞክሼ ሆይ! ምነው እንደ ሰው ብታናግረኝ ጃል?”

“ቅዱስ ነዎ ብዬ ነዋ”

“እሱማ የሰው ልጅ ሁሉ ቅዱስ ነው አንተም ጭምር።”

“ቅዱስ እንደሻው ቂቂቂቅ!”

“ልክ ነውና! ቅዱስ እንደሻው ነህና። ይልቅ ስማኝ ሞትኮ ምንም አይደለም። ከሰማይ ተዘራን ፥እምድር በቀልን ፡ መኸር ሲደርስ ወደ ሰማይ እንሰበሰባለን። ይኸ ምኑ ያስፈራል?”

“እሱስ አያስፈራም ፤ ግን እኔ መሰብሰብ ይቅርብኝ። እንደ ቃርሚያ ቁጠሩኝና ናቅ አርጋችሁ ተዉኝ።

እሽ? ጐሽ የኔ ሞክሼዬ! እኔ'ኮ አንቱን ስወድሁ! ምናለ ከሞት እንዳመልጥ ብትረዱኝ? ያገር ልጅ ሲረዳዳ ነው ጥሩ። ይበሉ ይንገሩኝ ፡ ከሞት ማምለጫው በየት ነው?”

“ምስጢር ነዋ”

“እሺ ይጠቁሙኝ ኣይንገሩኝ። በእጅዎ ያረመልክቱኝ። በሚወዱዋት ድንግል እመቤታችን ይዤዎታለሁ።”

አቡነ ተክልዬ ሳቃቸው አሸነፋቸውና መቃብሩ አፋፍ ላይ ቁጭ አሉ።

“አይ ያንተ ነገር! በቃኝ ማለት የለችም እ?”

“ቢበቃኝኮ በቃኝ እል ነበር። ግን መኖርን የመሰለ ነገር እንዴት ብዬ በቃኝ ልበል? እንዲያው ሰሞትልሁ የኔ ሞክሼዬ ፡ አፈር ስሆንልሁ! ትንሽ ፍንጭ ትበቃኛለች። እቺን እምታህል ፍንጭ። ሞትን ማምለጫ በየት በኩል ነው?”

አቡነ ሳቃቸውን በስንት መከራ ከገቱ በኋላ ፡

“ሳትሞት ወደ ሰማይ ቤት ልውሰድህ” አሉ።

“የብርሀን ሰረገላ አለኝ። በሱ እንሄዳለን ፡ እሽ?”

“እሱስ ጥሩ ነበር” አሉ አጋፋሪ። “ብቻ”

“አይዞህ ተናገር”

“እንደኔ እንደኔስ ወደ አዲሳባዬ ብመለስ በወደድኩ”

“ከሰማይ ቤት ኣዲሳባ ይሻልሀል?”

“አስር እጅ!” አሉ አጋፋሪ። ያዲሳባይቱ አድባር ይህን ሰምታ እልል አለች ፤ የገደል ማሚቶ እልልታውን ተቀበለች ፤ ምድረ ሀበሻ በእልልታ አስተጋባጭ

“ስማ ሞክሼ” አሉ አቡነ እልልታውን ሳይሰሙ “ሰማይ ቤትኮ ራብ የለ ፤ ብርድ የለ ፤ ሀሩር የለ ፤ እጦት የለ ፤ ድካም የለ ፤ በሽታ የለ ፤ ምቀኝነት የለ”

“አውቃለሁ

“ታዲያ ምንድነው?”

አጋፋሪ እንደ ማፈር አሉና “በጆሮዎ ልንገርዎ?” ኣሉ

“ብቻችንን ነን'ኮ”

“ቢሆንም”

ኣቡነ ባንዱ እግራቸው ነጥረው መቃብሩን ተሻገሩና ወደ አጋፋሪ ጐንበስ አሉ። አጋፋሪ በሹክሹክታ ነገሩዋቸው

አቡነ በመገረም “በስድሳ ስድስት አመትህ” ሲሉዋቸው ፤

“እና ስድሳ ስድስት አመት ምንድናት?” አሉ አጋፋሪ ዜማ እየለወጠ ፡ “ይልቅ ይስሙኝ እስቲ ሞክሸዬ። ምናልባት ሞትን ምታባርር ትንሽ ድግምት መሳይ አያውቁም??

አቡነ ተክልዬ በሳቅ እየተንከተከቱ ሆዳቸውን ይዘው ቁጭ አለ።

አጋፋሪ ሳቃቸውን እስኪጨርሱ ጠበቁና ፤ ትንሽ ልጅ የሚለማመጥ በሚመስል ዜማ ፡

“ወይም ከሞት ምትሸሽግ እፀ መሰውር መሳይ ቅጠል?” አሉዋቸው። ኣቡነ ሳቃቸው አላናግር አላቸው።

“ወይም ምናልባት ምድር ላይ አንድ ስርፋ ይኖር ይሆን ሞት እማይደርስበት? ምናለ ፍንጭ ብጤ ቢሰጡኝ? ሞክሼነታችን ለመቼ ነው? በዚያም ላይ ያገር ልጆች!”

“ይልቅ እያሳቅህ የመጣሁበትን ቁም ነገር አስረሳኸኝ” አሉ አቡነ ፡ “ቆሪጥ ማን እንደሆነ አውቀህል?”

“መጀመሪያ ሳየው እርስዎን መስሎኝ ነበር”

አቡነ ሳቃቸው ድንገት ጠፋ። ሲያስቡ ቆዩና “እኔን ይመስላል ... እኔ የሰራሁትን ያፈርሳል............ የተከልኩትን ይነቅላል.......”.

“እና ዝም ይሉታል እንዴ?”

“ታዲያ ምን ላርገው? ሰውኮ ራሱም ፈራሽ ነው ስራወም ፈራሽ ነው። በምድር ላይ ቋሚ ነገር የለም። ሁሉም ሀላፊ ነው።”

“ምን ሊያፈርስ ነው እንግዲህ?” አሉ አጋፋሪ

“ኦዚህ አካባቢ የተከልኩዋቸው ደብረ ሊባኖስና የይኩኖ አምላክ ዙፋን ናቸው። ወይ አንዱን ወይ ሁለቱን ሊያፈርስ ይሆናል። ያ የሚያፈርሰው ነገር ግን ካንተ ጋር የተያያዘ ነው። አለዚያ ላንተ እኔን መስሎ አይታይህም ነበር”

“እንዴት ከኔ ጋር ይያያዛል?”

“እንጃ? ጊዜ ሲደርስ እናውቀዋለና”

አጋፋሪ ለራሳቸው እያሰቡ “ታዲያ የሰሩትን ሲያፈርስ እንዴት አይከለክሉትም?” ኣሉ። የሙጥኝ የማለት ያህል።

“ጊዜው ካልደረሰ አያፈርሰውም'ኮ። በዚያ ላይ ደሞ አስታውስ ፡ እኔም የሱ አፍራሽ ነኝ። ስምንተኛው ሺ አልፎ አለም እንደገና ስትታደስ ያኔ ደሞ መስራት መትከል የሱ ተራ ፤ ማፍረስ መንቀል የኔ ተራ ይሆናል። ”

“አለም እንደገና ትታደላለች?” አሉ አጋፋሪ። አይናቸው በተስፋ እየተቁለጨለጨ።

“አዎን”

“እኛ እንደገና እንኖራለን?”

አቡነ አልተናገሩም።

“ስማ” አሉ አቡነ ፥ “የቆሪጥ መምጫው ፡ የኔ መሄጃዬ ደረሰ። ከንግዲህ በምንም ሰአት ቢሆን ፥ “ሞክሼዉዉዉ!!!!? ብዬ ስጠራህ-- ሶስትዬ ስጠራህ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ እያልክ ወደ ስድስቱም አቅጣጫ እንድታማትብ”

“ስድስቱም አቅጣጫ?”

“ቀኝ ግራ ፊት ኋላ ላይ ታች

“ገባኝ”

“ከዚያ በተቻለ ፍጥነት ለብቻህ ሁንና በገናህን አንስተህ ደርድር። ቅኝቱ ውስጥ መልእክት እተውልህለሁ። በል ሄድኩ፥ ደህና ሁን” አሉና አቡነ ተክልዬ አጋፋሪን በመነኲሳት ደምብ ትከሻና ትከሻቸውን ስመዋቸው መስቀላቸውን አሳልመዋቸው ሊሂዱ ሲሉ ፥ አጋፋሪ

“እኔ ምልዎት ፥ ሞክሼ” አሉዋቸው።

“ወይ”

“የሞት መድኃኒት ሳያመላክቱኝ ዝም ብለው መሄድዎ ነው?”

አቡነ ኣልፈው ከሄዱ በኋላ ሁሉ ሳቃቸው ይሰማ ነበር ፡፡

ገና የኣቡነ ሳቅ ጨርሶ ሳይጠፉ ቆሪጥ ባንድ እግሩ እየነጠረ መጣና ፡

“ጉድ ተሰራን ፡ ኣጋፋሪ” አላቸው።

“ምነው?”

“ሞትን ገደልኩት”

አጋፋሪ ጆሮአቸውን ሊያምኑትም ፈለጉ ፤ እንዳያምኑትም ፈሩና ፡ “ምን አልክ?” አሉ።

“ሞትን ገደልኩት። ሆነ ብዬ ሳይሆን?

“ገደልከው ሞተ?”

“አዎን”

“እንዲያው ሙትት ሙትት?”

“እንዲያው ድብን ድርቅ!” አለ ቆሪጥ

አጋፋሪ እየሳቁ ተነስተው ቆሪጥን አቅፈው ሳሙት።

“ተመስገን መድህኒአለም” አለ ቆ

“ምን አልክ?” አሉ አጋፋሪ ፡ ሳቃቸውን እየሳቁና አይናቸውን እየከፈቱ።

“ተመስገን መድህኒአለም አልኩዋ!” ኣሉዋቸው ወዳጃቸው ደጃዝማች ዳኛቸው ፡ “እኔማ ሞትክ ብዬ ተስፋ ቆርጬ ነበር።

ኣጋፋሪ አይናቸውን መልሰው ዘጉ ፤ አሰቡ። መልሰው አይናቸውን ከፈቱ። ደጃዝማች ዳኛቸው ከላይ ወደ ታች ያዩዋቸዋል እንባ ባዘሉ አይኖች። እሳቸው ወለሉ ላይ ተንጋለዋል።

“ምን ሆንኩ?” አሉ አጋፋሪ

“ወንድሜ ሲያቀብጠኝ በግድ ጠላ ካልጠባህ ብዬ ይገፍህ?”

“ትን አለኝ?” አሉ አጋፋሪ በፈገግታ

“እህሳ!”

“ታድያ እኔ እንደሻው ነኝ በትንታ እምሞት? እንኳን ትንታ ነጐድጓድ ኣይገድለኝም ልንገርህ። ገና ነኝ እኔ እንደሻው ገናገና ገና” እያሉ ተነስተው

ጓደኞቻቸወን ተሰናብተው በጭን በቅሎኣቸው ተቀምጠው የሳምንት ስንቅ የተጫነ በቅሎኣቸውን አስከትለው ወደ እንጦጦዋቸው አመሩ።

መጋቢት ፥ 1969

# አምስት ስድስት ሰባት

የዛሬን አያርገውና ፡ አቶ በርሱፈቃድ በጉርምስናቸው ዘመን የሶስት ሰው ምሳ አይመልሳቸውም ነበር። ሲያርሱም ያንኑ ያህል ነበር። ግዙፍ ደንደሳም በመሆናቸው ሁለት ሰው ታግሎ አይጥላቸውም ነበር።

ጐጆ ከወጡ በኋላ ፈጣሪ ድህነትና ፍሬን አጣምሮ ሰጣቸው ፤ አምስት ልጅ ወለዱ። ሚስታቸው በተፈጥሮ ለስላሳ ደካማ በመሆናቸው ፡ አምስተኛዋን ልጅ ከወለዱ በኋላ በሽታ ኣደረባቸው ፤ ለጉልጓሎ ለአረም፡ ለአጨዳ መውጣት አቃታቸው ፤ ውሀ መቅዳትና ወፍጮም እያሽነፋቸው ስለሄደ የመጀመሪያዋ ልጃቸው ፋናዬ በስምንት አመትዋ በገንቦ ውሀ መቅዳት ፤ በልጅ አቅምዋ እህል መፍጨት ግድ ሆነባት። በናትዋ የወጣች ልስልስ ነገር፥ ከእንዝርትና ከወስፌ የከበደ ማንሳት የማትችል ሰንበሌጥ መሳይ ነች ፤ በዚያ ላይ እስክትጠግብ አትበላም። በምን ጉልበትዋ ትቻለው ወሃውን ወፍጮውን እንጨት ለቀማውን?

በእህል እጦትም በሴት ጉልበት እጦትም ቤተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ ቆሎ ወይም ንፍሮ ብቻ ይበላል። ቢቸግራቸው አቶ በርሱፈቃድ ወንድ ልጅ የማይሰራውን ሰሩ፤ ሌሊት እየተነሱ እህል መፍጨት ጀመሩ። ሲያስቡት ፥ እጄም ወገቤም ሞፈር ለምደዋልና ከእፍረቱ በስተቀር ወፍጮ ምንም አያስቸግርም መስሏቸው ነበር። አልሆነም፤ እንዳሰቡት አልሆነም። መዳፋቸውም ወገባቸውም ስላልቻለ ጥቂት ፈጭተው ተመልሰው ተኙ። ግን የማይለመድ የለም ፤ ወፍጮውን ለመዱት። በበአል ቀን እየወጡ

እንጬት ለቅመው በማታ ጨለማ እያመጡ ፋናዬን ከእንጬት ለቀማውም አሳረፉዋት እንጂ እስካሁን ሞታ ነበር።

አርብ እለት ማለዳ ተነስተው ሞፈር ቀምበራቸውን ተሸከመው የቀራቸውን አንድ በሬና የጐረቤታቸውን የወይዘሮ ሹምነሽን በሬ እየነዱ ወደ ወይዘሮ ሹምነሽ እርሻ ሄደው ጠመዱ። አንድ ቀን የወይዘሮ ሹምነሽን መሬት ፤ ሁለት ቀን የራሳቸውን መሬት ነው የሚያርሱት። ይህን በሚዋዋሉበት ጊዜ አቶ በርሱፈቃድ ፥

"አንዱ በሬ የኔ ፡ ጉልበ የኔ ፤ ሞፈር ቀንበሩ የኔ ፤ ታዲያ አልተጐዳሁም?" ሲሉዋቸው ፡ ወይዘሮ ሹምነሽ መልሰው እንዲህ አሉ፡

"አዬ! እንዲህ ከከብት ባለቀበት ጊዜ ይህን አግኝተው ተጐዳሁ ይላሉ? አሁን ለልጆችዎና ለጉርብትናዎ ብዬ ነው እንጂ አንድ ቀን ለኔ አንድ ቀን ለራሱ የሚያርስ አጣለሁ? እንዲያውስ ሁለት ቀን ለኔ አንድ ቀን ላንተ ብለው እጅ ነስቶ የሚቀበለኝ አጣለሁ? ለዚህ ነው እንጂ እርስዎ ከሚመጡብኝ እኔ እናመጣብዎት አልነበረም?"

አቶ በርሱፈቃድ አንገታቸውን ደፉ ፤

"እሱስ ነው" አሉ "እርስዎ አራት ጥማድ በሬ እያሳረሱ እንደኔ አልተቸገሩምና ማለቴ ነው እንጂ።"

"አዬ አያ በርሱፈቃድ! እርስዎም እንዲህ ይላሉ? ባሌ ከሞተ ወዲህ ልጅ የለኝ ምን የለኝ። ብቻየን ባዶ ቤት ውስጥ ጥቅልል ብዬ እየተኛሁ ፤ አልተቸገርሽም ይሉኛል? አሁን እትዬ ዝማም እርስዎ ቢኖሩዋቸው ፋናዬ ብትኖራቸው ቤት ይውላሉ እንጂ እንደኔ ብቻቸውን ቢሆኑ ምን ይውጣቸው ኖሯል? ብታመም እንኳ ውሀ የሚያጠጣኝ የለኝ።"

"ምነው እኔ አምስት ልጅ አለኝ። አንዱን አይወስዱም?"

“እዚያ ቆላ ያለው ያጐቴ ልጅ ከፍቶት ልጄን እንድታሳድጊያት ልልክልሽ ነው ብሎ ልኮብኛል እንጂ ቀደም ብለው ቢነግሩኝማ ይሆን ነበር። ”

አይ እፍረት! አይ ኩምታ! አቶ በርሱፈቃድ አሁንም አንገታቸውን ደፉ። ..........

ያቺን ሰዓት እያስታወሱ “ወይዘሮ ሹምነሽ በሬዬን አልሰጥም ቢሉ ኖሮ ወይም አስቀድመው ከሌላ ሰው ተዋውለው ቢሆኝ ኖሮ ምን እሆን ነበር? እጄን ኣጣምሬ ቁጭ? ሞት መጥቶ ልጆቼንም ሚስቴንም እኔንም አንድ በአንድ እስኪበላን ቁጭ? በስመአብ ወወልድ!” ይህን እያሰቡ ሲያርሱ ፡ በባዶ ሆድ ላይ ሀሳብ ስራቸውን አስረስቷቸው እርፉን በቅጡ ሳይጨብጡ ቀርተው ኖሮ ማረሻው የበሬውን ሰኰና ወጋባቸው። ደሙን ሲያዩ ኣዘኑለት ፡ አቅፈው ሊያባብሱት አሰኛቸው በሬውን በንዴት ገረፉት በጅራፋቸው የባሰውን አሳዘናቸው ያ የሚወዱት በሬያቸው የሥራ ጓደኛቸው የፀሐይ ቃጠሎን የሚጋራቸው አርሶ የሚያበላቸው የመጨረሻ ተስፋቸው ጅራፍ ሲያወርዱበት ትእግስቱ እማያልቅበት።

“ሆድ ብሶኝ ነው ጨንቆኝ ነው ርቦኝ ነው ኣትቀየመኝ ሲሳይ ወዳጄ ፤ የመጨረሻ ወዳጄ” ባሉት ፤ የበሬ ቋንቋ ባወቁና የልባቸውን በነገሩት። ይኸ የስሜትና የሀሳብ ጕርፍ የጤና ሰላልመሰላቸው ሌላ ፍርሀት ያዛቸው። “ያበድኩ እንደሆነ ወይ የታመምኩ እንደሆነ ልጆቼን ምን ይውጣቸዋል? ልጆቼን ፡ ኰሳሳ ልጆቼን ፡ ፍሬዎቼን አጥንቶቼን ፥ አጥንት ሆነው የቀሩ ልጆቼን! እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ! አውጣኝ። ከዚህ ጭንቅ ሰውረኝ። ከልጆቼ መማቀቅ እግዚኦ ሞቴን ሰጠኝና ልጆቼን አብላልኝ አንተ ፈጣሪ!”

ይኸ ሁሉ ነብሳቸውን እያስጨነቀ እሳቸው የሲሳይን ሰኮና አንስተው አዩ። ክፉኛ ተወግቷል። ምናልባት ሳምንት ሙሉ ሊያርስ አይችልም ይሆናል። በሬዎቹንፈቱ፤ እርፍና ሞፈሩን ተሸክመው ወደ ቤት ሄዱ።

ከቤታቸው ኋላ ያለው ዋንዛ ስር ሁለተኛው ልጃቸው ወርቁ ቁጭ ብሏል። ከአምስት ዓመት በፊት ሶስት ጥማድ በሬ በነበራቸው ዘመን በጥጋብ ዓመት ሲወለድ ድቡልቡል ዱባ ልጅ ነበር። እሱማ እንዳባቱ ወፍራም ጉልበታም ብርቱ ሊሆን ነበር የተወለደው ድህነት ቤታቸው ገብታ ፤ ከስድስት አምስቱን በሬ ጨርሳ ፤ አሥራ ስድስቱንም በጎቻቸውን አንድ ባንድ አስሽጣ ፤ ቀስ በቀስ ሁሉን ነገር ውጣ ፤ ይኸው ወርቁን ልጃቸውን ሳይቀር ውፍረቱን ደሙን ምጥጥ አድርጋ አጥንትና ዓይን ብቻ አስቀርታ ጉድ ሰራቻቸው እንጂ።

ወርቁ መሬቱን በእንጨት እየጫረ በዝግታ ያለቅሳል።

"ምን ሆንክ?" አሉት።

"እማማ ሹምነሽ ናቸው" አለ።

"ምን አረጉህ ወይዘሮ ሹምነሽ?" አሉት።

"ልላክህ ከእማማ ወለተ ሃይማኖት ቤት ሰፌድ አምጣልኝ አሉኝ። እቺ ምራቅ ሳትደርቅ ሮጠህ ያመጣህልኝ እንደሆነ እንጀራ በጨው እሰጥሀለሁ አሉኝ። ሮጬ አይመጣሁላቸው ምራቋ ሳትደርቅ። ደርቃለች ኣሉና ከለከሉኝ። አልደረቀችም! ውሸታቸውን ነው አባብዬ ፤ አልደረቀችም! እንጀራዬን ከለከሉኝ።"

አቶ በርሱፈቃድ ከማዘናቸው የተነሳ ቆመው ቀሩ። በሆዳቸው ለፈጣሪ አቤት ኣሉ። ልጃቸው እንባቸውን እንዳያይ "በል ተነስ ቤት ግባ" አሉት። ተነስቶ ገባ።

የተሸከሙትን አውርደው በልጃቸው ቦታ ተተክተው ቁጭ ብለው አለቀሱ።

"የማበላቸውን ከልክለህ ልጆች የሰጠኸኝ ምነው?" አሉት ፈጣሪን።

********************

ህማማት ፡

አባ ወልደማርያም ንሰሀ ሲሰሙ ውለው ዘጠኝ ሰዓት አልፎ ህዝበ ክርስቲያን ወደ የቤቱ ሲሄድ ወደኋላ ቀርተው ለብቻቸው ሲፀልዩ ሲሰግዱ ቆይተው ወደ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ቆሎ ለመቅመስ ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥተው በመቃብሩ በኩል ሲያልፉ አዩት ራቁቱን ባርኔጣ አድርጎ መቃብር ድንጋይ ላይ ወጥቶ ሲቆም። ፊቱ ወደዚያ ነው። ረዥም ኣርባ ቅልጥም ቀጭን እንደ ጅማት። እንደሚሰብክ መምህር እጆቹን ዘርግቶ በልዝብ ድምጽ እንዲህ አለ ፤

"አምስት ስድስት ሰባት! ስሙኝ። ስሙኝ እናንት ሙታን ፤ ልንገራችሁ የማይነገር ለህያዋን። ከወዲያኛው አገር ሰይጣንን አይታችሁታል? አላያችሁትም። እዚህ ትታችሁት ሄዳችሁ እዚያ እንዴት ታገኙታላችሁ? እዚሁ ነው ከኛ ጋር ይኖራል። አምስት ስድስት ሰባት! ሰይጣን ማለት ጉተራ ነው ፤ ስልቻ ነው። የማይሞላ ጉድ ነው። ሰይጣን ማለት ሆደ ነው።

"አምስት ስድስት ሰባት ፤ አምስት ልጅ ሁለት እናት አባት። ሰይጣን ከእባብ ተዋህደ ሄዋንን አሳሳተ፣ ኣሳተ። ከእፀበለስ ተዋህደ፤ ሄዋን ሆድ ገባ። ከሆድዋ ተዋህደ ለልጆችዋ ተረፈ። ሰይጣን ሲኦል ወረደ ማለት ወደ ሆድ ወረደ ማለት ነው። ከዚያስ? ከዚያማ ጭለማ ውስጥ ቁጭ ብሎ ይገዛን ያስሰግደን ጀመር። አምስት ስድስት ሰባት! ቀኑን ሙሉ ስንሰራ ስንለፋ ስንዋሽ ስናስመስል ለምን? ለእንጀራ። ለማን? ለሰይጣን ሆድ። ሆድ ይኸ ሆድ ይኸ ጉተራ ፤ ይኸ ጭለማ የሰይጣን ቤት መኖሪያ። ሰው ከተወለደ እስኪሞት ተራራ ያህል እህል ይበላ። አይሞላ ታድያ ያ ሆዱ ያ ጉዱ። አይሞላም ሰይጣን ነው። ሆድ! ሆድ! ሆድ! ብሎ እየጮኸ ሆዱን በእጁ ደጋግሞ ሲፀፋው ተሰማቸዩ አባ ወልደማርያም።

"አምስት ስድስት ሰባት! አምስት ልጅ ፤ ስድስት እናት ፤ ሰባት አባት። እንግዲህ ሰሞኑን ስለ ክርስቶስ ስቅለት ትሰማላችሁ። ግን ማን ነው። ሰው

ሆኖ ያልተሰቀለ? ማነው በልጁ ለቅሶ ያልተቸነከረ? ማነው በሚስቱ ሞት ያልተቀበረ? ደጋግሞ ሊነሳ ደጋግሞ ያልተቀበረ ማነው? አምስት ስድስት ሰባት! እሳት። ገሀነም ትገባላችሁ ብለው ያስፈራሩናል። የት ነው ያለነውና ነው? ገሀነም አይደለም?! ኧረ ተው ኤድያ!" ብሎ ዘረ።

ዓይኖቹ በእብደት ደንግጠው እንደደነገጡ ቀርተዋል። ያስደነግጣሉ። እብዱ አባ ወልደማርያምን አያቸውና ከድንጋዩ ወርዶ ወደሳቸው መጣ። ቀጭን አጥንታም ረዥም ነው። ለሁለት ቢታጠፍ እሳቸውን ያህላል።

"ሰላም ለከ። ህማማት ነውና የይሁዳን ታሪክ ልንገርህ" አላቸው "አምስት ስድስት ሰባት!

"ሰማይን አንጋጠው ቢያዩት ደመና አጥቶ ራቁቱን ቀረና ፤ በፀሎት ቢጨምቁት ጠብ አልል አለና ፤ ምድር ጓጉታ ተነቃቅታ ደርቃ ቀረችና ፡ የይሁዳም በሬዎች አንድ በአንድ ከዱትና ፤ ታማኙ አልሞት ባዩ ጀግናው ሲሳይ ብቻ ቀረ። ቀንበር ሊሸከም ሞፈር ሊጎትት ኣብሮት ሊሠራ እስከመጨረሻ። አምስት ስድስት ሰባት! ይሁዳ ግን ሰው ነውና ፤ ከሀዲ ነውና ፤ በሬውን ሊሸጠው ተነሳ። ገዢ ታጣ። እንግዲያው ና ሲሳይ የመጨረሻ ወዳጄ ዘመዴ ፤ ወደ ጓሮ እንሂድ ልንገርህ ለብቻህ አለና ወሰደው። አምስት ስድስት ሰባት! በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! አለና የመጨረሻዪቱን ምስጢር በስለት ነገረው። እርድ! በሬው ከሃዘኑ የተነሳ ምንም አላለ። በዝምታ ነብሱን ሰጠ። ፀሀይ ይህን አይታ በእፍረት ፊትዋን ልትሸሽግ ዘወር ብትል ደመና አጣች ፣ ደም ኣለቀሰች።

"አረድኩት ፤ ገፈፍኩት ፤ ብልቱን አወጣሁት። ጠብሰን ቀቅለን በላነው ሲሳይን የመጨረሻ ወዳጃችንን። ወጥ እንዳይሆን እንጀራ የለን ፤ ቋንጣ እንዳይሆን ቶሎ ጨረስነው። በላሁት ሲሳይን ዘመዴን። ለሆድ ለሰይጣን ሰዋሁት።

"ታዲያ ይሁዳ ከዳተኛ ነው ይላሉ። የኔን ታሪክ ያላወቁ። ይሁዳ እንኳ ተፀፀተ ተሰቀለ ዕዳውን ከፈለ። እኔ ግን! እኔ ግን! እኔ ግን!" ብሎ ራሱን

ይዞ ጮኸ። “ወየው ወየው ወየው! ወይኔ ዘመዴን ወይኔ ወዳጄን ወይኔ ሲሳዬን ወይኔ ወይኔ!” እያለ እየተወዘወዘ የመርዶ የቀብር ለቅሶ አለቀሰ። ከዚያ ለቅሶውን ድንገት አቋርጦ ካጠገባቸው ትልቅ ድንጋይ አነሳ። ተንበረከከ። ድንጋዩን ትከሻው ላይ አኖረ።

“ማረኝ አንተ የዳዊት ልጅ ፤ ይቅር በሉኝ አባ” አላቸው

“እግዚኣብሔር ይቅር ይበልህ።

“አልፈልግም የሱን ይቅርታ!” ብሎ ተነስቶ በንዴት ድንጋዩን ወደዛ ወረወረው። “የተበደለ ምን ይቅርታ ያስፈልገዋል? ሰው በመሆንዎ ይቅርታ ለመንኩ እንጂ ፈጣሪን ይቅርታ እለምናለሁ? እሱማ ሊከሰስ ይገባዋል” ብሎ እጆቹን አንስቶ ለሙታን መናገር ጀመረ እብዱ ሰውዬ።

“አምስት ስድስት ሰባት! ንገሩልኝ ታገኙት እንደሆን። አበላቸው እህል ከልክለህ አምስት ልጆች የሰጠኸኝ ምነው? ብሎሃል በሉት። አምስት ልጅ ተሰብስቦ አብሮ ሲውል አንዲት ሳቅ ብቅ ሳትል ቀኑ መምሸቱ ምነው? ብሎሃል በሉት። ልጆቼ ኣንዲት ቀን እንኳ ኩኩሉ ሳይጫወቱ ማለቃቸው ምነው? ሚስቴንም ልጆቼንም አንድ በአንድ ስቀብር ዝም ብለህ ማየትህ ምነው? ብሎሃል በሉት። የፍርድ ቀን ቢመጣ የሚፈረድበት ማነው? ብሎሃል በርሱፈቃድ በሉት። የፍርድ ቀን ቢመጣ የሚፈረድበት ማነው? ብሎሃል በርሱፈቃድ በሉት። ኣምስት ስድስት ሰባት! የፍርድ ቀን ቢመጣ--”

ልስልስ ባለ ሩኅሩኅ ድምፅ “ምነው አለቀሱ አባ?” ሲላቸው ዓይናቸውን ከፈቱ። በነገሩ ምሬት በሥቃዩ ብዛት ዓይናቸውን ዘግተው ሲያዝኑ ቆይተዋል። ሲያዩት ጊዜ ላዩ የነበረው የእብደት ድንጋጤ የለም። ሥቃይ ሀዘን ነው መላ ፊቱ ሲያዩት። አንጀት የሚበላ ሥቃይ ሀዘን።

“ምን ሆኑ አባ?” አላቸው አዝኖላቸው። ፊቱላይ የሰፈረው ሀዘን ፊታቸው ላይም ታይቶት ይሆን?

"ምንም አልሆንኩም ልጄ ፤ ምንም አልሆንኩም። ደህና ነኝ" እያሉ እንባቸውን ጠረጉ። ማልቀሳቸውን አላወቁም ነበር።

"ለኔ ነው ያለቀሱልኝ?"

"አዎን ልጄ ፤ እውነትም ተሰቅለሃል። ግን አብሮት የተሰቀለ በቀኙ ይቀመጣል ፤ አይዞህ።"

ድንገት ቁጭ አለና ጉልበቱን አቅፎ ራሱን ደፋ። ተንበረከኩ አጠገቡ። "ምን ሆንክ ልጄ?"

"እርቃነ ሥጋዬን። አጠገብዎ ቆሜ። ይቅርታ ኣባ። ይለፉ ይሂዱ።"

አባ ተነሱ። አርባ ጊዜ የተጣፈ ቡትቶ ካባቸውን አውልቀው አለበሱት።


አይዞህ ልጄ። ከልብሱ ስር ሁላችንም እርቃነ ሥጋችንን ነን። በል ተነስ እንሂድ"

ጥቂት እርምጃ እንደሄዱ "ትንሽ አረፍ እንበል ፡ አባ? የፀሐይዋ ሙቀት ደስ ይላል" አላቸው። ሥፍራው ግን የምሽት ጥላ ሰፍኖበታል። "እስቲ እዚች አጋድሙኝ። እንደሱ! አይ ኣባ! እንዴት ደግ ነዎት! ለመሆኑ ሰው ነዎት? ዓይኑን ዘጋ። "........ ይግቡ እንጂ። ኧረ ይግቡ! ቤት ለንግዳ" አለ ዐይኑን እንደዘጋ ፋናዬ፥ ንሺ ውሀ ለእግር አምጪ። አባ ደክሟቸዋል ከሩቅ ነው የመጣነው።" ዓይኑን ከፈተ። "ወርቁ! ኧረ ወርቁ!! ሲጠሩህ አትሰማም? ከብቶቹ ሁሉ ገብተዋል? ለነሲሳይ ጭድ ሰጠሀቸው? ጎሽ የኔ እንበሳ። ና በል ያባን ጉልበት ሳም። መርቁኝ በላቸው። እናትህን ጠላ መሳይ አምጪልን በላት........ወርቁ! በቃ ጫጫታ ፥ ግቡ ጨልሟል በላቸው ልጆቹን.... ህልም ይፈታሉ ኣባ? ኧረ የገብሬል ያለህ! ምንኛ ክፉ ህልም አሳየኝ!? ረሀብ ገብቶ ያለኝን ጨርሼ ሁሉ ሞቶ ብቻዬን ቀርቼ....... ረሀብ መቸስ ጥጋብ ማለት ነው። ሰው ሲሞት ደስ ይለዋል ማለት ነው....

ግን እርስዎ ምን ይመስልዎታል እንዲህ ዓይነት ህልም......ህልም..... ህልም......" ሰውየው በዚያው ቀረ።

በርሱ ፈቃድ አለፈለት ፤ አለፈ።

1967



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ፋሺስት ኢጣሊያ ሀገራችንን በወረረበት 1927 ዓ.ም ገደማ ተፈጥረው የጥበቡን ከተማ በስራቸው ካስጌጡ ኢትዮጵያውያን መሃል አንዱ ደራሲ ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ነው። ሚያዚያ 27/1928 አድዋ አውራጃ ርባ ገረድ ከምትባል ስፍራ ከአቶ ገብረ እግዚአብሔርና ወ/ሮ መዓዛ ተወልደመድህን ከተወለዱት 11 ልጆች 7ኛ ሆኖ የተወለደው ስብሐት አድጎ የአንድ የአጭር ልቦለዶች ስብስብና የሦስት መካከለኛ ልቦለዶች "አምስት ስድስት ሰባት"፣"ሌቱም አይነጋልኝ"፣ "ትኩሳት"፣ "ሰባተኛው መልአክ" ደራሲ ብቻ ሳይሆን ከ30 ለበለጡ ዓመታት ጋዜጠኛም ነበሩ።

ጋዜጠኛው ስብሐት በ"አዲስ ዘመን" ጋዜጣ፣ "ሄራልድ" ጋዜጣ፣ "መነን" መጽሔት ፣ "Addis Reporter" ጋዜጣ፣ "የካቲት" መጽሔት፣ "ቁምነገር" መጽሔት፣ "ለዛ" መጽሔት፣ "አዲስ አድማስ" ጋዜጣ፣ "ሮዝ" መጽሔት ላይ ከአምደኛነት እስከ ዋና አዘጋጅነት መስራት ብቻ ሳይሆን በሚከተለው የአጻጻፍ ስልት የራሱን አንባቢያን መፍጠር ችሏል።

ስብሐት በተለይም ተፈጥሯዊነት ከሚጎላበት የአፃፃፍ ስልቱና ሕይወቱንም እንደሚጽፈው ለማኖር በሚያደርገው አኗኗር ደጋፊና ነቃፊ የፈጠረ አወዛጋቢ ሰው ነው። ይሁንና ስብሐት ገ/እግዚአብሄር ማንም ይደግፈውና ይንቀፈው ለማንም ይጣምና ይምረር የራሱን የሕይወት መንገድ አስምሮ በዚያ ላይ ሲጓዝ የነበረ ደራሲና ጋዜጠኛ ነው።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ1952 ዓ.ም የባችለር ዲግሪውን ካገኘ በኋላ ለሁለት አመታት የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህር ሆኖ አገልግሏል። ምንም እንኳን ትምህርቱን ሳይጨርስ ቢመለስም ለከፍተኛ ትምህርት አሜሪካና

ፈረንሳይ ሄዷል። ፈረንሳይ ትምህርቱን ባታስጨርሰውም "ትኩሳት"ንና "ሠባተኛው መልአክ"ን ሰጥታዋለች። ሆነም ቀረ ስብሐት በተለይም እሱ የህይወቱ ተልእኮ አድርጎ በያዘው ሥነ ጽሁፍ በየትም ደረጃ የተማረ ሰው ሊያበረክተው ከቢገባው በላይ ከፍ ያለውን ድርሻ ተወጥቷል ማለት ይቻላል። እንደ አፃፃፉ ሁሉ በአኗኗሩም ሕይወትን ከነብጉሯ መግለጽ ይወዳል። ስብሐትን ባህል፣ ይሉኝታና የሌሎች አስተሳሰብ ሳይሆን ህይወት ሊያውም የራሱን ህይወት ናት የምትመራው።ስለዚህም ይሆናል 70 ዓመት እድሜን ከዘለለ በኋላ ከአንዲት ወጣት ብን ያለ ፍቅር ውስጥ የገባው "እናም ተመቻችተናል" ያለው።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ትኩሳት(**ልብወለድ**)
2. ዐምስት ስድስት ሰባት(**ልብወለድ**)
3. ቴዎድሮስ(**ታሪክ**)
4. ታከለ ታገለ(**ታሪክ**)
5. ሌቱም አይነጋልኝ(**ልብወለድ**)
6. ሰባተኛው መልአክ(**ልብወለድ**)
7. እግረ መንገድ(**ወግ**)
8. እነሆ ጀግና(**ታሪክ**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY